የገዛ ራሴን መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ያገኘሁት ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ፣ የዐቢይን ስጦታ በጣም ዋጋ ሰጠሁት። ከዚህ የተነሣ፣ የብሉይ ኪዳኑ ክፍል ልከተለው እና ልረዳው ከባድ ቢሆንብኝም፣ ከማንም ሰው ምሪትን ሳላገኝ በራሴ ማንበብ ጀመርኩኝ። አብዛኞቹ ቅዱስ ገጽታ የተሰጣቸው ታሪኮች መጀመሪያ ላይ ለእኔ በጣም እውነታነት የሌላቸው መሰለውኝ ነበር። አዲስ ኪዳን፣ በተለይም የጳውሎስ መልእክቶች ስሜት የሚሰጡኝ ሆኑ። መጽሐፍ ቅዱስን በመጠኑ በመደበኛነት ማንበብ ጀመርኩኝ፣ ነገር ግን የማርክሲዝም ሥነ-ጽሑፍን እንደማነበው እየተስገበገብኩ እና እያመዛዘንኩ አልነበረም። ነገር ግን ያኔም እንኳን በአእምሮዬ ውስጥ የሚያልፉ አንዳንድ ጥቂት መገለጦች ነበሩ።

አበረ የሚባለውን የአይኢሲ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን እና ወደ ቤተ ክርስቲያን ፈገግታ ባለው ቸርነት ያስተናግደኝ የነበረውን ሰው ለመተዋወቅ የታደልኩት በዚህ ጊዜ ነበር። አበረ የአማኑኤል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ የነበረ ሰው ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያናቸው በአምባገነኑ የመንግሥቱ አገዛዝ ታሳልፈው ከነበረው የስደት ልምምድ የተነሣ ውስጥ ለውስጥ (በሕቡዕ/ ቤት ለቤት) በመንቀሳቀስ ላይ ነበረች። ከሞላ ጎደል ሁሉም የሚሰዮናውያን መገኛ ያላቸው የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው ስለ ነበረ፣ በምሥጢር ሆነው በየሰዎቹ ቤቶች ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። አይኢሲ የውጭ አገር ዲፕሎማቶች እና ከአገራቸው ውጪ የሚኖሩ ሰዎች እንደ አፍሪካ ኅብረት (ያን ጊዜ ኦኤዩ፣ አሁን ግን ኤዩ)፣ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፎር አፍሪካ (ኢሲኤ)፣ ያሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች የሚያመልኩባት ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ስለ ነበረች፣ መንግሥት ሊዘጋው አልደፈረም ነበር።

## ***ወደ መረዳቶች መምጣት***

አበረ እና በርቀት አውቀው የነበረው የቀድሞው የሕግ ትምህርት ቤት ጓደኛው፣ ሽፈራው፣ በዝግታ ጓደኛሞች መሆን ጀመርን። ጓደኛ ያደረጉኝ ምናልባት ብቸኛ እና በመጠኑ ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ድባብ እንግዳ እንደ ሆንኩ በመገመት ሊሆን ይችላል። ከእያንዳንዱ የእሑድ አምልኮዎች በኋላ እንድናወራ በቸርችል ጎዳና ላይ ካሉት የመቀጣጠሪያ ምርጥ ካፍቴሪያዎች ወደ አንደኛው ይወስዱኝና አንዳንድ ጊዜ ለምሳ ወይም ለእራት ይጋብዙኝ ጀመር። ሽፈራው





ሲነግረኝ ከአምስት ዓመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ ታስሮ የሚያውቅ የቀድሞ የኢሕአፓ አባል እንደ ነበረና እግዚአብሔርን ያወቀው፣ ደግሞም የተሰጠ ክርስቲያን የሆነው በእስር ቤት ውስጥ እንደ ሆነ ጠቆም አደረገኝ። እያንዳንዳችንን እግዚአብሔር እንዴት እንደ ተከታተለን፣ ወደ ሽለቆ እንዳመጣን እና በዚያም እንዳገኘን ሲታይ ነገሩ አስደናቂ ነው። በሌላ አነጋገር፣ እርሱ ከተራማጅ የኢሕአፓ ታጋይነት "ዳግም ወደ ተወለደ ክርስቲያንነት" የተለወጠው በእስር ቤት ውስጥ ነበር ማለት ነው። የሚደንቀው ነገር፣ "ዳግም ወደ ተወለደ ክርስቲያንነት" መለወጥ የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ሆነ የተማርኩት ኋላ ላይ ዘግይቼ መሆኑ ነው። ጣዕመ "ዳግም የተወለደ ክርስቲያን" የሚለውን ሐሳብ ጠቆም አድርጎኝ ነበር፣ ነገር ግን በጊዜው ጉልህነቱን ያን ያክል ሳልይዘው ቀረሁ። ስለዚህኛው ጠቃሚ ፍሬ ሐሳብ ከአዲሶቹ ጓደኞቼ አሁን የበለጠ መማር እየጀመርኩኝ ነው።

ከላይ እንደ ገለጽኩት፣ አበረ ያን ጊዜ በድብቅ ትንቀሳቀስ በነበረችው የአማኑኤል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንጌላዊ ሆኖ ያገለግላል። ነገር ግን፣ በአይኢሲ ደግሞ እንደ ዲያቆን ሆኖ በሚያገለግልበት ጊዜ በመጠኑ ቁጥብ ከነበረው ሽፈራው በተለየ በጣም ተግባቢ እና ደስ የሚል ሰው ሆኖ አገኘሁት። ቀስ በቀስ ሁለቱንም ወደድኳቸው ደግሞም አመንኳቸው፣ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር መሆን ቤተኝነት እንዲሰማኝ አደረገ። ኋላ ላይ በሌሎች ጥሩ ክርስቲያን ጓደኞች ታጀብን - አሌ፣ ሚሊ፣ የእንስሳት ሐኪሙ ዜይ እና ያን ጊዜ ለዓለም አቀፉ የቀንድ ከብት ኤጀንሲ ይሠራ የነበረው ለጌ። የእምነት ጉዳዮችን በግልጽ ለመወያየት የሚፈቅዱ፣ ሲበዛ ተንከባካቢ እና ቸር የሆኑ፣ ደግሞም ለምግባቸው እንኳን ሳይቀር ተቀጣጥለው በሚጸልዩ የተሰጡ ክርስቲያኖች መካከል አዲስ የጓደኞች ከበብን ቀስ በቀስ ማዳበር ቻልኩኝ።

አንድ ጊዜ አበረ በማናቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዝግጅት ላይ እሳተፍ እንደ ሆነ ሲጠይቀኝ፣ ስለ ታሪኬ ደግሞም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ መጣሁና ራሴን የማስጠጋበት ቡድን እንደሌለኝ ፍርጥ አድርጌ ነገርኩት። ተከታታይ በሆኑት መገናኘቶቻችን የተሰጠ ክርስቲያን ለመሆን እና ክርስቶስንም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ለመከተል ጠንካራ ውሳኔ፣ ደግሞም የበረታ እርምጃ እንዳልወሰድኩኝ አስተዋለ። በእርግጥ፣ አንድ ቀን ያንን አድርጌ

እንደሆን በግልጽ ጠይቆኛል። ምንም እንኳን የምችለውን ያክል እና በቀረው ዘመኔ ሁሉ ጌታን ሙሉ ለሙሉ ለማወቅ እና ለማመን የቆረጥኩ ብሆንም፣ ሕይወቴን ለክርስቶስ ለመስጠት የትኛውንም የምር መስጠት እንዳላደረግሁኝ በቀጥታ ነገርኩት። ይህንን መረጃ ከእኔ ካገኘ በኋላ፣ ካዛንቺስ ውስጥ በምሥጢር ይደረግ ወደ ነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ይወስደኝ ጀመር። እዚያም አስቀድሜ ጨርሶ የማላውቀው ከሆነው በውስጥ ለውስጥ (ቤት ለቤት) ይንቀሳቀሱ ከነበሩት ቤተ ክርስቲያናት ጋር ተዋወቅሁኝ። ልክ እንደ ኅቡዕ ድርጅቶች፣ ማለትም፣ እንደ ኢሕአፓ፣ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ለውስጥ ትንቀሳቀስ እንደ ነበረ ያወቅሁት ያኔ ነው። በዚያ ጊዜ ያጠናቀቀው ሰባተኛ ክፍልን ብቻ ስለ ነበረ እኔ የነበረኝን ያክል የትምህርት ደረጃ አበረ አልነበረውም። ሆኖም ግን፣ ከአሜሪካውያን እና እንግሊዘኛ ከሚናገሩ ሌሎች የውጭ ዜጎች ጋር ይገናኝ ስለ ነበረ፣ ጥሩ እንግሊዘኛ መናገር ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የተዋጣለት ሰባኪ ነው ለማለት በሚያስችል መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን ቀላል እና ግልጽ በሆነ ቃላት ያቀርባል። እንዲያውም፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሲገልጥ አንዳንድ ጊዜ በጣም ጠለቅ የሚል ሊሆንም ይችላል። ከሁሉ በላይ፣ ከእግዚአብሔር ርቀው ላሉት እና ሕይወታቸውን ግልጽ በሆነ የአቅጣጫ መጠቆሚያ ለማይመሩት፣ ደግሞም ዓላማ ለሌላቸው ሰዎች ትልቅ ልብ እና እንስፍስፍነት አለው።

ከእኔ ጋር በቂ የሆነ መተማመንን ካዳበረ በኋላ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል፣ በተለይም የድነት መልእክትን ግልጽ በሆነ መልኩ ለማስተማር ጥሩ የሚባል ጊዜን በእኔ ላይ ካጠፋ በኋላ፣ የጠፋሁ ሰው መሆኔን በማመን ዮሐንስ 14፡16 እንደሚለው እምነቴን መንገድ፣ እውነት እና ሕይወት ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት እንዳለብኝ በማመን ሕይወቴን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠት ዝግጁ እንደ ሆንኩ ጠየቀኝ። እኔም በበኩሌ፣ ዝግጁ እንደ ሆንኩ ያንን ግን እንዴት እንደማደርግ እንደማላውቅ ስነግረው በእኔ ቦታ ለእኔ ለሞተው፣ በጥልቀት ለሚወደኝ፣ ከነማንነቴ ለተቀበለኝ፣ ልጁ ላደረገኝ እና የዘላለም ሕይወት ለሰጠኝ መላውን ሕይወቴን እንድሰጥ በጸሎት መራኝ። ይህንን ያደረግሁት በቤቱ ይሁን ወይም ከመቀጣጠሪያ ካፍቴሪያዎች በአንደኛው ይሁን በትክክል ባላስታውስም፣ በመቀጣጠሪያው ቦታ ውስጥ ሊሆን እንደሚችል ግን እገምታለሁ። ሁለተኛው የወሰደው እርምጃ እኔን ደቀ





መዝሙር ማድረግ ሲሆን፣ ይህም ሥራ አስቀድሞም ጀምሮት የነበረው በመሆኑ፣ በበለጠ ፍስሐ እና ፍላጎት ያደርገው ዘንድ ቀጠለ። ያኛው እርከን ባለቀ ጊዜ፣ ለመጠመቅ ፈቃደኛ እንደ ሆንኩ ሲጠይቀኝ ዝግጁነቴን ገለጽኩለት። ክርስቲያኖች በጥምቀት ልምምድ ውስጥ በማለፍ ለምን ክርስቶስን መታዘዝ እንዳለባቸው እና ጥምቀትም ለድነት መንገድ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ክርስቶስን ለመከተል ተምሳሌታዊ መሰጠት እንደ ሆነ አንዳንድ ትምህርቶችን ይሰጠኝ ጀመር። ያንን ተከትሎ የቤት ለቤት ቤተ ክርስቲያን በሆነችው የመጋቢው ቤት ውስጥ ባለ የመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ በመጋቢ በቀለ ላቀው እጅ ጠልቄ ተጠመቅሁኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል መሆኔ ታወጀ - የኢጥቢያዋና የዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን። በጥቅሉ፣ እግዚአብሔርን እኔን ያገኘው እና የድነት መንገድ ያሳየኝ፣ ደግሞም ልጁ እና የቤተ ክርስቲያን አካል ባለድርሻ እንድሆን ያደረገኝ በዚህ መልኩ ሲሆን፣ ለዚህም ደግሞ ሁልጊዜ እርሱን አመሰግነዋለሁ። ከሁሉ በላይ፣ ይህንን ያደረገው ከጄው እና በሕዝብ ፊት ቀልጄበት ለነበርኩት ለእኔ ለኃጢአተኛው ነው። ሆነ ብዬ ከእርሱ በኮበለልኩባቸው እና ለሕዝቦቹ ደስታ በፈጠረው በዚህ ውብ ዓለም ውስጥ ቤት-አልባ እንደ ሆንኩ ይሰማኝ በነበረበት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በኖርኩባቸው በእነዚያ ሁሉ ዓመታት ቆይታ ውስጥ ድንቅ በሆነችው እጁ ሰወረኝ። የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመለማመድ፣ ራሴን ለመቀበል እና እረፍት-አልባ በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ እረፍት የሞላው ኑሮ ለመኖር ለእኔ ምንም ዓይነት መንገድ ያለ አይመስልም ነበር። አንድ ጊዜ ሐረር ውስጥ ሳለሁ እያለፍኩበት የነበረውን ትርምስ እና "መታፈን" ለማምለጥ ስል ወደ ጫካይቱ ምድር ወደ ኢሊባቡር ለመሄድ እውነተኛ ፍላጎት ተሰምቶኝ የነበረበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። እንዲህም የተሰማኝ ጫካው አንዳች ዓይነት ምትሃታዊ የፈውስ አቅም ኖሮት ሕይወቴን ሊያነቃቃልኝ የሚችል ያክል ስለ ተሰማኝ ነበር።

ሁሉንም ነገር ከግምት በሚያስገባ መልኩ ብርቱ እና በሳል ወደ ሆነ ክርስቲያንነት የማድግበት ሂደት ከልክ በላይ ረጅም ጊዜን ወሰደ። እንደ ክርስቲያን የምኖረው ኑሮ እና ሃይማኖቱ ለእኔ የቀረበበት መንገድ ሙሉ ለሙሉ የተለየ ጨዋታ ሆነብኝ። "የጦርነት ቀጠናውን እንደ ተሻገርኩ" እና በአሸዋ ላይ ድንበር እንዳሰመርኩኝ አወቅሁ። አዲስ የመከተቻ ደንቦችን መቀበልን በሚጠይቀው አዲሱ የሕይወት ግዛት ውስጥ ደንገተኛ ጠልቆ መግባትን

ማድረጉ ከባድ እንደሚሆን ግልጽ ሆነልኝ። ስለዚህም፣ ሕይወቴ ከፍ ብሎ በከፍታ የሄደበት ደግሞም ዝቅ ብሎ የወረደባቸው ቀናት ስለ ነበሩ፣ የተሰጠ ክርስቲያን ሆኖ መገኘት ለእኔ አንዳች ዓይነት ከፍታ እና ዝቅታ ውስጥ በማለፍ ሕይወትን ማስመስከርን ጠይቆኛል። ይህም ሊሆን የቻለው የእኔን መንገድ በቀላሉ ልትከተል ካልቻለችው የሴት ጓደኛዬ ጋር ከነበረኝ አባጣ ጎርባጣ ግንኙነት የተነሣ፣ እንዲሁም ደግሞ እስከዚያ ጊዜ ድረስ አንዳንድ ማራኪነትን ይዘው የነበሩና ሕይወቴን ጫና የሚያሳድሩ የሐረር ጓደኞቼ ጋር ግንኙነቴን ከመጠበቄ ነበር። ከአሮጌው የሕይወት ዘይቤዬ ተራማጅ የሆነ መለየት እንዳደረግሁ ለሁሉም ጓደኞቼ ግልጽ በሆነላቸው ጊዜ ላይ፣ ያን ጊዜ የሴት ጓደኛዬ የነበረችው አዜብ እንኳን ሳትቀር ይህንን በቀላሉ አስተዋለችው። ምንም እንኳን ቢራ መጠጣትና ማጨስ ባቆምም፣ ካስቀመጥኳቸው የሕይወት ደረጃዎች የምወድቅባቸው አጋጣሚዎች ስለ ነበሩ፣ በውስጤ የሚያመረቅዝ እና ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝን ጉዞ የሚያበላሽ ኃጢአት-ነክ የሆኑ ችግሮች በሕይወቴ ተከስተው ያውቃሉ። ያ በሚሆንበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በእኔ መገኘት መርከስ የሌለባት ቅዱስ ስፍራ ነች በሚለው እምነት ተመሥርቼ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ እታቀባለሁ። በአይኢሲ የአምልኮ ዝግጅቱን ባልተገኘሁ ቍጥር አበረ ስለ ሁኔታው ይጠይቀኝ ነበርና፣ የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ በግልጽነት እናዘዝለታለሁ። ያን ጊዜ እርሱም በበኩሉ፣ ሁላችንም በማይለዋወጡ መንገዶች አንዱ ከሌላው የሚለይ ኃጢአትን እንደምናደርግ፣ ነገር ግን "ኃጢአት በበዛ ቍጥር ጸጋም እንደሚበዛ" ነግሮኝ ያጽናናኝ ነበር። የዚህን ንግግር ጥልቀት ከነገረ-መለኮት አኳያ ሙሉ ለሙሉ ባልይዘውም - ጭነተ-ሙሉው አገላለጽ እርምጃዎቼን እንደገና እንዳስብባቸው እና በንስሐ ወደ መንገዴ እንድመለስ መገለጥን ሰጠኝ። ስለዚህም፣ በሐሳቦቼ፣ በአመለካከቶቼ እና በድርጊቶቼ ላይ አዳዲስ ስሜታዊ ሁኔታዎችን እንዳዳበርኩኝ አስተዋልኩ። ያም ደግሞ ምንም እንኳን የአልፎ አልፎ መዋዠቆችን እና አባጣ ጎርባጣ ነገሮችን የማሳልፍ ብሆንም፣ ከዚህ ቀደም ሳልቀጣ እንደምቀርበት ሕይወት ያሉትን ነገሮች እንዳላደርግ የከለከለኝ አዲስ ንቃተ ሕሊና ሆነልኝ።

ቀጣይነት ላለው መንፈሳዊ እድገቴና ሂደቴ በእሑድ አምልኮዎች እና አልፎ አልፎ በአበረ ቡድን ውስጥ የማደርጋቸው ስብሰባዎች ብቻቸውን በቂ እንዳልሆኑ ስለ ተገነዘብኩኝ፣ ከዚያ ያለፈ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ።





በዚህ ስሜት ውስጥ እያለሁ፣ *"ሥሩ ዘ ባይብል* የተሰኘው እና በዶ/ር ቬርኖን ማክጊ" ይዘጋጅ የነበረ ክርስቲያናዊ ሬዲዮ እና ከኬኒያ/ሲሼልስ ይተላለፍ የነበረ የአማርኛ የወንጌል ክርስቲያናዊ ሬዲዮ (ትራንስ ወርልድ ራዲዮ) አገልግሎት እንዳለ ደረስኩበት። እነዚህን የሬዲዮ ዝግጅቶች ማድመጡ ከእግዚአብሔር ቃል አዳዲስ መገለጦችን እንዳገኝ እና አይኢሲ ወዳለው የእሑድ አምልኮ እስከሄድ ድረስ እምነቴን ለመጠበቅ ረዳኝ። ባጭሩ ግን፣ አይኢሲ ውስጥ ከመጋቢ ባርክ እና ሌሎች ተጋባዥ ሰባኪዎች አገኝ የነበሩት ኃይለኛ መንፈሳዊ ትምህርቶች ብርቱ የእምነቴ ማነቃቂያዎች እና ዋና ምንጮች እንደ ነበሩ ምንም ጥርጥር አልነበረውም።

አንዳንዶች እንደሚገምቱት ቀላል ነገር ባይሆንም፣ እንዴት በሂደት እንደምጸልይ የተማርኩበትን ሁኔታ ከርእሴ በጥቂቱ ልውጣና ትረካውን ላካፍላችሁ። የአበረ ጓደኛ ሽፌ ለሠርጉ ቀን ከሚዜዎቹ አንደኛው እንድሆን ጠየቀኝ። በክርስቲያናዊው ዓለም ውስጥ ጀማሪ እንደ መሆኔ ያንን ሚና ለመወጣት ዝግጁ አልነበርኩኝምና ማቅማማት ስጀምር፣ ከተሞክሮው የምጠቀመው ነገር እንዳለ እና በረከቶችንም እንደምቀበል ነግሮ አደፋፈረኝ። ምንም እንኳን እያጉረመረምኩ ቢሆንም፣ ኃላፊነቱን ተቀበልኩኝና በሠርጉ ዋዜማ ሙሽራው ለሙሽሪት የገዛቻውን አልባሳት እና ሽቶዎች ጥሎሽ አድርገን ልንሰጥ ሄድን። ከሞላ ጎደል ምንም አላውቀውም ሊባል የሚችለውን የወንጌል መዝሙሮች የምንዘምርበት ሥርዓት ውስጥ ጥቂት ጊዜ ካሳለፍን በኋላ፣ ለእራት ተቀመጥን። ብዙም ሳይቆይ፣ እንግዶችን ከሚያስተናግዱት ቤተሰብ መሪ የሆኑት አንደኛው ሰው ለእራቱ እንድጸልይ ጠየቁኝ። ከዚያ ቀን በፊት በሰዎች ፊት ጸልዬ ስለማላውቅ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። እንደ ዕድል ሆኖ አበረ ከእኔ ጎን ተቀምጦ ነበርና እንዲረዳኝ ልጠይቀው ወዲያውኑ ሐሳብ መጣልኝ። በዚህ ጉዳይ ላይ እባክህ ልትረዳኝ ትችላለህን ብዬ ሳንሾካሹክለት ፈቃደኛ ሆኖ ራሱን በመስጠት በሰዎች ፊት ከማፈር አተረፈኝ።

የሥራ ባልደረባዬ እና ውድ ጓደኛዬ ከሆነው ከጦምቲ ጋር ሆነን አዲስ የተጋቡ ጥንዶችን ለመጎብኘት የሄድንበትንም አጋጣሚ አስታውሳለሁ። ለተወሰነ ጊዜ በጥንዶቹ ቤት አብረን ቆየንና ከመሄዳችን በፊት የእግዚአብሔርን ቃል እንድናካፍል ስንጠየቅ፣ አንዳችን ለሌላችን 'ጉዳችን ፈላ' ተባባልን። አንዳችንም ብንሆን እንኳን በተጠየቀው መንገድ ቃል ልናካፍል ቀርቶ አንዲት ጥቅስ

ብትሆን እንኳን የማካፈል ልምዱ አልነበረንም። በዚያን ዘመን እንኳን አዲስ የተጋቡ ጥንዶችን ቀርቶ አንድን ቤተሰብ በምትጎበኙ ጊዜ "ቃል ማካፈል" የሚባለው ነገር ዓይነተኛ ልማድ እንደ ሆነ ስለ ተረዳሁ፣ እነዚህን ነገሮች በልምድ ልማራቸው የሚገባኝ ነገር ሆነ። ጓደኛዬ የመጣው ከደቡብ እስከ ሆነ ድረስና የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ዳራ ያለው በመሆኑ ይህንን 'ማካፈል' የተባለውን ነገር እርሱ ሊያደርገው ይችል እንደ ሆነ ስጠይቀው፣ ፈገግ አለና የትኛውን ጥቅስ ማካፈል እንዳለበት መልሶ ጠየቀኝ። ከጳውሎስ መልእክቶች አንደኛውን ቢያካፍል ዓላማችንን እንደሚያሳካልን ነገርኩትና እንዲያው በዘፈቀደ ከቆሮንቶስ መጽሐፍ አንድ ጥቅስ አውጥቶ ለእኔ ምንም ትርጉም ያልሰጠ፣ ለጥንዶቹ ግን በጥሩ ሁኔታ የተቀበሉትን ቃል አካፍሏቸው ወጣን።

መጽሐፍ ቅዱስን ችላ ብዬ አበረ የሚመራው የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረት ውስጥ ምንም ላልሳተፍ እገኝ ስለ ነበር፣ ከኢየሱስ ጋር በነበረኝ አዲስ ጉዞ ውስጥ አንዳች ዓይነት የተደበቀ ኩራት እንዳለኝ ማስተዋሉ ለእኔ ከባድ አልነበረም። ከስንት ጊዜ አንዴ ግልጽ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ወይም አንዳንድ ጥርጣሬ በፈጠሩብኝ ላይ አንዳንድ ኮስታራ ጥያቄዎችን አነሣለሁ። ነገር ግን ለውይይት በሚቀርቡ ርእሶች ላይ የዩኒቨርስቲ መምህር ሆኜ ሳለ የማውቀው ግን ትንሽ ብቻ መሆኑን እንዳይታወቅብኝ ስለምፈራ በነጻነት ከመሳተፍ እታቀባለሁ። አንድ የሆነ ቦታ ላይ፥ ይህ እንደማይረዳኝ ስላወቅሁኝ ሐቀኛ መሆንና ለመማርም ሆነ አስተዋጽዖ ለማበርከት ጭምር መሳተፍ እንዳለብኝ ወሰንኩ። ለዚህ ደግሞ እውቀት እና ብርታት ያስፈልገኝ ስለ ነበር፣ ይህ አዲስ መንገድ ከጠበቅሁት በላይ ረጅም ጊዜ ወሰደብኝ። በሌላ መንገድ ደግሞ፣ በበቂ አለመሳተፌ ሙሉ ለሙሉ ከኩራት የመነጨ ላይሆን እንደሚችል እገምታለሁ። ምናልባትም መጥቶ ሊሆን የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል በፍርሃት ልንነጋገርበትና ልንወያይበት ይገባል ከሚለው መረዳቴም የመጣ ሊሆን ይችላል።

ምንም እንኳን በጌታ አዲስ ያገኘሁት እምነት፣ በዝግታ ፍጥነት የመጣ ቢሆንም በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ወደ ሆነ ለውጥ መራኝ። ምንም እንኳን ለውጡ በዋናነት ውስጣዊ ቢሆንም፣ እንዲሁም ደግሞ ግልጽ የሆኑ ሌሎች የለውጡ መገለጫዎችም ይታዩ ጀመር። ሕይወቴን መልሼ የምመራበትን አዲስ ማዕከላዊ እሴቶችን ከማግኘቴ በተጨማሪ ሕይወትን የምሬን እያዛት ዘንድ





ጀመርኩኝ፣ ደግሞም በአሮጌው ሕይወቴ ላይ ይሠሩ የነበሩት አጥፊ ኃይላት ወደ አዲሱ ሕይወቴ ዘልቀው ይሰራጩ ዘንድ ዕድል ሊኖራቸው አልቻለም። ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ትዳር በመመሥረት በሕይወት ውስጥ ሰከን መቀመጥ ፈለግሁኝ። ከአዜብ ጋር የነበረኝ ግንኙነት የሚቀረቀር ስለ ነበረ የሚሠራ ነገር እንዳልሆነ አወቅሁና ክርስቲያን የሆነች ሚስት ለማግኘት የምሬን ማሰብ ጀመርኩኝ። አሁን ሕይወቴ የበለጠ ሥርዓት ይዟል፣ በትምህርቴ በርትቼ የሠራሁ ሲሆን ጥሩም ሆኖልኛል፣ ዝርክርክ ከነበርኩበት ከቀድሞው ዝንባሌዬ በተለየ ጨዋ በሆነ መልኩ መልበስም ጀምሬያለሁ። ጌታን ከማግኘቴ በፊት ግን፣ ለልብሶቼ መቼም ጨንቆኝ የማላውቅ ግድ-የለሽ ሰው በመሆኔ ስታወቅ ቆይቻለሁ። ከመጠጥ እና ማጨስ ከመታቀቤ የተነሣ ገንዘቤንም ብዙም የማላጠፋ በመሆኔ ከቀድሞው ይልቅ ለበለጠ ጠቃሚ እና ምርታማ የሚሆኑ ዓላማዎች የምጠቀመው ገንዘብ በእጄ ላይ ይበረክትልኝ ጀመር። ብዙም ባይሆን ትንሽ ክብደት ስለ ጨመርኩኝ፣ ደግሞም እፊቴ ላይ የሚንጸባረቅ ጸጋም ስለ ነበረ፣ ለውጤ በአካላዊ ሁኔታዬ እንኳን ግልጽ ሆኖ ታየ። በአጭሩ፣ በዚህ ዓለም ላይ ለመኖር የሚፈልግ የተሻለ እና የበለጠ የተረጋጋ ሰው መሆን ጀመርኩኝ። ብርቱ የሆነውን መልህቅ እንደ ማግኘቴ፣ በኃላፊው ጊዜ ውስጥ ሕይወቴን ይገልጸው የነበረው "ቤት-አልባነት" ባልታወቀ መንገድ ከእኔ ዘንድ ጠፋ።

ከዚያም በላይ፣ ሕይወቴን የቀየረውንና እኔ የተቀበልኩትን የምስራች ከጓደኞቼ ጋር ለመካፈል አዲስ ናፍቆት በሕይወቴ ውስጥ እየተጠነሰሰ ስለ ሄደ፣ በእኩዮቼ እና ጓደኞቼ መካከል ወንጌላዊ ሆንኩኝ። ከሞላ ጎደል ለሁሉም ጓደኞቼ በሕይወቴ ካገኘኋቸው እውቀቶች መካከል ትልቁ እውቀት በኢየሱስ እግዚአብሔርን የማወቅ እውቀት እንደ ሆነ በድፍረት እና ሳላፍር ነገርኳቸው። በትርፍ ጊዜዬ ወደየቤታቸው እየሄድኩኝ በታማኝነት ጓደኞቼን አነበኞቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ እገዛላቸውና እንደ ስጦታ አበረከትላቸው፣ ደግሞም ኢየሱስ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት እንደ ሆነ እነግራቸው ጀመር። አንዳንዶቹ ጓደኞቼ በአዲሱ ሚናዬ ይደነቁ እንጂ፣ የምራቸውን እና በአክብሮት ይሰሙኝ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እንደ ሰይፈቲ ያሉ ለውጥን ተቃዋሚ ሰዎችም ቢኖሩም፣ የሚያስደስተው ነገር የኋላ ኋላ በሕይወቱ አንደኛው እርከን ላይ ጌታ ሰይፈቲን አስደናቂ በሆኑ ሁኔታዎች መካከል አገኘው።

ምንም እንኳን ብቸኛ ዓላማው ያ ሊሆን ባይችልም፣ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን በጊዜው እንዳጠናቅቅ ብርታት እና ወኔ ስለ ሰጠኝ፣ እምነቱ ተሞክሯዊ ጥቅሞች ጭምር ነበሩት። ወደ አሥመራ ዩኒቨርስቲ ከመመለሴ በፊት አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ዓመት ለመቆየት ከመፈለግ የተነሣ፣ ትምህርቴን ለመጨረስ አቅማምቼ ነበር። እግዚአብሔር መልካም ነው! ምክንያቱም ትምህርቴን በአንድ ዓመት አስረዝሜው ቢሆን ኖሮ እባረር፣ ደግሞም ለመማር የሚኖረኝ ዕድል ይቋረጥ ነበር። ዩኒቨርስቲው በጊዜው ማጠናቀቅ ስላለባቸው ሰዎች ማስታወቂያን/መመሪያን አሠራጭቶ የነበረ ሲሆን፣ ማስታወቂያውም ትምህርታቸውን ከአራት ዓመታት በላይ የሚገፉ ተማሪዎች ብቃት እንደሌላቸው ተቆጥረው ከሥራዎቻቸው እንደሚባረሩ የሚገልጽ ነበር። ይህ በሚያሳዝን ሁኔታ አሥመራ ዩኒቨርስቲ ይሠሩ የነበሩ እንደ አሌክስ እና ሌሎችንም ዓይነት ጥሩ ጓደኞቼን ያጠቃ ነገር ሲሆን፣ እኔ ላመልጠው የቻልኩት እንዲያው በእግዚአብሔር ጸጋ ነበር።


በሁለተኛ ዲግሪዬ ምረቃ

## የእግዚአብሔርን ኃይል ማግኘት

ጌታ ኢየሱስ በሕይወቴ ውስጥ ፍቅሩንና ኃይሉን የገለጸበት አስገራሚ ነገሮችን አደረገ። ከአራት ኪሎ የዩኒቨርስቲው መኖሪያ ወጥቼ ከልጅነታችን ጀምሮ ሐረር ውስጥ ጥሩ ጓደኛዬ ወደ ነበረው እና ለድኅረ-ምረቃ ትምህርት ወደ አሜሪካን ወደሚሄደው፣ በጥሩ ሁኔታ ዕቃ ወደ ተሟላለት የታዴ ቤት ተዘዋወርኩኝ። ቤቱ የሚገኘው አዲስ የመኖሪያ ሠፈር በሆነ ቦታ ሕዝብ ከሚበዛበት አካባቢ ራቅ ብሎ ስለ ነበር፣ ትኩረት ማድረግ እና ስለ ጅጅጋ ታሪክ የማዘጋጀውን የጽሑፍ ውጥን-ሥራ ማከናወን ቻልኩኝ። ትርፍ ክፍል ስለ ነበረ በጣም የምወዳትን እናቴን ከእኔ ጋር እንድትኖር ከሐረር ይዣት በመምጣት በሕይወቴ ላከናውናቸው ከማስባቸው ነገሮች አንደኛውን አሳካሁ። ሁልጊዜ አብራኝ አልኖረችም፣ ነገር ግን ከእኔ ጋር በቆየችባቸው በእነዚያ ወራት፣ ከእኔ ጋር መሆኗ ለእኔ ብዙ ነገር ማለት ሆነልኝ።

ከአዜብ ጋር የነበረኝ ያልተረጋጋ ግንኙነት ባልታወቀ መልኩ አበቃ።





በቀደሙት ዘመናት ውስጥ በርካታ የተጎሳቆለ ግንኙነት የነበረን ሲሆን፣ ደግሞም እንደማይዘልቅ ግልጽ ምልክቶች ነበሩ። ግንኙነታችንን ከቀየሩት በረከቶች አንዱ እርሷ ራሷ መጨረሻ ላይ ወደ ጅጅጋ ለመሄድ እና የወላጆቿን የሆቴል ንግድ ሥራ ልትመራ እንደሚያስፈልጋት መወሰኗ ሲሆን፣ ‘በረከት’ ነው ልልበት የቻልኩበት አንደኛው ምክንያት ከዚያ በኋላ የመመረቂያ ጽሑፌ ላይ ሙሉ ለሙሉ ማተኮር መቻሌ ነበር። ግልፍተኛ ከሆኑት ልዩነቶቻችንና ለዓመታት ከነበረን የተጎዳ ጓደኝነት የነተሣ፣ ግንኙነታችን ወደ ደስተኛ ትዳር ሊመራን የሚችልበት ምንም ዕድል አልነበረውም። በዚያ የጊዜ ስንዝር ውስጥ፣ በክርስትና እምነቴ በሰልኩ ደግሞም ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጠንካራ እና የሚያድግ ግንኙነትን መገንባት ቻልኩ። ያለምንም ጥርጥር፣ በምሁራዊ ጉዞዬም እንዲሁ የተሻልኩ መሆን የጀመርኩት ያኔ ነው።

እግዚአብሔር ራሱን ወደ እኔ የሚያስጠጋበት ሌሎች መንገዶችም ነበሩት። አንዳንዶቹ ተዓምራታዊ ክስተቶች ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ በሕይወቴ ላይ ጫን ያለ ምልከታ በማድረግ ውስጥ ከወሳኝ ማገናዘብ እና የጸኑ ጸሎቶች ጋር ሆኜ ያወጣኋቸው ትምህርቶች ነበሩ። አንድ ጊዜ፣ አሁን ላይ ገርጂ ተብሎ ወደሚጠራው አዲስ መኖሪያ አፓርታማዬ አቀናሁ። የሄድኩትም በፀሐይ መጥለቂያ ወቅት ምሽት ላይ ስለ ነበር ብርቱ ነፋስ አንዳንድ አቧራ እና ሌሎች ነገሮችን በማንሣት ወደ እኔ አቅጣጫ ሲነፍስ ነፋሱ ያመጣውና እግሬ ሥር የጣለው ቁራጭ ወረቀት ትኩረቴን ሳበው። በላዩ ላይ አንድ ነገር በእርሳስ ተጽፎ ስላየሁ አንሥቼ ሳነብበው፣ "እግዚአብሔር አይታለልም" ይላል። ወዲያውኑ፣ "ይህ ቁራጭ ወረቀት በነፋስ ተገፍቶ እንዴት ሊመጣ ቻለ? እግዚአብሔር ካልሆነ፣ ይህንን ማን ሊያደርገው ይችላል? ይሄ እንዲያው በአጋጣሚ የሆነ ነገር ነውን?" የሚሉ ጥያቄዎች ወደ አእምሮዬ ጎረፉብኝ። በእነዚህ ጥያቄዎች እየታገልሁ እያለሁ፣ ጠለቅ ባለው <u>እግዚአብሔር አይታለልም!!!</u> በሚለው አገላለጽ ፋይዳ ላይ አሰላስል ጀመር። ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ በርካታ ነገሮችን፣ በተለይም ስለ ሐቀኝነቱ ብዙ የሚል ሆኖ አገኘሁት። እግዚአብሔር በዚህ ወረቀት በኩል ተናገረኝ! ይህንን ጠለቅ ያለ "ሰማያዊ" መልእክት እስካሁን ባለኝ ጉዞ ውስጥ ምን ያክል እንደማስታውሰው ራሴን እጠይቃለሁ።

ከጌታ ጋር የነበረኝ ግንኙነት እያደገ ነበር፣ ነገር ግን በክርስትና ተሞክሮዬ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ያልተረዳኋቸው አንዳንድ ክልሎች ይገጥሙኝም ነበር። ለምሳሌ፣ አንድ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች አንደኛው በነበሩት ጋሽ ከንዲያ ቤት ውስጥ በድብቅ ይካሄድ የነበረ የመነቃቃት ስብሰባ ተካሄደ። በዝግጅቱ ማብቂያ ላይ አንዲት ሴት በጸሎት እየመራች ሳለ፣ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከጌታ ዘንድ የጥበብ ቃላትን ተቀበለችና ለጉባዔው ትገልጠው ጀመር። መልእክቱን ከተቀበለችና ከተናገረችው በኋላ፣ ይህ መልእክት የሚመለከተው ሰው እንድጸልይለት እጁን ያንሣ ብላ አከለችበት። ለተናገረችው ነገር ምላሽ የሰጡ በርካቶች ነበሩና ወደየነበሩበት እየሄደች እጃቸውን በመጫን ትጸልይላቸው ጀመር። አንደኛው ከቀኝ ዓይኔ ችግር ጋር በተያያዘ፣ ሌላኛው ደግሞ ከቀኝ እግሬ ጋር በተያያዘ የነበሩ ሁለት ችግሮችን ስለ እኔ አያሰለሰች ተናገረች (በእርግጥም፣ ስለ እኔ የመጡ ትክክለኛ መልእክቶች ነበሩ)። መልእክቱ ለእኔ እንደ መጣ በእርግጠኝነት እያወቅሁ፣ ነገር ግን ተለይቶ በመታወቅ በጉባዔው ፊት ለመውጣት ብርታት አጣሁ። ዓይኖቼን ገልጬ ስመለከታት በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ያለች እና በጥሩ ሁኔታ ያልለበሰች ሴት መሆኗን በመገመቴ የሰዎችን ትኩረቶች ወደ እኔ መሳቡን አስፈሪ ሆኖ ስላገኘሁት፣ ተደጋጋሚ ልመናዋን ቸላ አልኩት። ከዚያ ይልቅ፣ በዝምታ ውስጥ ጠልቄ ስለ መላው ሁኔታ እያሰብሁ እያለሁ እንዲህ ማለት ጀመረች፤ "በዚህ ጉባዔ ውስጥ እዚህ ምን እየተከናወነ እንደ ሆነ በማሰብ ላይ ያለ እና በአእምሮው ጥያቄዎችን የሚጠይቅ አንድ ሰው አለ። ጌታ ሕይወትህን መንካት ይፈልጋል። እባክህን እጅህን አንሣ።" መልእክቷ ያን ያክል ግልጽ ሆኖ ሳለ፣ ትግል ውስጥ ግን ገብቼ እጄን ሳላነሣ ቀረሁ። ነገር ግን፣ በመጨረሻ በቂ ብርታትን አሰባስቤ እጄን ሳወጣ የተቀመጥኩት መጨረሻ ላይ ነበርና እጄን ማውጣቴን ወዲያውኑ ሳታስተውለው ቀረች። ይህም ሁኔታ ለአፍታ እጄን ትንሽ ዝቅ ለማድረግ ዕድል ሰጠኝ። ከእኔ ጀርባ የነበረችው ሴት "እባክህን እጅህን አንሣ። ጌታ ምሕረቱን እያሳየህ ነው" አለችኝ። "ስለ ነገሩ ኋላ ላይ እጸልይበታለሁ" ስልም መለስኩላትና እጄን ሳላወጣ ቀረሁ፤ ለመንፈሳዊ ልምምዴም አንዳች ጠቃሚ የሆነን ነገር አጣሁ።

ስብሰባው ካለቀ በኋላ፣ ከማውቃቸው እና ከማከብራቸው ሰዎች መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ በሴትየዋ በኩል እንደ ተናገራቸው መስማት ጀመርኩኝ። የቀድሞው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የነበሩትና ያን ጊዜ ኢሲኤ ውስጥ ይሠሩ የነበሩት ሰው ሚስት የሆኑ አንዲት ሴት ወዲያውኑ ስለ ተቀበሉት ፈውስ ጌታን





ሲያመሰግኑም አየሁ። ሌሎችም እንዲሁ ታሪኮቻቸውን በመናገር ሲመሰክሩ ወደ ቦታው የጋበዘኝና ያን ጊዜ ለኢትዮጵያ አውራ ጎዳና ባለ ሥልጣን መሐንዲስ ሆኖ ይሠራ የነበረው ሰው በጣም እየፈለገው እያለ እርሱን በተመለከተ የመጣለት አንድም የእውቀት ቃል ባለመኖሩ ተስፋ መቁረጡን ተናገረ፤ ያም ትኩረቴን ሳበው። እኔ ሦስት ዕድሎች እየነበሩኝ ሁሉንም ግን ስላጣኋቸው፣ አንድ ችግር ሳይኖርብኝ አይቀርም ብዬ አሰብኩኝ። ከአገልጋዩዋ እየመጣ የነበረውን መንፈሳዊ ምልክቶች ለይቼ ማየት እንዳልችል ያደረገኝ አንዳች ነገር አእምሮዬን ሸፍኖታል ብዬ ለራሴ ተናገርኩኝ። ከመንፈስ ቅዱስ አሠራር ጋር በተያያዘ ላውቀው እና ልለማመደው የሚገባኝ መንፈሳዊ ክስተት እንዳለ ተረዳሁ።

በክርስትናዬ ውስጥ በኃይል ሕይወቴን የነካው ሌላኛው ልምምድ በ1981 ዓ.ም አንድ እሑድ ላይ ከጠዋቱ 3:00 አካባቢ የተከናወነው ነገር ነበር። በመመረቂያ ጽሑፌ ላይ እየሠራሁ እንደ መሆኑ፣ ወደ መኝታ የምሄደው እያመሸሁ ሆነ። በአንደኛው ጠዋት ወደ 3:00 ገደማ በሕልሜ ኢሳይያስ 32 እና ኢሳይያስ 66 በቀይ ማርከር እኔ ከምተኛበት ክፍል ቀጥሎ ባለው በር ላይ ተጽፎ ይኸንኑ በሕልሜ ያየሁትን ነገር በግልጽ በማስታውስበት ሁኔታ ነቃሁ። ወዲያውኑ፣ ዐቢይ የሰጠኝን እንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ አነሣሁና ምዕራፎቹን ማገላበጥ ጀመርኩኝ። በእውነት ለመናገር፣ በዚያን ጊዜ ስለ ብሉይ ኪዳን የማውቀው በጣም ጥቂት ነበርና በኢሳይያስ ላይ ያነበብኩትም ሆነ የሰማሁት የትኛውም መልእክት አልነበረም። ስለዚህም፣ ምዕራፎቹን ለማግኘት የተወሰነ ጊዜ ከወሰደብኝ በኋላ፣ ሁለቱንም ምዕራፎች ከልቤ ሆኜ አነበብኳቸው። ደግሞም ለምን እንደ ሆነ እንጃ ብቻ ኢሳይያስ 32 ከሌላኛው ምዕራፍ በላይ ማረከኝ። ይህንን ንባብ ሳጠናቅቅ፣ "ይህ እንግዳ የሆነ ልምምድ ምንድን ነው? ክርስቲያኖች •ራእይ• ብለው የሚጠሩት ይሄንን ነው እንዴ?›› በማለት ራሴን ጠየቅሁት። አስገራሚ አጋጣሚ ነበርና እንዴት ትርጉም እንዲሰጠኝ ማድረግ እንደምችል በጊዜው ላውቅ አልቻልኩም። ከእግዚአብሔር የመጣ ነገር እንደ ሆነ ባውቅም፣ አልገባኝም ነበርና ወደ አልጋዬ ተመልሼ ልተኛ ስሞክር ሊሳካልኝ አልቻለም። እንዲሁ ወደ ግራና ቀኝ ስገላበጥ እንዳነጋሁ ጠዋት 3:00 ላይ ከኬንያ የሚተላለፈውን የክርስቲያን ራዲዮ ፕሮግራም መስማት እንዳለብኝ ተሰማኝ። ከራዲዮ ዝግጅቱ የምሰማው ነገር በሕልሜ ካየሁት ነገር ጋር የሚያያይዘው ነገር እንዳለው እያሰብኩ ሳለሁ፣ ቄስ ሙሴ ሰለሞን የሚባሉት

አገልጋይ የዕለቱ መልእክት ከኢሳይያስ 32 እንደሚሆን ልክ ራዲዮኔን በከፈትኩበት ቅጽበት ሰማሁ። ማድረግ ያለብኝን ባለማወቅ ከአልጋዬ ውስጥ ዘልዬ ወጣሁና ጌታዬን ባልተለመደ አኳኋን ማምለክ ጀመርኩኝ- አንዳንዴ ወለሉ ላይ በመነጠፍ፣ አንዳንዴ አምልኮቴን ለመግለጽ እጆቼን ወደ ሰማይ በመዘርጋት። ወዲያውኑ እግዚአብሔር ለእኔ መልእክት እንዳለው አወቅሁኝ፣ በእርግጥም፣ እርሱ በልቤ ደጃፍ ቆሞ የምሩን በር እያንኳኳ ነበር።

ሊቆም በማይችል የደስታ እና የመደነቅ ሁኔታ ውስጥ እየተምላሁ ከካሴቶች አንደኛውን አንሥቼ በፍጥነት መላውን መልእክት ቀዳሁት። ይሄ መለኮታዊ መልእክት ከሰማይ በቀጥታ ለእኔ ይዞ የመጣ መለኮታዊ የተዓምር አጋጣሚ እንደ ሆነ ግልጽ ስለ ሆነልኝ በሕልሜ ስላየሁት ሌላኛው ምዕራፍ፣ ስለ ኢሳይያስ 66 ማሰላሰል ጀመርኩኝ። ምዕራፉ፣ በሕልሜ ከኢሳይያስ 32 ጋር በሚገናኝ መልኩ እንዴት ሊመጣ እንደ ቻለ አመክንዮታዊ ሆኜ መተንተን ጀመርኩኝና መልሱ ለእኔ በጣም ግልጽ ሆነልኝ። የእኔን ተጠራጣሪ አእምሮ የሚያውቀው እግዚአብሔር ሕልሙ ከእርሱ ዘንድ እንጂ፣ ከሌላ ከየትኛውም ምንጭ እንዳልሆነ አረጋገጠልኝ። የኢሳይያስ መጽሐፍ 66 ምዕራፎች ያሉት እና ምዕራፍ 66 ከሌላኛው ምዕራፍ ጋር የሚመጣበት የራሱ ምክንያት ያለው ነበር። በሕልሜ ያየሁት ኢሳይያስ 67 ወይም 65ን ቢሆን ኖሮ ትርጉም-አልባ ይሆን ነበር። በተጨማሪም መላው መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻሕፍት እንዳሉትም አስተዋልኩኝ። ይኸውላችሁ እንግዲህ በዚህ ቀላል ትንተና እግዚአብሔር ትኩረቴን እየተቆጣጠረው እንደ ሆነ፣ ደግሞም በኢሳይያስ 32 - በተለይም ከቊ. 1-3 ባሉት-ሰባኪው በጠዋቱ የራዲዮ መልእክት ሲናገርባቸው በነበረባቸው ቊጥሮች ላይ ኮስታራ ትርጉም እንዳለ ራሴን አሳመንኩ። ያን ጊዜ በዩኒቨርስቲ ውስጥ ባለው የመልክዐ-ምድር ጥናት ትምህርት ክፍል በማስተማር ላይ ለነበረው ክርስቲያን ጓደኛዬ የነበረኝን ልምምድ እስክነግረው ድረስ ብቻኮልም፣ ተሰፋን ሰኞ ዕለት አገኘሁትና ሁሉንም ነገር ነገርኩት። የእርሱ መልስ አጭር ነበር፦ "ጥበበ፣ እግዚአብሔር ለአንተ ሕይወት ኃያል ዕቅዶች እንዳለው እወቅ። በግልህ እና በመለኮታዊ መንገዶች እያነጋገረህ ነው።" እኔም በበኩሌ የተዓምራታዊ አጋጣሚውን ትርጉም እንዲፈታልኝ ብፈልግም በድጋሚ የእርሱ መልስ በጣም አጭር ሆነ፣ "ስለ ነገሩ የምርህን ሆነህ ጸልይና ራሱ መንፈስ ቅዱስ በጊዜው ይገልጥልሃል።"

ይህ ልምምድ ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ መንፈሳዊ ጉዞዬ ውስጥ በጣም






አስደናቂ ውጤት አመጣ። ይህ ክስተት በሕይወቴ ውስጥ ከድነቴ ቀጥሎ ኃይለኛው ልምምድ እንደ ሆነ አድርጌ ቈጠርኩኝ። የትኛውንም የተደበቀ ጥርጣሬ እና ስለ እግዚአብሔር ያለኝን ጥርጣሬም አስወግዶልኝ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማምነው ከልቤ ጭምር እንጂ፣ ከአእምሮዬ ብቻ እንዳይሆን አደረገ። ኋላ ላይ ለሐረሪው ጓደኛዬ ልምምዴን እንደ መንፈሳዊ መከላከያ ግንብ ወይም ታኮ አድርጌ ገለጽሁለት።

በ1981 ዓ.ም፣ በጌታ ጸጋ ለሁለተኛ ዲግሪዬ መመረቂያ ያደረግሁትን ጽሑፍ በተሳካ ሁኔታ ተፈትኜ በቂ መልስ መስጠት ቻልኩና ለምርቃት ዝግጁ ሆንኩኝ። ጌታ ኢየሱስ በዛው ጊዜ ላይ በሁለት አስደናቂ ስጦታዎች አስደነቀኝ። የእነርሱንም ዝርዝር ሐሳብ እንደሚከተለው ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ፓሪስ ላይ ለሚደረገው የኢትዮጵያ ጥናት 10ኛ ዓለም አቀፍ ጉባዔ ውድድር የጽሑፌን የመግቢያ ሐሳብ በአጭር ገለጻ ፓሪስ ላይ ለሚገመግሙት ላከሁኝ። ከመግቢያዊ አጭር የገለጻ ጽሑፉ የተነሣ በዝግጅቱ ላይ ከሚሳተፉት ዕጩዎች አንደኛው ተደርጌ ብመረጥም፣ ወረቀቱን ለመጻፍ ችላ አልኩኝና ከተስፋ መቁረጥ የተነሣ ተስፋ ሰጪ የነበረውን ውጥን-ሥራ ተውኩት። አንድ ቀን በስድስት ኪሎ ግቢ ውስጥ በእግሬ እየሄድኩኝ እያለሁ ራሴን የኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ከሆነው ሰው ጋር በመንገድ ላይ ተገጣጥሜ አገኘሁት። ሰላም ሊለኝ ያስቆመኝ ደስ የሚል ሰው ሲሆን፣ የማስረከቢያ ቀኑ በማለፉ ወረቀቴን ምን አድርጌው እንደ ሆነ ሲጠይቀኝ፣ ጥሩ ሰበቦችን እየደረደርኩ ውጥን-ሥራው ላይ ተስፋ የቆረጥኩባቸውን ምክንያቶች አስረዳሁት። ነገር ግን፣ ኮሚቴው የእኔን ውጥን-ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ ቦታ ስለ ሰጠው እንድጨርሰው በመምከር በዚያ ቦታ እና ያን ጊዜ የሦስት ቀናት ጭማሪ ጊዜ ሊሰጠኝ እንደሚፈቅድ ነገረኝ። የሰጠኝን ዕድል እንድቀበል ምን እንደ መራኝ አላውቅም፣ ነገር ግን ወረቀቱን በሦስት ቀናት ውስጥ ልጨርሰውና ቢሮው ድረስ በአካል ቀርቤ ላስረክበው ቃል ገባሁለት። አንድ ጊዜ ራሴን ሰጥቼ ቀን እና ሌሊት ስሠራው ቆየሁና እንደ መከረኝ ወረቀቴን አጠናቅቄ አስረከብኩት።

በምርቃቱ ቀን አንዳንድ ነገሮችን ለማጣራት ብዬ ወደ ምርቃት ክብረ-በዓሉ ከመሄዴ በፊት ወደ ቢሮዬ ሄጄ ነበርና ከኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት (አይኢኤስ) የሆነች ደብዳቤ በበሬ በኩል ተንሸራትታ ገብታ አገኘኋት። አንሥቼ

ሳነብበው የእኔ ወረቀት ለፓሪሱ ጉባዔ የተመረጠ መሆኑን ተገነዘብሁ። እኔ ገና ጀማሪ ምሁር እንደ ሆንኩ ደግሞም ውድድሩ በጣም ከባድ እንደ ነበር በጣም ጠንቅቄ ባውቅም፣ እግዚአብሔር በድጋሚ ጸጋውን በእኔ ላይ ሊያፈስስ ብሎ፣ ደግሞም የበለጠ ሙሉ ለሙሉ በእርሱ ላይ እንድታመንና እንድመካ ኃይሉንና ታላቅነቱን ሊያሳየኝ የተከሰተ ነገር መሆኑ ገባኝ። የፓሪሱ ጉዞዬ ለምዕራባዊያኑ ዓለም የመጀመሪያው ዕድል ሲሆን፣



ፓሪስ ከጓደኞቼ ጋር

ከሕይወቴ አንደኛው ማራኪ ክስተት አድርጌ አሁን ድረስ ትልቅ ዋጋ እሰጠዋለሁ።

ያም ብቻ አልነበረም፣ በሌላም የሚያስደንቅ ነገር ተንበሸበሸ ነበር። ታደርገዋለች ብዬ አስቤያት ያልነበረችው እናቴ በጣም የማይቻሉ ይመስሉ የነበሩትን ሁኔታዎች በማሸነፍ ከሐረር በመምጣት እንደ ምንም ብላ ለምርቃቴ ሰድስት ኪሎ ግቢ ተገኘች። ከብረ-በዓሉ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ፣ ተጠራሁና እናቴ ቆማ ወዳየሁበት ዋናው በር እንድሄድ ተጠየቅሁኝ። እርሷን እዚያ ማየቱ እንዴት ያስደስታል! ሞቅ ባለ አቀባበል ስሜያት በፍጥነት ወደ አዳራሹ አስገባኋትና እንግዶች ከሚቀመጡበት ስፍራ ቦታ ሰጠኋት። በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ዲግሪዬን ለመቀበል ስሜ ሲጠራ ትልቁን እልልታ በአዳራሹ ውስጥ ያሰማችው እርሷ ነበረች። ለእግዚአብሔር ከመስጠት በቀር ሁለቱን ተዓምራት በሰውኛ ሁኔታ ለማስረዳት ምንም ምክንያት አይኖረኝም። እግዚአብሔር በሕይወቴ የገለጻቸው እነዚህ ተዓምራት እምነቴን አጠናከሩት፣ ደግሞም እርሱን ለመታመን እና በእርሱ ብቻ ለመመካት ውሳኔዬን ጨመሩት።

ወደ ፓሪስ ስንሄድ አገርን ወክለን በከፍተኛ ደረጃ ነበር የተጓዝነው። አቀባበሉም እንዲሁ። ታዲያ በዚያው ለመሸፈት እንደ መዳዳት ብሎኝ ነበር። አብሮኝ የሄደውና ደህና ዝግጅት አድርጎ በዚያ የቀረው የድሬው ወንጌም ጠቆም አድርጎኝ ነበር። ያንን ሐሳብ እንዳላስተናግደው ያስቻለኝ አዲሱ የእምነት ጉዞዬ ነበር። ራሴን ያሳመንኩት እግዚአብሔር በጀመረው አዲስ ጉዞ





ውስጥ በግሌ ጣልቃ በመግባት መስመር መቀየስ የለብኝም በሚለው ሐሳብ ነበር።

## *መልስ ወደ አሥመራ፦ የተለወጠው ሰውዬ*

የሁለተኛ ዲግሪዬን ካጠናቀቅሁ በኋላ ለማስተማር ወደ አሥመራ ተመለስኩኝ። በዚያን ጊዜ በቅርበት ያውቁኝ ለነበሩት እና የአጋጣሚ መተዋወቅ ላለን ሰዎች ሁሉ በተሻሻለ ክፍያ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን እንደ አዲስ የተፈጥርኩኝ ያክል ሆኜ መጣሁ። ብዙም ሳልቆይ ከርስቲያን የሥራ ባልደረቦችን በዩኒቨርስቲው ውስጥ ፈለግሁኝና ኋላ ላይ በሕይወቴ ውስጥ አውራ ሚና የተጫወተውን አንደኛውን አገኘሁ። መኩዬ ብለን እንጠራው የነበረው መኮንን ጌታን የሚወድ እና አሥመራ ውስጥ ካሉት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በአንደኛው ውስጥ የታወቀ መሪ ሆኖ የሚያገለግል የሥነ-ሕይወት (ባዮሎጂ) መምህር ሲሆን፣ ሕይወቴን ለጌታ እንዴት እንደ ሰጠሁ ታሪኬን ነገርኩት፣ እርሱም እጅግ ሲበዛ ያንን በመስማቱ ተደሰተ። ረጅም ጊዜ ሳይሆነው የቀድሞውን ሕይወቴን ያውቁ የነበሩ ሰዎች አማኝ መሆኔን ሲሰሙ ሊያምኑ ሲከብዳቸው፣ ለመኩዬ ግን በጭራሽ ችግርም አልነበረም። እርሱም በጣም ወደ ወደድኩትና ጌታን ወደሚያመልክበት ቤተ ክርስቲያን ሲጋብዘኝ እኔም ጌታን የማመልክባት ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን ውሳኔ አሳለፍኩኝ፣ ደግሞም በመደበኛነት እሑድ አምልኮዎችን መታደም ጀመርኩኝ። በማኅበረ-ምእመናኑ ውስጥ ሁለቱንም ቋንቋዎች የሚወክሉ ሰዎች ስለ ነበሩበት፣ አምልኮ የሚካሄደው አንዳንድ ጊዜ በአማርኛ ሌላ ጊዜ በትግርኛ መሆኑ አስደሰተኝ። ቋንቋውን መስማት ያልቻልኩበት ገደብ ለእኔ ችግር አልነበረም። በትግርኛ የሚካሄዱትን አምልኮዎች ልክ በአማርኛ የሚካሄዱትን ያክል ተባርኬባቸዋለሁ።

ያጋጣሚ ነገር፣ ሐብቴ የሚባል አሥመራ ውስጥ አስተማሪ ሆኖ ለረጅም ጊዜ የቆየ የሐረር ጓደኛ ነበረኝ። ሐብቴ እና እኔ ወደ አዲስ አበባ ለትምህርት ከመሄዴ በፊት አሥመራ ከተማ ውስጥ ወደ ሴክቴቶ አካባቢዎች አብረን የምንሄድና የምንዝናና የቅርብ ጓደኛሞች የነበርን ሲሆን፣ ወደ አሥመራ ስመለስ የተወሰኑ ጊዜያት ያክል ወደ እርሱ ቤት ለጉብኝት ሄድኩኝና ብዙ

መለወጡን አስተዋልኩኝ። ቀደም ሲል ያደርገው እንደ ነበረው ዝምተኛና ቁጥብ ስለ ነበር፣ ከስንት ጊዜ አንዴ ወደ ቡና ቤቶች አብረን ስንሄድ ልክ እንደ እኔው አልኮል መጠጦችን ስለማይጠጣ፣ በእርሱ ሕይወት ውስጥ ምን እየሆነ እንደ ሆነ ማሰብ ጀመርኩኝ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ሕያው የሆነውን ጌታ በተለያዩ መንገዶች በማግኘት ጎዳና ሁለታችንም እንዳለፍን ደረስኩበት፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ስላለው ማስደመም አብረን ፈነደቅን። በዚያን ጊዜ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን በመደበኝነት መታደም ጀምሬ ነበርና ወደዚያው ቤተ ክርስቲያን አብሮኝ እንዲሄድ ጋበዝኩት። እርሱ ግን፣ እንደ ክርስቲያን ትርጉም የማይሰጥ ምክንያት ነግሮኝ ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ከአንዳንድ ኤርትራውያን ጓደኞቹ ጋር መራራ የሆነ ልምምድና ቅያሜ ስለ ነበረው ራሱን በዳርቻ ላይ ማቆየት እንዳለበት ስለ ተሰማው ልገፋው አልፈለግሁም። ከዚያ ይልቅ፣ በቃሉ እንድናድግ ሁለታችን በመደበኛነት መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት እንድንጀምር ጥቆማ ሰጠሁት። እንደዚያውም አደረግንና ለሁለታችንም በጣም አትራፊ ሆኖ አገኘነው።

የሆነ ጊዜ ላይ ጓደኛዬ ውሳኔውን ቀየረና ከእኔ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ እንደሚፈልግ ገልጾልኝ አንዴ ከጎበኘው በኋላ፣ ወደደው። አሥመራ ብዙ ከመቆየቱ የተነሣ ትግርኛን በጥሩ ሁኔታ በመናገሩ፣ በትግርኛ የሚካሄዱ ስብከቶችን ለመስማት ችግር አልነበረበትም። እኔም፣ ከእኔ ጋር በመደበኛ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ጓደኛ በማግኘቴ ተደሰትኩኝ።

በታሪክ ትምህርት ክፍል ውስጥ ካሉት የሥራ ባልደረቦቼ አንዳንዶቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ እንደሚፈልጉ ሲገልጹልኝ እጅግ ተደነቅሁ። መጀመሪያ ላይ፣ ከእኔ ጋር አዲስ አበባ ውስጥ ሁለተኛ ዲግሪውን ሊሠራ ሄዶ የነበረው ቤን ብቻ ነበር የጠየቀኝ። ከዚያም ከፖላንድ የፒኤች.ዲ. ዲግሪውን ይዞ የተመለሰው ተስፉ፣ ከዚያም ከቅድመ-አብዮቱ ኢትዮጵያ ጀምሮ የድሮ ጓደኛዬ የነበረውና አሁን ከቡልጋሪያ ፒኤች.ዲ. ዲግሪ ይዞ የመጣው መኮ ሲሆኑ፣ ሁላችንም በጋራ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጀመርን። በእርግጥ፣ ቤን ጌታን ያገኘውና ኋላ ላይም የተጠመቀው በዚያች ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፣ ሁለቱ ቤተ ክርስቲያን ይታደሙ የነበረው አልፎ አልፎ ነበር። በየትኛውም ደግሞ በሆን፣ ከዛው የትምህርት ክፍል የሆንነውና ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንሄደው ሦስታችን በግቢው ውስጥ ኃይለኛ ቅስቀሳ አደረግን። እኔ በዚህ ትምህርት ክፍል በጣም





በታታሪነት እሠራ ስለ ነበር፣ አዲሱ ክስተት በአካባቢው ችግር አልፈጠረብኝም። በዚህም አጋጣሚ ከሞላ ጎደል ሁሉም የሥራ ባልደረቦቼን እና ከእኔ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደውን የሐረር መልካም ወዳጄን ጨምሮ በጌታ ቤት ለመሰማራት በቅተናል። ይህ ሁሉ፣ ማብራሪያ እንኳን ልሰጥ የማልችልበት አስደናቂ ልምምድ ነበር።

ለአምልኮ ወደዚያችው ቤተ ክርስቲያን ይሄዱ የነበሩት ክርስቲያን ተማሪዎቹ የምርምር ሥራዬን በጸጥታ በምሠራበት ምሽቶች ላይ ቢሮዬ ይጎበኙኝና በጣም ደስ ብሎኝ እቀበለው ወደ ነበረው የተማሪዎች ኅብረት ይጋብዙኝ ጀመር። ምንንም እንኳን አዎንታዊ ምላሽ ባያገኙም፣ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ለሌሎቹም የሥራ ባልደረቦቼ ግብዣ ሰጥተዋቸዋል። በአንድ በኩል በአማርኛ የሚካሄደውን፣ ሁለተኛ ነገር ደግሞ ድባቡ በጣም ተስማሚ የሆነውን በተማሪዎች ኅብረት ውስጥ የሚካሄዱትን አምልኮዎች ወደድኳቸው። ተማሪዎቹ አብዛኛውን ጊዜ ራሳቸው በተራ ሆነው በፈጠራዊ መንገድ ይሰብኩ የነበረ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የተለያዩ ሰባኪዎችን ይጋብዛሉ። ከሰባኪዎቹ አንዳንዶቹ የገዛ ራሴ ተማሪዎች ስለ ነበሩ፣ የተዋጣለት በነበረው የስብከት አቀራረባቸው ከመገረም ባለፈ እንደ አስተማሪያቸው በጣም በቅርበት ከእነርሱ ጋር በመሆኔ ያለመረጋጋት ስሜት ነበረኝ። ነገር ግን በሂደት ያንን ስሜት ማሸነፍ ቻልኩኝና ከእነርሱ ጋር በደንብ ተቀላቀልኩኝ። በእርግጥ እንደ አባቡ፣ መላኩ፣ ዳምጤ እና ዳዊት ከሚባሉት ጋር ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ማዳበር ችያለሁ።

በአብዛኛው ሙያተኞች የሆኑትንና ከሁሉም እርከኖች የሆኑትን ክርስቲያን ምሩቃን በአንድነት የሚያሰባስብ የምሩቃን ኅብረት እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። ስለዚያ ኅብረት እንዴት እንደ ሰማሁ አሁን ባላስታውስም፣ እኔን ከመሰሉ ሰዎች ጋር መሆን የምችልበትና ከእነርሱ ጋር በጌታ የማድግበት በመሆኑ ለእኔ የበለጠ የሚመጥነኝ ጥሩ ቦታ ሆኖ አገኘሁት። እንደ ዶ/ር ፍጹም፣ ዛሬም ድረስ ዳኒ እያልኩ የምጠራውና ኋላ ላይ ለሠርጌ ሚዜዬ የነበረው ወንጌላዊ ዳን እና በርካታ ምርጥ ክርስቲያን ጓደኞችን ተዋወቅሁኝ። ኅብረቱ በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ ስለ ነበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች በእያንዳንዱ የመኖሪያ አካባቢዎች ተቋቁመው፣ እኔም በአንዳቸው ውስጥ ተመደብኩኝ - የዕድል ጉዳይ ምርጥ የሆነው ውስጥ ነበር የተመደብኩት። ያን ጊዜ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ የነበረው የጥናቱ መሪ ከሆነው ከዳኒ ጋር ጥሩ ጓደኝነትን

የመሠረትኩት በዚያ ጊዜ ነበር። የቡድኑ አባላት ከሆኑ እንደ ሰለሞን፣ ዘማሪው እቁባይ፣ እና በዩኒቨርስቲ ውስጥ የሥራ ባልደረባዬ የነበረችው አበባ ዓይነት በርካታ ሰዎችን በኅብረቱ ውስጥ ተዋወቅሁኝ። ከተለያየ ሁኔታዎች የመጣን ነበርን ደግሞም እያንዳንዱን ከፍለ ጊዜ ሁላችንም በአስደሳች ሁኔታ እንድንሳተፍ የሚያደርግ ጥሩ መሪ ነበረን። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ስለ ተማርኩኝ እና በእምነቴም የበለጠ ሥር ስለ ሰደድኩኝ፣ በዚያ ቡድን ውስጥ ብዙ ተባርኬያለሁ።

በዚህ ጊዜ በአሥመራ የነበረኝ ሕይወት በጣም የተደሰትኩበት ሲሆን፣ አሳማኝ በሆነ መልኩ በበርካታ መረቦች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀላቅያለሁ። በአሥመራ ያሉት ክርስቲያኖች በጣም ሐቀኞች፣ የተሰጡ እና አፍቃሪ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። በኃላፊው ጊዜ በሕይወቴ ከተከሰቱት በርካታ ነገሮች የተነሣ ስለ ኤርትራውያን ወንድሞች እና እኅቶች የነበረኝ የትኛውም የቆየና ትርፍ የሆነ የማይጨበጥ ሐሳብ ከሕይወቴ በንኖ ጠፋ። ከዚህም በተጨማሪ፣ በማስተማር እና በምርምርም በጣም ውጤታማ ሆንኩኝ። እምነቴ ከፍተኛ ጥንካሬን፣ ዓላማን፣ እና ለሙያዬም ተጨማሪ የሆነ መሰጠትን አበረከተልኝ። የጸሎት ሕይወቴ ዘለቄታ ያለው ሆነ፣ ደግሞም ከጌታ ኢየሱስ ጋር ያለኝ ግንኙነት ጠልቆ ሥር ሰደደ።

ቡና ቤቶች በመሄድ ጊዜዬንና ገንዘቤን በመበተን ባልተገራ ሕይወት መኖርን ስላቆምኩ፣ አሁን በሕይወት ውስጥ አንድ አውራ የሆነ አጀንዳ ነበረኝ - በእኔ ላይ የከበደው የማግባት ፍላጎቴ። አዲስ አበባ ውስጥ በነበርኩኝ ጊዜ አጥልቄ አስቤበት ነበርና እንደውም ሐሳቡን ከአማኑኤል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አንደኛው ከሆኑት ከጋሽ ክንደያ ጋር ተካፈልኩት። በውጥን-ሥራው ለመቀጠል ማቅማማቴን በማየት ባይገፉበትም ቅሉ፣ እንደውም በጣም የሚያውቋትን ልጃገረድ ሊያስተዋውቁኝ አስበው እንደ ነበረ ሰምቻለሁ። አዜብ ከሕይወቴ ወጥታለች፣ ሌሎች ልጃገረዶች በመንገዴ ላይ አቋርጠዋል፣ ነገር ግን በምወስዳቸው እርምጃዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ መተላለፍ ስላልፈለግሁና በክርስቶስ አዲስ ያገኘሁትን ሕይወት በየትኛውም ነገር መለወጥ ስላልፈለግሁ፣ በዚህ ጊዜ ጠንቃቃ መሆን ነበረብኝ። ክርስቲያናዊ ጋብቻ መከናወን ያለበት ተመሳሳይ አስተሳሰብ ባላቸው አማኞች መካከል መሆን እንዳለበት አውቄያለሁ ደግሞም አድንቄዋለሁ። ስለዚህም፣ የምሬን





እጸልይበት ጀመር፣ ደግሞም አንድ ወቅት ላይ ነገሩን አሥመራ ዩኒቨርስቲ አብሮኝ ለሚሠራው መኩዬ አሳወቅሁት።

## የጋብቻ ሕይወት

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ አዜብ የምትባል ሌላ ወጣት ልጃገረድ ተዋወቅሁኝ። ይህችኛዋን አዜብ የተዋወቅሁበት መንገድ የሚስብ ታሪክ አለው። አስቀድሜ፣ የአጎቴን ልጅ ጌቱን የሚያውቁ ሆነው የተገኙና ከአዲስ አበባ የመጡ አሰፋ እና ካሱ የሚባሉ ጓደኞችን ተዋወቅሁኝ። አልፎ አልፎ የሚኖሩበት አፓርታማ እየሄድኩኝ በመጎብኘት ሌሊቱን አብሬያቸው አሳልፋለሁ። አሰፋ እና ካሱ አንዱን የአፓርታማ መኖሪያ ለሁለት ተጋግዘው በሚከፍሉበት ሁኔታ በጋራ ይኖሩበት ነበር። ሁለቱም ከአሥመራ የሆኑ የሴት ጓደኞች የነበሯቸው ሲሆኑ፣ እኔም ጓደኞቻቸውን ጥሩ ጓደኞቼ ላደርጋቸው ቻልኩ። አንድ ቀን ወደ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እየሄድኩ ሳለሁ፣ የካሱ ጓደኛ የሆነችውን ሣራን አገኘኋት። እርሷም ከቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ ባለው አጎራባች ቤት ውስጥ ከምትኖረው ከአዜብ ጋር አስተዋወቀችኝ።

እንዲህ እንዲህ እያለ፣ አንደኛው ነገር ወደ ሌላኛው ነገር የሚመራ ሆነ። ቀደም ብሎ አይቼያትም ባላውቅም፣ አዜብ እኔ በመደበኛነት በምታደምበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል ነበረች። ስለ ጋብቻዬ የምሬን እጸልይ በነበረበት ወቅት ላይ ከእርሷ ጋር ያለኝ ትውውቅ ተከሰተ። ስለ ትዳሬ ደግሞ አራት ነገሮችን እንዲያደርግልኝ እግዚአብሔርን ጠይቄዋለሁ።

1. በጸሎት ከጌታ ጋር ያለኝን እምነት የምታጠናክር ክርስቲያን፣ በእኔ ምርጫ ሳይሆን በእርሱ ምርጫ የሆነችውን ሚስት እንዲሰጠኝ እግዚአብሔርን ጠየቅሁት።
2. ሐቀኝነት የሌለውን ሁሉ ስለምጠላ፣ ሐቅ ከሌላቸው ሰዎች ጋር መኖር ስለማልችል፣ ሐቀኛ የሆነችን ሚስት እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት።
3. ከቀድሞዋ የሴት ጓደኛዬ ጋር ሰላማዊ በሆነ መልኩ ግንኙነቴ እንዲቋረጥ እግዚአብሔርን ጠየቅሁት።
4. የጋብቻ ቀኔ ከ1982 ዓ.ም በኋላ እንዲሆን እግዚአብሔርን ጠየቅሁት።

ከአዜብ ጋር ከተዋወቅሁኝ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፣ በምኖርበት የናኩራ ግቢ ከታናሽ እኅቷ ተናኜ ጋር አየኋት። ወደ መኖሪያ አፓርታማዬ እንዲመጡ ስጋብዛቸው፣ ግብዣዬን ተቀበሉትና ለትንሽ ጊዜ ተቀምጠው ከተወያየን በኋላ ሄዱ። መቼ እንደ ሆነ በማላስታውሰው አንድ ቀን፣ ገና በማለዳ አዜብ በሬን አንኳኳች፣ እኔም ስላየኋት ተደንቄ በዚያ ማለዳ ምን ሊያመጣት እንደሚችል እና ለመምጣትም ድፍረቱን ከየት እንዳገኘችው ራሴን ጠየቅሁኝ። ላጤ እንደ ሆንኩኝ ታውቃለች፣ ደግሞም በወንደ-ላጤ ወደ ተያዘ መኖሪያ ቤት በዚያ ማለዳ መምጣቱ በዚያ ባህል ውስጥ በጣም ያልተለመደ ነገር መሆኑ ይታወቃል። በኤርትራ ያሉ ልጃገረዶች ለባህላቸው በጣም ጠንቃቆች ስለ ሆኑ ለቀላል ጉብኝት እንኳን የሚመጡት ነጠላ ደረብ አድርገው ነበር። በዚያ ማለዳ እከፍሌ መገኘቷ ያስደመመኝ ለዚያ ነበር።

በደንብ ከማላስታውሰው የዮሐንስ መልእክት አንድ ጥቅስ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ጠቀሰችልኝ። በሆነ መልኩ በዚያ ፍቅር ስለ ተነካች በዚህ ማለዳ መተኛት እንዳልቻለች እና አንድ ነገር እያስቸገራት እንደ ሆነ ደግሞም ያንን ስሜት ማብራራት እንዳልቻለች እና የመጣችውም የገጠማትን ነገር ልታካፍለኝ እንደ ሆነ ነገረችኝ። ካለን ውሱን ትውውቅ አኳያ ይህ ያልተለመደ ነገር በመሆኑ ሁኔታውን እንዴት መያዝ እንዳለብኝ፣ ምን ማለት ወይም ምን አለማለት እንዳለብኝ ባላውቅም፣ ምናልባት ከመኩዬ ጋር ላደረግነው ጸሎት የጸሎቱ መልስ ምልክት እንደ ሆነ አድርጌ ተቀበልኩት። ያንን ከእኔ ጋር ከተካፈለች በኋላ ወዲያውኑ ሄደች። ምንም እንኳን ትክክለኛውን ምላሼን ባላስታውስም፣ ይሄ ነገር የምሯን ልትጸልይበት የሚገባ ጉዳይ እንደ ሆነ ለእርሷ መንገሬን አስታውሳለሁ።

በዚህ አጋጣሚ ተደንቄ የነበረው እንግዳ ነገር በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ከሳምንት በፊት በጋብቻ ጉዳይ ላይ ከመኩዬ ጋር ኮስታራ የሆነ የጾምና ጸሎት ጊዜ ካሳለፍን በኋላ የተከሰተ መሆኑ ነበር። እርሱ ጸሎታችንን ለመዝጋት ወደ ክፍሌ መጥቶ በጣም በተቀጣጠለ ሁኔታ ከጸለየ በኋላ፣ ከእርሱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአንደኛዋ ጋር ትውውቅ እንዳደረግሁኝ በመጠኑ ነገርኩት። ከዚህም ሌላ፣ የሥራ ባልደረባዬ የሆነችና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ውስጥ ከምትገኝ አንዲት ልጃገረድ ጋር እየቀጠለ ያለ ጓደኝነታዊ ግንኙነትም እንዳለ ነገርኩት። በጸሎቱ ውስጥ በግልጽ በማስታውሰው መልኩ፣ 'አባክህ





እግዚአብሔር አንተ ለጥበበ ያሰብክለትን ሚስት ገፍትረህም ቢሆን አምጣት፤' በማለት ተናገረ። የአዜብን በዚያ ማለዳ ወደ ክፍሌ መምጣት የምመለከተው በዚያ የጸሎት ብርሃን ነው። እናንተ ይህንን እምነት ወይም ገራገርነት ልትሉት ትችላላችሁ፤ እኔ ግን በሙሉ ልብ ሆኜ ከአዜብ ጋር ጓደኝነቴን ማጠናከር እንዳለብኝ ወሰንኩኝ።

ከዚህ ክስተት በኋላ ብዙም ሳይርቅ፣ ለኮስታራ ውይይት አዜብን ወደ አፓርታማዬ ስጋብዛት ዝግጁ በሆነችበት መልኩ ግብዣዬን ተቀበለችውና ወደ መኖሪያዬ መጣች። በምቾት ወደ ተቀመጥንበት የአራተኛ ፎቅ በረንዳ ወሰድኳትና ከእርሷ ጋር የምር የሆነና የሚዘልቅ ግንኙነትን ለማዳበር መፈለጌን ነገርኳት። ሁለታችንም ስለ ነገሩ እንድንጸልይበትና እግዚአብሔር ከመራን ብቻ እርምጃ እንድንወስድ ነገርኳት። ለወራት ያክል መደበኛ የሆነ የጸሎትና የጾም ጊዜ ማድረግ ጀመርን። ይህንንም ስናደርግ በባለፉት ዘመናት ከነበረኝ ዝንባሌዎች አንጻር በቀላሉ ሊሆን ስለሚችል እግዚአብሔርን ለማክበርና የትኛውንም ተገቢ የማይሆንን ባሕርይ ለማስወገድ ሁልጊዜ እስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት በማድረግ ነበር።

በግንኙነታችን ውስጥ ሁለታችንም ሰላምንና ምቾትን በማግኘታችን እንድታገባኝ ስጠይቃት ሳታቅማማ ተቀበለችኝ። ከዚያ በኋላ፣ በጥልቀት ደረጃ እርስ በርስ ለመተዋወቅ በቂ ጊዜ ስላልነበረን፣ ምንም ዓይነት የጆርባ ጥናት ምርመራ ሳናደርግ፣ እንዲሁም ሁለታችንም በእግዚአብሔር እና በጸሎታችን ላይ በእጅጉ ተደግፈን የዕጮኛዎቼን ሁኔታ ጨምሮ፣ ስላለፉት ዘመናትና ስለ አሁን ሁኔታዬ ማወቅ የሚገባትን ሁሉ ነገርኳት። ብዙውን ጊዜ እርሷ ዝምተኛ ስለ ነበረች፣ ደግሞም ስለ ራሷ ብዙም ስለማታወራ፣ ከእርሷ ወገን የመጣው በጣም ጥቂት መረጃ ሆነ። ይሁን እንጂ፣ እኔ ራሴን ለእርሷ ግልጽ እስካደረግሁ ድረስ በቂ ነው ብዬ አመንኩ።

የክረምት እረፍት ጊዜ መጣና ሐረር የነበረችውን እናቴን ለማየት አሥመራን ለቅቄ እወጣ ዘንድ መዘገጃጀት ጀመርኩ። እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ጉባዔ ቡዳፔስት፣ ሐንጋሪ ወረቀት ለማቅረብ ዝግጅት ባደርግም፣ የጉዞ ወጪውን ለመሸፈን አስተዳደሩ ውሳኔውን አዘገየው። ሐረር ውስጥ ለሚኖረኝ ረጅም እረፍት አሥመራን ለቅቄ እንደ ወጣሁ፣ በጣም በሚያስደንቅ መልኩ የእኔን ፈጣን ትኩረትና ምላሽ የሚሰበው ጥሪ ሐረር በደረስኩበት በዚያው ቀን

ላይ ደረሰኝ። በዚያው ቀን ድሬዳዋ ተመለስኩኝና በሚቀጥለው ቀን ወደ አሥመራ ለመብረር ወደ አዲስ አበባ አውሮፕላን ያዝኩኝ። አሥመራ እንደ ደረስኩኝ፣ ሐንጋሪ ውስጥ ስላለው ጉባዔ እና የጉዞዬን ወጪ ስለሚሸፈንበት ዘግይቶ ስለ ነበረው የገንዘብ ጥሪት ለማነጋገር ወደ ዩኒቨርስቲው ፕሬዘዳንት ቢሮ ተጣደፍኩ። ፕሬዘዳንቱ፣ "ዩኒቨርስቲው ሙሉ ወጪህን ሊሸፍን ፈቃደኛ የሚሆንበት እንደ አሜሪካ ባሉ ሌሎች ዓለማት መሳተፍ ስትችል ሐንጋሪን ለምን መረጥክ?" ሲል አስደነቀኝ። ፕሬዘዳንቱ ለምን ይሄንን እንደ ጠየቀኝ ምንም ፍንጭ የለኝም፣ ነገር ግን እኔ ወደዚያች ምድር እንድጋበዝ ምንም ነገር ያደርግ ዘንድ ልገፋፋው አልፈለግሁም። በእርሱ አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ ያላመንኩበት ብሆንም፣ ሐሳቡን ግን ቦታ ሰጥቼው በተለየሁት ጊዜ ከአሥመራ ሐረር ለተመላለስኩባቸው ጉዞዎች ወጪውን ማን እንደሚሸፍን ጠየቅሁት። ዩኒቨርስቲው ያንን ሙሉ ለሙሉ እንደሚሸፍን ካረጋገጠልኝ በኋላ ሰነዱ ተዘጋ፤ እኔም ወደ ሐረር ተመለስኩኝ።

ፕሬዘዳንቱን እንደ ተለየሁት፣ በአሥመራ የነበረችኝን ያችን አንድ ሌሊት ወደ ጥሌ ቤት ሄድኩኝና፣ "ይሄ ሁሉ ውስብስብ ነገር ምንድን ነው?" እያልኩኝ እግዚአብሔርን በመጠየቅ መጸለይ ጀመርኩኝ። እየጸለይኩኝ እያለ ለጥያቄዬ መልስ እንዲሆን መልእክቱ ግልጽ ወዳልሆነልኝ ወደ ኢሳይያስ 32 ጌታ መራኝና በጥልቅ አእምሮዬ ውስጥ አንዳች ነገር ሰከነ። ምንም ነገር ቢሆን ለምክንያት ነው የሚሆነው ብዬ ከደመደምኩ በኋላ፣ ምንም እንኳን በዚያ እንደምገኝ ባትጠብቅም፣ አዜብን ላገኛት እንደሚገባኝ ሐሳብ መጣልኝ። ደወልኩላትና ለከሰዓት በኋላ ቀጠሮ ይዘን በናኩራ ግቢ ውስጥ በበረንዳው ላይ ወደ ማምሻው ላይ ተገናኘን። ወደ ብርሃን መጥቶ የነበረውን ነገር ሁሉ በምነግራት ጊዜ ባልተጠበቀ መልኩ ወደ አሥመራ እንድመጣ ያደረገኝ ላስረዳው ከምችለው በላይ የሆነ አንዳች ምክንያት ሊኖር እንደሚችል ገለጽኩላት። በጥሌ ቤት እጸልይ በነበረ ጊዜ ያኔ ወደ አሥመራ መምጣቴ ከአዜብ ጋር የሚያያይዘው ነገር እንደሚኖር በመጠኑ ተሰምቶኝ ነበር። ጌታ በኢሳይያስ 32 ሲያበረታታኝ፣ ግራ የሚያጋቡ ለሚመስሉት ክስተቶች መዝጊያ ማኖር እንደሚያስፈልግ ተሰምቶኛል። እርሷም እንዲሁ ወደ ካናዳ ለመሄድ ዐቅዳው የነበረው ነገር ከአንዳንድ መሰናክሎች የተነሣ እንዴት እንደ ከሸፈባት ነገሩን እያይዛ ከነገረችኝ በኋላ፣ ለሠርጋችን የሚሆን ቀን መቁረጥ እንደምፈልግ ነገርኳት። እኔም ወደ





ሐንጋሪ ላደርገው የነበረው ጉዞ ከሸፈ። ስለዚህ፣ ጋብቻችን በጥር ወር ሊከናወን እንደሚችልና ዝርዝሩን ለኋለኛ ጊዜ መተው እንደምንችል ተነጋገርን። በአካባቢው ባህል መሠረት ልክ ከእረፍት እንደ ተመለስኩኝ መስከረም ላይ ሽማግሌ እንደምልክ ነግሬያት ተስማማንና ተለያየን። በሚቀጥለው ቀን አብዛኛውን እረፍቴን ከእናቴ እና ጓደኞቼ ጋር ወዳሳለፍኩበት ሐረር ተመልሼ በረርኩኝ።

ከክረምቱ እረፍት መጠናቀቅ በኋላ፣ ወደ አሥመራ ተመልሼ ማስተማር ጀመርኩኝ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ፣ ለአዜብ ቃል እንደ ገባሁት፣ ሚስት አድርገው እርሷን እንዲሰጡኝ በይፋ ፈቃድ ይጠይቁ ዘንድ ወደ አዜብ ቤተሰቦች ዘንድ የሚሄዱትን ሽማግሌዎች መረጥኩኝ። እንደ ሽማግሌ እኔን የወከሉት የዩኒቨርስቲው ምክትል ፕሬዘዳንት አቶ ኪዳኔ፣ የማሪታይም ባለ ሥልጣን ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ መኮንን፣ እና የሥራ ባልደረባዬ መኩዬ ነበሩ። ወላጆቿ ፈቃዳቸውን ሰጡ። ስለዚህም በእርሷ ማረጋገጫ ጥር ላይ ለሚሆነው ሠርጌ ማቀድ ጀመርኩኝ።

ከአፈጻጸም አንጻር በዚህ ዓይነቱ ከሁለት የጎሣ ቡድን የሆኑ ሰዎች የጋብቻ ቅንጅት ውስጥ ምንም ችግር ሊኖር አይገባም። ነገር ግን፣ ኤርትራ ውስጥ የነበረው የመልክዓ-ምድራዊ ፖለቲካዊ ድባብ በተወሰነ መልኩ ከሌላው የኢትዮጵያ ክልል ይልቅ በኤርትራውያን እና በሌሎች መካከል የሚደረገው ጋብቻ ከባድ እንዲሆን አድርጎት ነበር። በትውፊት፣ ኤርትራውያን በራሳቸው መካከል እንኳን፣ በወንድ እና ሴት ልጆቻቸው መካከል ለሚደረግ ጋብቻ ፈቃድ ለመስጠት አስቀድመው የጀርባ ማንነት ማጣራቶችን ያደርጋሉ። ኋላ ላይ ስሰማ የአዜብ አባት፣ አቶ ተሰማ ስለ ሁኔታው መረጃ ሲደርሳቸው የመጀመሪያው ጥያቄያቸው "የየት አገር ሰው ነው?" የሚለው ሆነ። ከሐረር እንደ ሆንኩኝ ሲሰሙ አረንጓዴውን መብራት በመስጠት አዎንታዊ ይሁንታቸውን እንደ ሰጡ እና "ከሐረሪ ሰዎች ጋር ጸብም የለኝ" ብለው እንደ ነበር ኋላ ላይ ተነገረኝ። ወልዲያ ውስጥ የሚነግዱ ሰው እንደ መሆናቸው፣ በማኅበራዊነታቸው እና ወዳጃዊ አመለካከታቸው የተነሣ ካስደመሟቸው በርካታ የሐረሪ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ ታድለዋል። የእርሷ ታላቅ እኅት ከዩኒቨርስቲው ዲግሪ አግኝታ ነበርና ስለ እኔ አንዳች ነገር እንደምታውቅ በመናገሯ አዜብን እንዳገባት ለመፈቀዱ የረዳ ይመስለኛል። እኅቷ የዩኒቨርስቲ ሠራተኛ እንድታገባ መፍቀዱ ችግር እንደሌለው አልጋነሽ በደንብ ያየች ይመስላል።

አዜብ እና እኔ ያደረግነው የሚቀጥለው ነገር ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ለመጋባት ማሰባችንን ማሳወቅ ነበር። አንድ ቀን ከሽማግሌዎች ቦርድ ጋር ስብሰባ ተቀምጠን በጋራም ሆነ በተናጠል በርካታ ጥያቄዎችን ተጠየቅን። ሽማግሌዎቹ ይህ የበዘፈቀደ ስሜታዊ ውሳኔ እንዳልሆነ እርግጠኞች መሆን ፈልገው ስለ ነበር ጥያቄዎቻቸውን በምንችለው ሁሉ መለስንላቸው። በደንብ የማስታውሰው ወሳኝ ሆኖ ከሽማግሌዎች የተነሣ አንድ ጥያቄ ይህ ትዳር ከእግዚአብሔር ለመሆኑ እንደ ማስረጃ የምንሰጠውን አንዳች ዓይነት ነገር ካለ የተጠየቅንበት ነበር። በግሌ፣ ሰዎች ባል እና ሚስት እንዲሆኑ በሕልሞች፣ በራእዮች እና በሌሎች ጠቃሚ መገለጦች



የእኔና የአዜብ ሰርግ በ1982 ዓ.ም

እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመራቸው ሰምቼያለሁ። ለእኔ ልገልጸው የምችለው ብቸኛው ማስረጃ አዜብ እና እኔ አንድ ላይ ስንሆን በመካከላችን ያለውን ሰላም እና የስሜት መገፋፋቶች አለመኖራቸው ነበር። ሽማግሌዎቹም ውሳኔያችንን በማክበር በጸሎቶችና ባርኮቶች አሰናበቱን።

አዜብና እኔ መደበኛ የጾምና ጸሎት ጊዜን ስለ ጋብቻችንና ለዝግጅት ስለሚያስፈልገን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን፣ ስለ የወደፊት የትዳር ጊዜያችን እና መሰል ነገሮች በተከታታይ ጸለይን። ትውውቃችን አጭር በመሆኑ፣ ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ለመሸጋገር እንዲሁም ረጅም የመጠናናት ጊዜ ስላልነበረን፣ እርስ በርስ ለመተዋወቅም ጊዜ ወሰድን። በጸሎት እና በመማከር የጋብቻው ቀን ጥር 5 ቀን 1982 ዓ.ም እንዲሆን ስንወስን፣ ለጋብቻ ቀን ሚዜ በመሆን ከእኛ በቅርበት የሚሆኑትን ጓደኞቻችንንም በጥንቃቄ መምረጥ ጀመርን። ኋላ ላይ፣ ሚዜዎቼ የሆኑትን ሁለቱንም ጓደኞቼን አቤን እና ዳኒን አስተዋወቅኋት።

ወንጌላዊው ዳኒ በጋራ በመሆን የበለጠ ጊዜ እንድንወስድ መከረን። በሰዎች ፊት የበለጠ ዘና የምንልበት ውይይት እንዲኖረን ወደ ኒያላ ሆቴል ለቡና





ወሰደን። ከናኩራ ግቢ ውጭ በሰዎች ፊት የታየንበት የመጀመሪያው ጊዜ ያ ሆነ። ምናልባት ከእድሜዋ ወይም ባላቅኋቸው ምክንያቶች አዜብ ዓይናፋር ልጃገረድ ሆና በመዋሏ ዳኒ እና እኔ ከእርሷ ጋር ቀላል የሆነውን ጭውውት ለማድረግ ዝምታውን መስበር አንዳንድ ጊዜ ከባድ ሆኖ አናገኘው ነበር። በልቧ ንጹሕ እና ምንም የማታውቅ ከምትመስለው አዜብ ጨዋታ ውስጥ አማኝ የሆነችው ከሁለት ዓመታት በፊት እንደ ሆነ እና አሥመራ ውስጥ አብራት ትኖር የነበረችው ታላቅ እኅቷ፣ አልጋ 'መጤ' ወደ ሆነ እምነት መቀየሯን ባለመቀበሏ ያለፈችበት ስደት እንደ ነበረ ላውቅ ቻልኩ።

ዳኒ እና እኔ ከጋብቻዬ ጋር በተያያዙ ላሉት ነገሮች መጸለይ እና በጥንቃቄ ማሰብ ጀመርን። በተፈጥሮ የሐረሬ ሰው እንደ መሆኔ በደቂቃዎች ዝርዝር ለማቀድ ፈጽሞ ያልተደራጀሁ መሆን ይቀናኛል። ለዚህ ሁኔታዬ እንደምትክ የሚሆነው እግዚአብሔር የሰጠኝ ወንድሜ ዳኒ ግን በሁሉ ነገር ሠራተኛው አእምሮ የመሆን ያክል ሁሉን ሠርቶ አጠናቀቀና ጋብቻው የሚፈጸምበት ቤተ ክርስቲያን ተመረጠ። ምሳ እና እራት የሚስተናገድባቸው ቦታዎችንም ለይተን ካወጣን በኋላ፣ ለቀሩት ዝርዝሮች ሁሉ ኃላፊነቱ በዳኒ ላይ ተጣለበት።

ለጋብቻ ዝግጅቱ ያስፈልጉ የነበሩትን የገንዘብ ጥሪቶች ሁሉ በማዘጋጀት ጌታ ኃይሉን ገለጸልኝ። ለሠርጌ ስለምለብሰው ልብስ ወይም ስለ ሌሎች ከዚያ ጋር ስለ ተያያዙት ውጪያዊ ነገሮች ቁብም አልነበረኝ። ይልቅ፣ እንግዶች በጥሩ ሁኔታ እንዲስተናገዱና በሚቻለው መንገድ ሁሉ እንዲዝናኑ ማድረግ በመፈለጌ ከእንግዶች ጥሩ ምላሽ የሚገኝበት መልካም የሠርግ ቀን እንዲኖር የበለጠ ስጨነቅ ሰነበትሁ። አብዛኞቹን የዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ ጋብዤ ስለ ነበር፣ ሰዎች የክርስቶስን መልእክት እንዲሰሙ አጋጣሚው እንደ መድረክ እንዲያገለግል ፈልጌያለሁ። ስለዚህም፣ በመላው ዝግጅት ውስጥ የመልካምና ሁሉን ቻዩ ጌታ ክብር እንዲገለጥ ከጓደኞቼ ጋር በቁምነገር እየጸለይን ቆየን።

በዚያው ዓመት ከአቶ አማኑኤል ጋር የጥናትና ምርምር ባልደረባ ሆኜ እንድሠራ ወደ አሥመራ ዩኒቨርስቲ የአፍሪካ ጥናት ማዕከል ተዘዋወርኩኝ። አዲሱን የሥራ መስክ እያቅማማሁ ብቀበልም፣ ለመልካም እንደ ነበረ ኋላ ላይ አወቅሁኝ። ከድንገተኛ የሠራተኛ መታመም ጋር በተያያዘ በፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት ክፍል ውስጥ በርካታ ኮርሶችን እንደ ተጋባዥ በመሆን ማስተማር ነበረብኝ። በፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት ክፍል ውስጥ የአስተማሪዎች እጥረት

ኮርሶች እንዲሰረዙ እና የታሪክ ክፍለ-ትምህርቶችም ድጋሚ እንዲወጡ አደረገ። የፋኩልቲ አባላት ከሚያስተምሩት ይልቅ ለተማሪዎች እንዲያስተምሩ የሚሰጧቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርቶች ላይ በርካታ የዳሰሳ ኮርሶች ነበሩ። ያ ሁኔታ ከሚከፈለኝ መደበኛ ደመወዝ በተጨማሪ በትርፍ ጊዜዬ እንዳስተምር ዕድልን ፈጠረልኝና ከትርፍ ጊዜ የማስተማር ሥራዬ በቀጥታ ለሠርግ ዝግጅቴ የሚሆን በርካታ ገንዘብ አገኘሁ። በአሥመራ ዩኒቨርስቲ ያሉት ጓደኞቼ በቸርነት ለሠርግ ወጪዬ መዋጮ አደረጉና በጥቂት ወራት ውስጥ ጌታ፣ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ፣ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሁሉ አሟላልኝ። እንደ ዘርዖም ያሉ ሁኔታዬን የሚያውቁ ሰዎች መስከረም ላይ የምጀምርበት አንዳችም ነገር እንዳልነበረኝ ያውቁ ስለ ነበረ በሚጨነቁልኝ ጊዜ ሁሉ ጌታ እንደሚያዘጋጅ ደጋግሜ ነግሬያቸው ነበር። ከፍተኛው ውዳሴዬ የሚገባው ጌታ ለእኔ ስላዘጋጀልኝ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ የሚያዘጋጅ መሆኑን ጓደኞቼም ስላዩት በጣም አመስግነዋለሁ። በዚህ አጋጣሚ፣ ሠርጌን የማይረሳ ላደረጉልኝ ጓደኞቼ፣ በተለይም ለዩኒቨርስቲ ባልደረቦቼ በጣም አመሰግናለሁ።

ሠርጉ በሁሉም መስፈርት ግሩም ሆኖ በተዋጣለት ሁኔታ የተካሄደው በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሆን፣ ለተሰበሰበው ታዳሚ መልእክት ያቀረበው ሰው ደግሞ መጋቢ እቁባይ ነበር። መልእክቱ በዮሐንስ 2፡1-12 ላይ ያተኮረ፣ ኢየሱስ ገሊላ ውስጥ የመጀመሪያ ተዓምራቱ የነበረውን ውኃውን እንዴት ወደ ወይን ጠጅነት እንደ ቀየረ የሚተርክ፣ እና የመልእክቱ ተዛምዶም፣ ኢየሱስ መራራውን የሕይወት ሁኔታችንን ወደ አንዳች የሚጣፍጥ ሕይወት በመቀየር እንዲሁ ያደርግልናል የሚል ነበር። በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ መልካሙን የምስራች እየሰሙ ለነበሩት ሰዎች ኃይለኛ መልእክት የነበረ ሲሆን፣ ከዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ በጉባዔው ውስጥ ታድመው የነበሩ በርካታ እንዲህ ያሉ ሰዎች እንደ ነበሩ አስታውሳለሁ። የአምልኮው አገልግሎት፣ የመዘምራን አገልግሎት እና የማኅበረ-ምእመናኑ ዝማሬ ሁሉም እኩል በሆነ መልኩ ኃይለኛ እና የሚያንቀሳቅሱ እንደ ነበሩ ሠርጉ ተጠናቀቀ። መዘምራን ቡድኑ *'ሰንቱን ፈፋ አሳልፎ፣ በሰልፍ ተሰልፎ፣ እዚህ አደርሶናል፣ እላለሁ ምስጋና'* የሚለው መዝሙር በተለይ እኔ እንዴት ተነክቼ እንደ ነበረ መቼም አልረሳውም።

ቀኑን ለእኔ በጣም የተለየ ያደረገው ነገር ከእንቴ፣ ከጌቱ፣ ጋር ከሐረር እዚያ





ድረስ የመጣችው፣ በባሕርይ እና በሕይወት ፍልስፍና በከፋም በደጉ ያልተለየችኝ እናቴ መገኘቷ ነበር። ሐረር ውስጥ ከልጅነቴ ጀምሮ ጓደኛዬ የነበረውና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበርን ጊዜ ሥነ-ጽሑፎችን በማንበብ እፎካከረው ስለ ነበረ በሕይወቴ ላይ ቀላል የማይባል በጎ ተጽዕኖ የነበረው ቴድ ከሐረር መጥቶ በመገኘቱ በተናጠል ተባርኬ ዋልኩ። እርሱ የሞቱትንም ሆነ በሕይወት ያሉትን የዚያን ዘመን ትውልድ በመወከል በሠርጌ ላይ ተገኝልኝ። ምንም እንኳን የእርሱ እልፎ አልፎ የነበረው ጥያቄያዊ ፈገግታ በእኔ በኩል መጠነኛ የሆነ ምቾት ማጣትን የፈጠረ ቢሆንም፣ የእርሱ መገኘት ለእኔ ብዙ ነገር ማለት ሆነልኝ። ቴድ ለእንዲህ ያለ ረጅም ጊዜ የቅርብ ጓደኛዬ ስለ ነበረ፣ እኔን የበለጠ ያውቀኝ የነበረው በኃላፊው ጊዜ ማንነቴ በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ በአዲስ የጼንጤ ወግን በተላበሰ የጋብቻ ሁኔታ ውስጥ እኔን ሲያየኝ አዲስ ጉዳይ ስለ ነበር ትንሽ ግር እንዳለው ይሰማኝ ነበር። ምን ያክል ከባህሉ ውጪ እና ትዕግሥት-አልባ እንደ ነበርኩኝ ያውቅ ነበርና ከእርሱ እይታ አንጻር ለእንዲህ ዓይነቱ ትዕግሥትና ዲሲፕሊን ለሞላበት የሠርግ ሥነ-ሥርዓት መገዛት መቻሌ ሳያስገርመው አልቀረም።[46]

በተለይም የማርክሲስት መንግሥት ፓርቲ አባላትና መኮንኖች በዋናነት ይጠቀሙበት የነበረውን አዳራሽ ጌታ እንዴት አድርጎ እንድንጠቀምበት ዕድል በመስጠት እንደ ከፈተው ሳስብ እደነቃለሁ። አዳራሹ ይገኝ የነበረው በከተማዋ የንግድ ማዕከል አጎራባች እና በወታደራዊው ዋና መሥሪያ ቤት መስቀለኛ መንገድ ላይ ሲሆን፣ ሠርጋችንን ያከበርንበት እና በዚያ ስልታዊ ስፍራ ጌታን በነፃነት ያመለክንበት አስደናቂ ጊዜ ነበረን። በዚያ ቦታ የዘመርናቸውን መዝሙሮች በግልጽ አስታውሳለሁ፤ ከሁሉ በላይ፡ *"ደስ ደስ ይለኛል እግዚአብሔርን ስጠራ (2)፣ በምስጋና ሆኜ ከልቤ፣ ፍቅሩን ምሕረቱን አስቤ"* የሚለው መዝሙር። በብዙ አጃቢዎች ተከብበን ከአዳራሹ ስንወጣ፣ የወንጌል መዝሙሮችን መዘመራችንን ቀጠልን፣ ይህም ደግሞ በመንገድ ዳር ቆመው የሚመለከቱት እስኪደነቁ ድረስ በድፍረት ተከናወነ። እንዲህ ያለ የክርስትና እምነት ያላቸው ሰዎች የሚያደርጉት ሕዝባዊ መታየት በእነዚያ ዘመናት መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ጠላት ሆኖ እያለ ጌታ በገዛ ራሱ መለኮታዊ ፈቃድ እና ኃይል እንዲከናወን ካልፈቀደ በቀር ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነበር። ከዘመቻ ቀናት ጀምሮ የድሮ ጓደኛዬ የነበረውንና በአንዳች ዓይነት የቢሮ ሥራ ገዢውን ፓርቲ እያገለገለ የነበረውን ጥሌን በሠርጌ ላይ እንዲገኝ ጋብዤው ሳለ፣ የፓርቲ

አባላት ከሚገቧቸው መሐላዎች አንዳንዶቹን የሚጥስ ስለ መሰለው ብቻ ግብዣዬን ለመቀበል በማቅማማት ሳይገኝ ቀረ። ያ የሕይወት ምጸታዊ አሠራር ነበር።[47] እርሱ ግን ያልተረዳው አዳራሹን ለሠርጌ እንድጠቀምበት ፈቃዱንም ዕድሉንም ያገኘሁት ማታ ማታ በማስተምራቸው የፓርቲው አባል በሆኑት ተማሪዎቼ በኩል መሆኑን ነበር።

በአዳራሹ ውስጥ እራት ግብዣ የማድረጉን ሐሳብ ሳነሣ፣ አንዳንዶቹ ተደነቁ፤ መኩዬ ደግሞ ባሰብኩት ነገር አፉን ገጥሞ ሳቀብኝ። ሙቼም ይሆናል ብሎ ባይጠብቅም፣ ከምሽት የማታ ትምህርት ጋር በተያያዘ ያሉ ሁኔታዎችን በመጠቀም እግዚአብሔር በሩን ከፈተው። የፓርቲ መኮንኖች የነበሩና በጥሩ ሁኔታ ያውቁኝ የነበሩ፣ ደግሞም ስለ ክርስቲያን እምነቴ ምንም ጥርጥር የሌላቸው የማታ ተማሪዎች ነበሩኝ። የተሰጠሁ፣ ታታሪ አስተማሪ እና የዕድል ነገር ሆኖ በጣም ሥራዬን የምወድና የማከብር እንደ ሆንኩኝም ጨምረው ያውቃሉ። ታሪክን አስተምር የነበረው የተለያዩ አተያዮችን ወደ ክፍል በማምጣት በተቻለኝ መጠን ገሃዳዊ ሊድርጌ ነበር። የማታ ተማሪዎቼን በሕይወት ውስጥ የበለጠገ ተሞክሮዎች ያሏቸው እንደ መሆናቸው አከብራቸዋለሁ፣ ደግሞም ከእኔ ጋር ውይይት እንዲያደርጉ እፈቅድላቸዋለሁ፣ የመንግሥት ሠራተኞች እንዲለብሱት መንግሥት ያስገድደው የነበረውን በሰሜን ኮሪያ ዘዬ የተሰፋውን ካኪ ልብስም ለብሼ አላውቅም። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ራሴን ከመንግሥት እርቄ እንደ ነበረ ግልጽ ምልክቶች ይሁኑ እንጂ፣ በክፍሌ ውስጥ ያሉት የፓርቲ መኮንኖች ለእኔ መጥፎ ስሜት ኖሯቸው አያውቅም። ጌታ በእነርሱ ፊት ሞገስ ሆኖኝ እንደ ነበረ አምኛለሁና ከአዳራሾቻቸው አንደኛውን እንድጠቀምበት ፈቃድ ልጠይቅ ወደ ቢሯቸው በሄድኩኝ ጊዜ በደስታ ነበር የፈቀዱልኝ። በድጋሚ፣ ይህም ቢሆን የማይቻል በሚመስለው ሁኔታ ውስጥ ጌታ ፈቃዱ እንዲፈጸም ጣልቃ ሊገባ የሚችል መሆኑን የሚጠቁም ሌላኛው ምልክት ነበር።

መላው የሠርግ ኩበረ-በዓል እና የነበሩት ማኅበራዊ ክስተቶች እንደ ተጠናቀቁ፣ ባለቤቴ እና እኔ ለሥመራ ዩኒቨርስቲ በቸርነት ወዳዘጋጀልን የቲራቮሎ እልፍኝ ሄድን። አፓርታማው ቀደም ሲል ተገንብቶ የነበረው በቃኘው የሳተላይት ጣቢያ ይሠሩ የነበሩትን አሜሪካውያንን ለማስተናገድ ነበር።[48]

አዲሱን የጋብቻ ሕይወታችንን ከመጀመራችን በፊት መጀመሪያ





ያደረግሁት ነገር አዜብ ከእኔ ጋር ተንበርክካ የወደፊት ዘመናችንን ለጌታ እጅ አሳልፈን እንድንሰጥ እንጸልይ ዘንድ መጠየቅ ሆነ። ከዚያ በፊት ግን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ጥቅስ አነበብኩላት፦

> ይህን ስለ ቈረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥14-15)

ጋብቻችንን እና በወደፊቱ ጊዜም ሊሰጥ የሚችለውን ትርጉም ሁሉ በዚህ ቃል ብርሃን እንደምመለከተው አብራራሁላትና እንደ ባልና ሚስት ሕይወታችንን ሊመራ የሚገባው መፈክርም ሆነ መምሪያ ይህ ሊሆን እንደሚገባ አበክሬ ነገርኳት። ሁሉንም ነገር ለጌታ ሰጠንና እርስ በርሳችን በፍቅር በተቃቀፍንበት ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አልጋ ሄድን። ምንም እንኳን ከጥልቁ የልቤ ዳርቻ ሆኜ ያልኩት ቢሆንም፣ ሁለታችንም ጳውሎስ የተናገረውን ነገር ጥልቀት በእውነት ተገንዝበነው እንደ ሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው ያንን ኃይለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ በጋብቻ ሕይወታችን ጉዞ ሁሉ ውስጥ ኖረነው እንደ ሆነ ለመገምገም ለእኔ ከባድ ነው።

ልጆች እንዲኖሩን ብርቱ የሆነ መሻት ነበረኝ፣ ደግሞም በጥቅሉ ልጆችን እወዳለሁ። ነገር ግን፣ ምክንያታዊ ያልሆነውን "ልጆች ባይኖሩኝስ?" የሚለውን ፍርሃት ማስተናገድ ጀመርኩ። የዚያን ፍርሃት ምንጭ ባላውቅም፣ የተጋቡ ጥንዶች ፈጠኑም ዘገዩ ልጅ ይኖራቸዋል ከሚለው አጠቃላይ መጠባበቅ ውጪ ልጅ እንዲኖረኝ ምን ያክል ናፍቄ እንደ ነበር ለማንም አልተናገርኩም። ስለ ነገሩ ጸለይኩኝና ጌታ ኢየሱስ ምትክ የሚሆነኝንና የሞተውን ወንድሜን ኀዘን የሚያስረሳኝን ወንድ ልጅ እንዲሰጠኝ ስለምነው፣ ጌታ ጸሎቴን መለሰልኝ። ከተጋባን ጥቂት ወራት በኋላ አዜብ ነፍሰ-ጡር መሆኗን ስሰማ ፍጹም እርግጠኛ በመሆኔ ጓደኞቼ እስኪደነቁ ድረስ በእርግጠኝነት ወንድ ልጅ እንደሚሆን ተናገርኩ። የእርግዝናዋ ሦስት ወራት ሲቆጠር የቀሩትን የቤተሰቤን አባላት ልታያቸው እንድትችል ወደ ሐረር ይዤያት ሄድኩኝ። በዚያው ሳምንት የሚደረገውን የጓደኛዬን የቴዲን ሠርግ መታደም ስለፈለግንም ጭምር ነበር የሄድነው። ሆኖም፣ ከአዲስ አበባ ወደ ድሬዳዋ የሚወስደውን ሻካራ ጉዞ በባቡር እንድንሄድ በማድረጌ ስሕተት ሠራሁ። ስለዚህም፣ ሐረር ውስጥ ጥቂት

ቀናት ብቻ ከቆየን በኋላ ለቴዲ ሠርግ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ነበረብን።

በሚቀጥለው ቀን አዲስ አበባ እንደ ደረስን፣ የእሑድ አምልኮን ለመታደም ወደ አይኢሲ. ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ መጠነኛ ደም መፍሰስ እንደ ገጠማት አዜብ ነገረችኝ። ከእርግዝናዋ በኋላ የወር አበባዋ መምጣቱን አቁሞ ስለ ነበረና ያንን ማስተናገድ ስላልነበረባት፣ ሁለታችንም ግራ ተጋባን። ወደ መድኃኒት ቤት ሄደን አንዳንድ መድኃኒት ከገዛን በኋላ፣ ቢያንስ አምልኮ እስኪያልቅ ድረስ ጊዜያዊ መፍትሔ አገኘች። የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ሲያልቅ ታክሲ ይዘን ያን ጊዜ የሕክምና ዶክተር የነበረው የልጅነት ጓደኛዬ ብሬ ለምሳ ይጠብቀን ወደ ነበረበት ላሊበላ ሆቴል ሄደን፣ እንዳገኘነው የአዜብን ሁኔታ አሳወቅነው። ችግሩን ወዲያውኑ ገመተና መጀመሪያ ወደ ቤት መሄድ እንዳለብን ነገረኝ። ቁልፉን ለባለቤቱ ሰጥቷት በዝግታ እንድትነዳ ከነገራት በኋላ ወደ ቤቱ ስንደርስ ከእርግዝና ጋር በተያያዘ በባለቤቴ ላይ ሊያየው የሚገባው አንዳች ነገር እንደ ተፈጠረ አስታውቆኝ፣ ምን ያክል ተርበትብቼ እንደ ነበረ በማስተዋሉ፣ ዘና እንድል እና እንድረጋጋ ነገረኝ። ለባለቤቴ የምታርፍበት ቦታ ሰጣትና በሕክምና ሙያው ያስተዋለውን ነገር ሳይነግራት በአንዳች ዓይነት አኳኋን እንድትተኛ በማድረግ እንድትረጋጋ፣ እና በዚያ አተኛኘት እንድታርፍ መከራት።

በቀላሉ እንደምረበሽ፣ ደግሞም በትንንሽ ነገሮች እንደምጨነቅ ጥሩ አድርጎ ያውቀኛል። በአዜብ ሁኔታ ውስጥ ተፈጥሮ ሊሆን የሚችለውን ነገር ለራሱ እና ለሚስቱ ለአባይ በምሥጢር ጠብቀው ቆዩ። የደም መፍሰሱን ሁኔታ በትጋት ከመረመረ በኋላ እንደ ቆመ ተረዳ። ደሟ መፍሰሱን ባያቆም ኖሮ የመጀመሪያ ልጃችንን እንደምናጣው እግዚአብሔር ስላወቀ፣ የእርሱ ዕቅድ እንዲፈጸም በዚያ ቀን ያገኘን ዘንድ ጓደኛዬን አዘጋጀልኝ።

ቀደም ባለው ሳምንት ውስጥ በጋሪ እንጓዝ በነበረበት ጊዜ እንዲሁ ዓይነት አንዳንድ እንግዳ ነገር መፈጠሩን አስተውለናል። ያን ጊዜ፣ ከእርግዝናዋ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ያልተለመደ ነገር እየተሰማት እንደ ሆነ አዜብ ስትነግረኝ በፊቷ አልቅሼ፣ "ውርጃ እያጋጠመሽ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ" አልኳት። እምነቷን ያደነቅሁበት በእርሷ በኩል የተሰጠኝ አጭር እና ቁርጥ ያለ መልስ ግን፣ 'ጌታ ያበጀውን ማንም አያፈርሰውም' የሚለው ነበር። ምንም እንኳን ብሬ የሚያነቃትን ምንም ዓይነት ምልክት ያልሰጣት ቢሆንም፣ አዲስ አበባ ውስጥ በገጠመንም ነገር እንዲሁ ዓይነት ነገር ተሰምቷታል። በድጋሚ ጌታ የሰይጣንን





ዕቅድ ለመቀልበስ እና የእርሱን ዓላማ በሕይወታችን ውስጥ ለመትከል ኃይሉን ገለጠ።

ከእረፍት በኋላ ወደ አሥመራ ተመለስን፣ ነገር ግን በእርስ በርሱ ጦርነት መባባስ እንደ አዲስ መቀስቀስ ተቸገርን። የኤርትራን ከኢትዮጵያ መንግሥት መገንጠል ፈልገው ይዋጉ የነበሩት ኃይላት ሻቢያ ተብለው በተለምዶ ይጠሩ እንጂ፣ የኤርትራ ሕዝቦች አብዮታዊ ግንባር በሚለው ስማቸው እየተዋጉና ከቅርብ ርቀት ሆነው መድፍና ከባድ መሣሪያዎችን በዋናነት ወደ አየር ማረፊያው እየተኮሱ ወደ ከተማይቱ ተቃርበዋል። ምንም እንኳን አብዛኞቹ ተኳሾቹ ዒላማዎቻቸውን የሚመቱ የነበረ ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ ቀልሃዎች በሰላማዊ ሰዎች መኖሪያ አካባቢ ያርፋሉ። በሌሊት ቀልሃዎቹ በጣሪያችን ሲያልፉ ፉጨታቸውን፣ ፍንዳታዎቹም መሬቱንም ሲመቱ ድብይቱን እየሰማን ሁለታችንም በፍርሃት ተቆራምደን እንጸልያለን። ይህ ከስተት የየዕለቱ እየሆነ ሄደ።

የምጽዋ ወደብ በሽምቅ ተዋጊዎቹ መያዝ ለመንግሥትም ሆነ ለሁላችንም በእጅጉ አስደንጋጭ ነገር ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ከተማይቱ አንዳንድ ወሳኝ የሆኑ የምግብ አቅርቦቶችን ከአዲስ አበባ በወደቡ በኩል ታገኝ ነበርና ያ ተቋረጠ። ወዲያውኑ ጤፍን ጨምሮ የበርበሬ እና ሌሎች ምርቶች ዋጋ አሻቀበ። ስንጋባ 250 ብር የነበረው የጤፍ ዋጋ ወደ 400 ከዚያም ወደ 800 ብር አሻቀበ፤ የሌሎች ምግቦች ዋጋም እንዲሁ። ያን ጊዜ አዜብ ሥራ ስላልነበራት ከአንድ ወገን ብቻ የሆነ ገቢ ላላቸው አዲስ የተጋቡ ጥንዶች ያ ሁኔታ አዲስ አሳሳቢ ሸክም ፈጠረ። መንግሥት ምግብ በአውሮፕላን ማጓጓዣነት እንዲገባ በማድረግ ሁኔታውን በከፊል ማረጋጋት ጀመረ። ነገር ግን አየር ማረፊያውን በቦንብ መደብደብ በመቀጠሉ፣ በቂ የነበረውን የአየር ማረፊያውን አገልግሎቶች ጠቀሜታ አደናቀፈው። የጦርነቱ መባባስ ውኃን፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎቶችን፣ ጨምሮ እያንዳንዱን የሕይወት ገጽታ አጠቃው። ይህም መደበኛውን የሕይወት ሁኔታ እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ አደረገው።

ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከውጪ እርዳታ ትቀበልና እንደየሰዉ የገቢ ልክ በጥቂት ክፍያም ሆነ በነጻ አቅርቦት ለአባላቷ መሠረታዊ የምግብ ዕቃዎች ትሰጥ ስለ ነበር፣ በእንዲህ ዓይነቱ ቀውስ ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በድጋሚ እኛን በመመገብ ኃይሉን ገለጠልን። በቤተ ክርስቲያን በኩል የበቃ የምግብ

ዓይነቶች ስለ ነበሩን፣ በጣም ተባርከን ያንን ጊዜ አሳለፍነው።

ለቤተሰቡ ገቢ የሚያስገባው ብቸኛ ሰው እኔ በመሆኔ በመጠኑ ብጨነቅም፣ አንዳንድ ጊዜ የእምነቷ ምንጭ ከየት ይሆን እያልኩ እስክጠይቅ ድረስ አዜብ በእምነቷ የተረጋጋች እና ጽኑ ሴት ነበረች። አዜብ በጌታ ገና ልጅ የነበረች ሲሆን፣ የእኔን ያክል መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ወይም ቢቃል በማጥናት ብዙ ጊዜ ባታሳልፍም፣ በእግዚአብሔር ላይ ያላት ብርቱ እምነት ግን አስደናቂ ነበር። አንድ ጊዜ ዋጋቸው ከመጨመሩ በፊት ዕቃዎችን ገዝቶ ለወደፊቱ ማስቀመጡ የተለመደ ነገር ስለ ነበረ እና ሌሎችም እንዲሁ ስላደረጉ እርሷም እንደዛው እንድታደርግ ስነግራት ምላሿ፣ "እንደ አሕዛብ አላደርግም!" የሚል በመሆኑ አስደነገጠኝ። ሊታስቀምጠው የፈለገችው ነጥብ ለእኔ አሳማኝ ባለመምሰሉ ሚስቴ እንድትሆን የመረጥኳትን ሴት ምን ያክል እንደማውቃት አንዳች ያልሆነ ጥርጣሬ ቢያሳድርብኝም፣ እምነቷ ግን ፈጽሞ አሳማኝ ነበር።

በሚካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት ሁኔታ ውስጥ ዩኒቨርስቲው እንደሚገባ መሥራት ስላልተቻለ፣ በዚህ ቀውስ ውስጥ የአሥመራ ዩኒቨርስቲን ዕጣ ፈንታ በተመለከተ በመንግሥትና የዩኒቨርስቲው መኮንኖች መካከል ውይይቶች ይካሄዱ ጀመር። የከፍተኛ ሥራ ሂደትን እና የምግብ አቅርቦት ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን፣ የተማሪዎች ደህንነት ጉዳይም ወሳኝ ነገር ሆነ። በመጨረሻም፣ ዩኒቨርስቲው ለጊዜው ወደ አዲስ አበባ እና በባሌ ክፍለ-አገር ባለው አጋርፋ እንዲዘዋወር ተወስኖ የፋኩልቲው ሠራተኞች እና ተማሪዎች አሥመራን ለቅቀው እንዲወጡ የአጭር ጊዜ መመሪያ ተሰጣቸው። በዚህም መሠረት አዜብ እና እኔ አዲስ የገዛናቸውን ንብረቶች ሁሉ እና ምርምር-ነክ ሰነዶችን ጨምሮ ለእኔ እጅግ ክቡር የሆነውን ምትክ የማይገኝለትን የብዙ ዓመታት የዕለት ሁኔታ መመዝገቢያዬን እና ብዙ ነገሮችን እዚያው በመተው አሥመራን ለቅቀን ወጣን። ከተማይቱ በሻቢያ ኃይሎች እጅ ሥር ትወድቃለች ብለን ለአንድ ጊዜም ቢሆን ስላላመንን፣ ወደ ፊት የሆነ ጊዜ ላይ እንመለሳለን ብለን በገራገርነት አስበን ተሰደድን።[49]

አዲስ አበባ ውስጥ ሕይወትን እንደ አዲስ መጀመር ነበረብን። የቀሩት ፋኩልቲ እና ተማሪዎች ወደ አጋርፋ፣ ባሌ ሲሳኩ፣ እኔ ግን አንዳንዶቹ የአሥመራ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተመድበው በነበረበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዳስተምር ተመደብኩ። መጀመሪያ ላይ፣ ከተመሠረተ ብዙ ዓመት በሆነው





አሮጌው የጣይቱ ሆቴል ስናርፍ ምንም እንኳን ለክፍሉ የሚከፈለውን መንግሥት እየከፈለ ቢሆንም፣ ኑሮ በመጠኑ ተወድዶብን ተቸገርን። ብዙም ሳይቆይ፣ የመጀመሪያው ወንድ ልጃችን መወለጃ ጊዜ እየደረሰ በመምጣቱ የምንከራየውን ቤት መፈለግ ጀመርን፣ ደግሞም እንደ መሸጋገሪያ ውሳኔ በቴዲ አፓርታማ ውስጥ አረፍን። ከዚያም አንድ መኝታ ቤት እና ኩሽና ያላትን አነስተኛ የሆነች ሕንጻ ነፋስ ስልክ አካባቢ በወር 200 ብር ተከራይተን ለጥቂት ወራት እዚያኖርን። ከብሬ አገዛ ጋር የመጀመሪያ ልጃችንን ሳሙኤልን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስንታቀፍ፣ ሐና የመጀመሪያ ልጇን ነብዩ ሳሙኤልን ባገኘችበት መልኩ እኛም በጸሎት ያገኘነው ልጅ በመሆኑ፣ ሳሙኤል ብለን ሰየምነው።

ልጅ ስላገኘን እና ጠያቂዎች ወደ እኛ ሊያዩን ይመጡ ስለ ነበር፣ ቤት መቀየር ባስፈለገን ሰዓት ላይ ጌታ በድጋሚ እጁን ዘረጋልን። የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ከአሥመራ ለመጡት ሰዎች ማረፊያ የሚሆናቸውን ቦታ በጣም ይፈልግ ነበርና ከምሥራቅ አውሮጳ አገሮች ወደ አገራችን መጥተው የነበሩትን ሰዎች ለማስተናገድ በዋናነት ተይዘው የነበሩትን አንዳንድ አፓርታማዎች ለጊዜው እንድንጠቀም የትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ ሰጠን። ጥያቄው "ለበርካታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች አፓርታማውን ማከፋፈል የሚገባው በምን መስፈርት ይሁን?" የሚለው ሲሆን፣ ለሁሉም ፍትሐዊ ለመሆን ሲባል በዕጣ እንዲሰጥ ተወሰነና ቤት በዕጣ ለመቀበል ዕድለኞች ከሆኑት መካከል አንደኛው እኔ ሆንኩኝ። በእርግጥ፣ ከምርጥ ጓደኞቼ አንደኛው የሆነው እና በድንገት ከመሞቱ በፊት የኮምቦልቻ ወረዳን ያገለግል የነበረው ጴጥሮስ በመሞቱ ምክንያት ለቅሶ ወደ ሐረር ሄጄ በነበረበት፣ ስለ እኔ ሆኖ ዕጣውን ያወጣው ጓደኛዬ አቤ ነበር። ወደ ሐረር ከተጓዝኩኝ በኋላ መልካሙ የምስራች ሲነገረኝ፣ ዕጣውን ስለ እኔ ያወጣው አቤም የአፓርታማው ባለ ዕድል እንደ ሆነ ጭምር ሰማሁ። አቤ የወጣለት ቤት የሚገኘው ከፍተኛ የመኖሪያ አካባቢ በሆነው ቦሌ አካባቢ ሲሆን፣ የእኔ ደግሞ በቡና ቤቶቿ ታዋቂ በሆነችው ካዛንቺስ ውስጥ ሆነ። በመንግሥት የተያዙ አፓርታማዎችን ለማግኘት አንድ ሰው እስከ አሥር ዓመታት ድረስ ይጠብቅ በነበረበት በእነዚያ ዘመናት ከሚገጥሙ ጥቂት ነገሮች አንደኛው ይሄ በመሆኑ የእውነት ትልቅ ክብረ-በዓል አደረግን።

በአስደናቂ እና ምቹ ሁኔታ በአዲስ አበባ መካከል በምትገኘው ካዛንቺስ

ወደሚገኘው አዲሱ ቤታችን ተዘዋወርን። በአካባቢው "አረንጓዴዎቹ ሕንጻዎች" ይባሉ የነበሩ በዩኒቨርስቲ ያስተምሩ ለነበሩ ኩባውያን እና የምሥራቅ አውሮጳ ፋኩልቲ አባላት በመንግሥት ቅርብ ጊዜ የተገነቡ ሁለት ትልልቅና አዳዲስ አፓርታማ ሕንጻዎች ነበሩ። የእኛ አፓርታማ 778/14 የሚል ተጽፎበት በ4ኛ ፎቅ ላይ ያለ ሲሆን፣ አንድ ትልቅ መኝታ ቤት፣ አንድ የመመገቢያ ክፍል፣ እና ትንሽ ኩሽና ነበረው። በእርግጥም ለኑሮ የሚወደድ እና በጣም ውብ አፓርታማ በመሆኑ፣ ጥሩ ቤት በተዓምራዊ መንገድ ያዘጋጀልንን ጌታ *ጀሆቫ ጃይሬን* አመሰገንን።

አዲስ የገባንበት ቤት ለሚጎበኙን ሰዎች ማስቀመጫ ወንበርን ጨምሮ ምንም ዓይነት የቤት ዕቃ አልነበረውም። በጥቂቱ የምትሰፈርልንን ገንዘብ አልጋ እና የመመገቢያ ጠረጴዛ፣ ደግሞም ጥቂት ወንበሮች እና አንዳንድ የኩሽና ዕቃዎችን ገዛንበት። በጎረቤት የነበረው የአቤ ጓደኛ፣ ሽፌ ጥቂት በርጩማዎችን እስካመጣልን ጊዜ ድረስ ለጎብኚዎች ማረፊያ ልንገዛው እንችለው የነበረው ብቸኛ ነገር የሰሌን ምንጣፍ ነበረ።

የሚያስደንቀው፣ ጌታ ያልተጠበቀ የዕድሎችን በር በመክፈት በረከቱን በእኛ ላይ አዘነበው። ለተወሰኑ ጊዜያት አገኘው የነበረውና አጻጻፈው የነበረው የሚሽጋን ስቴት ዩኒቨርስቲ መምህሩ ፕሮፌሰር ሐሮል ማርከስ - ቫኒቲ ፌር (ከንቱ ትርኢት) ከሚባል መጽሔት ጋዜጠኛ ጋር ለምርምር ጉዞ ወደ አዲስ አበባ መጣ። የምርምር ሥራን የሚያቀላጥፍ እንዲሁም ቃለ መጠይቅ ለሚያደርግላቸው ደግሞ የሚያስተረጉምለት ሆኜ ረዳሁት። ጉዞውን ከማጠናቀቁና ወደ አሜሪካ ከመመለሱ በፊት በሒልተን ሆቴል ቁርስ ላይ የተዋወቀውን የክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ባስተዋወቀኝ ሰዓት ላይ ለአካባቢው አዲስ ስለ ነበሩ የምርምር ሥራ ረዳት በማፈላለግ ላይ ነበሩ። ማርከስ ረዳታቸው እንድሆን እኔን በተመለከተ ጥሩ መረጃ እና ጥሩ ጥቆማውን ከሰጣቸው በኋላ፣ በሚቀጥለው ቀን የቲቪ ሠራተኞቹን ተዋወቅሁኝና ከእነርሱ ጋር መሥራት ጀመርኩኝ። ያ ከመሆኑ በፊት ባለው ቀን ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ ደወለልኝና ጥሩ ሊከፈለኝ የሚገባኝ ሆኜ እንዳገኘኝ ነገረኝ። ቀጥሎም፣ "ከአሜሪካ የመጡ ጥቂት ጋዜጠኞችን ትረዳቸዋለህ፣ እነርሱም በቀን 50 ይከፍሉሃል" ሲለኝ አመሰገንኩት። ከዚያም "ያልኩትን አድምጠሃል?" "በእያንዳንዱ ቀን ምን ያክል ልታገኝ እንደ ሆነ አውቀሃል?" ሲል





ጠየቀኝ። 50 ብዬ ስመልስለት ሳቀና "50 የአሜሪካን ዶላር ነው" አለኝ። እኔ ግን በራሱ በቂ የነበረውን በቀን 50 የኢትዮጵያ ብር እንደሚከፈለኝ በማሰብ ላይ ነበርኩ። ነገር ግን፣ 50 የአሜሪካ ዶላር ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር ማለት ብዙ ገንዘብ ማግኘት ማለት በመሆኑ እንደ ምርምር ረዳት ሆኜ በአንድ ቀን አገኘው የነበረው ገንዘብ በአነስተኛ ገቢ ያለ መካከለኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ቅጥረኛን አማካኝ የወር ገቢ ያክል እንደሚሆን በማሰብ ጌታን አመሰገንሁ። ያንን ያክል ገንዘብ በቀን ማግኘት፣ ከዚያም ሌላ ምግቤን በየዕለቱ ከቀሩት የቲቪ ሠራተኞች ጋር እንድመገብ መደረጉ ተደራራቢ ተዓምራት ሆነውብኝ ሰነበትሁ።

ከቲቪ ጋዜጠኞቹ ጋር ኢትዮጵያ ውስጥ በቆዩበት ጊዜ ልክ አብሬ ሠራሁ። ወታደራዊው መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) የጦርነት ትግል ተገርስሶ ኢሕአዴግ ሥልጣን በመያዙ በአገሪቱ የሽግግር ወቅት ወሳኝ ሰዓት ላይ ነበር ጋዜጠኞቹ የመጡት። ቡድኑን እንደ ምርምር ረዳትና እንደ አስተርጓሚ ብቻ ሳይሆን፣ ምርጥ የሚባለውን የጋዜጠኝነት ተደናቂነት እንዲያገኙ ምን ዓይነት ስልታዊ ርእሶች ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ እየተከናወነ ላለው የመቃብር ቁልል ዓይነት የለውጥ ባሕርያትን እንዲያገኙ እንደ አማካሪ ሆኜ ብዙ ነገር ጠቀምኳቸው።

አጋዴን፣ በተለይም ቀላፎ እና ጎዴ አካባቢ ያሉ አደገኛ የሆኑ የተመረጡ ቦታዎች ድረስ ሄደን ከወታደራዊው መንግሥት መውደቅ ጋር በተያያዘ እና የሶማሌ ነዋሪዎችም ለውጡን እንዴት እንደ ተቀበሉት አጋዴን ውስጥ ስላለው ሁኔታ የሚማርኩ ሥራዎችን አከናወንን። በዋና ከተማዋ አካባቢ ባሉ ገጠራማ አካባቢዎች የመልሶ ሰፈራ ጉዳይን በተመለከተ እንዲሁም የተበተኑትን ወታደሮች ሁኔታም በተመለከተ አዳዲስ ሥራዎችን አከናወንን።[50] የቲቪ ሠራተኞቹ ኋላ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ሠሯቸው አንዳንድ ዝግጅቶች የተለየ ሽልማት (አዋርድ) ተሰጣቸው። ኋላ ላይ፣ ከቲቪ ሠራተኞቹ ዲሬክተር የአድናቆት ደብዳቤ ስለ ደረሰኝ መሸለማቸውን ለማወቅ ቻልኩኝ።

ቡድኑ ወደ አገሩ በሚመለስበት ጊዜ በሠራሁባቸው ቀናት ልክ ለፈጸምኩት አገልግሎት ክፍያዬን፣ እንዲሁም ደግሞ እንደ ምስጋና መግለጫ ተጨማሪ ጉርሻ ክፍያዬን በጥሬ ገንዘብ ስቀበል፣ በሕይወት ዘመን ቆይታዬ አይቼው የማላውቀው እንዲያ ያለ ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ እጄ ገባ። ይህንን ተዓምራት ነበር ከማለት በቀር ሌላ ምንም ነገር የተፈጠረውን ነገር ሊገልጠው አይችልም።



ቤተሰቤ- ባለቤቴ አዜብ ተሰማ እና ልጆቼ ሳሙኤል፣ ሕሊና፣ ጸጋ

ከቲቪ ሠራተኞቹ ጋር በመሥራቴ ያገኘሁት የገንዘብ ሲሳይ በቤተሰባችን ሕይወት ላይ አስደናቂ የሆነ ለውጥን አመጣ፣ እኖርበትም የነበረው አፓርታማ በሚያስገርም መልኩ ተለወጠ። የተከበረ አፓርታማ ሊኖረው የሚገባቸውን እንደ ማቀዝቀዣ፣ የተሟላ ቲቪ፣ እንደ ማብሰያ ምድጃ እና ሌሎች የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ጭምር ገዝተን አሟላንለት። የገንዘብ ችግር የነበረባቸውን ዘመዶች በመርዳት እና ዕዳዎቻችን መክፈል ዓይነተኛ ጉዳይ ሲሆን፣ ሌሎች ነገሮችንም ለማድረግ የሚያስችል የተረፈ ገንዘብ ነበረን።

ቀጣዩዋ ልጄ ሴት እንድትሆን የነበረኝን ምኞት ለእግዚአብሔር ነግሬው ስለ ነበር ጌታ አከበረኝ፣ ደግሞም የምወዳትን ልጄን ሕሊናን በዚያው ዓመት ሰጠኝ። ሕሊና የሚለው ስያሜ ትርጉም በኢትዮጵያ ባህል ውስጥ ማዕከላዊ ከሆኑ የግብረ-ገብ እሴቶች ጋር በተያያዘ በሕሊናችን ግዛት ውስጥ ጠልቆ የተቀረጸብን ነገርን እንደሚያመለክት የታወቀ ነገር ነው። በእናቷ ውስጥ እንዲህ ያለውን የግብረ-ገብ አመዳደብ አይቼ ስለ ነበር፣ ሴት ልጄን ሕሊና በማለት ለመጥራት ፈልጌ የነበረው ለእርሷ ማስታወሻ እንዲሆን በማሰብ ነው። በውስጡ የአንድን ሰው ግብረ-ገባዊ ትክክለኛውን ነገር ለመፈጸም የመፈለግ ሁኔታ የሚያሳየው ሕሊና የሚለው ጽንሰ ሐሳብ እኔም ራሴ የምሬን የማደንቀው ነገር ነው። ይህንን ስል ግን በዚህ ነገር እኔ ፍጹም ነኝ ወይም ሕይወቴን ለመምራት





በሚፈለገው ልክ ተጠቅሜበታለሁ እያልኩኝ አይደለም። ምንም እንኳን በአንዳንድ ትንንሽ የሕይወት ችግሮች ምክንያት የደመና ድባብ ሊጋርደው ቢችልም፣ በእርግጥም በአእምሮዬ የመረጃ ቋት ውስጥ ዘላቂ የሆነ ማገሪፊያን ያገኘ ብርቱ እሴት ነው። ሕሊና የተወለደችው በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ሲሆን፣ የእኅቴ ልጅ የጌቱ ጥሩ ጓደኞች የሆኑት የድሮ ጓደኞቼ ዶ/ር ብሬ እና ዶ/ር ሰብለ በሰላም እንድትወለድ እገዛ አድርገዋል።

## *ወዳጆችን በወንጌል መድረስ*

ምንም እንኳን ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔ የምሄደው አልፎ አልፎ ቢሆንም፣ ቤተሰቤ እና እኔ በመደበኛነት የአይኢሲ አምልኮን እንታደማለን። በዚህ ወቅት፣ አይኢሲ የተለያዩ ሰዎች ከወትሮው በበለጠ ሁኔታ የሚገኙበት ሆኗል። ከመካከለኛ ገቢ የሆኑ አያሌ ቤተሰቦች ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲጎበኙ፣ አምልኮውን የሚታደሙ ብዙ ቍጥር ያላቸው ሐረሪዎችንም ሲመጡ አይቻለሁ። አይኢሲ ይመጣ የነበረ ሌላኛው የሐረሪ ሰው ያን ጊዜ ለአድማስ አየር መንገድ ይሠራ የነበረው አብራሪው የትሽ እዚያው ተዋውቄው፣ ስለ ጋራ እምነታችን ግልጽ የሆኑ ውይይቶችን ማድረግ ጀመርን። በክርስቲያናዊ ጉዟችን ውስጥ ብርታት እና ጉድለት የሆኑትን ነገሮች በሐቀኝነት ስንነጋገር ቆይተን የጀመርነው ክርስቲያናዊ ሕይወት ተግዳሮት እንዳለበት ሁለታችንም ልንደመድም ቻልን። ይህንንም ስንነጋገር አልፎ አልፎ በመንገድ ላይ መሰናከሎች ቢገጥሙትም፣ በአዲሱ የእምነት ጎዳና ላይ ለመጓዝ ምን ያክል እንደሚፈልግ የትሽ እንዴት አድርጎ እንዳብራራልኝ በግልጽ አስታውሳለሁ - እንደዚህ ነበር ያለው፣ 'ምንም ቢሆን ውር ውር ማለቱ ይሻላል።' ሐቀኛ እና እውነተኛ የሆነው አገላለጹ ልቤን ነካኝና ወዲያውኑ "ብረት ብረትን ይቀርጸዋል የእኛኑ ኅብረት ለምን አንጀምርም?" ስል መለስኩለት፤ በሐሳቡም ተስማማ።

ከሐረር የመጣነው ሰዎች በግልጽነት የእምነት ጎዳናዎቻችንን እንወያይ ዘንድ፣ ምስክርነቶችን እንድንከፋፈል፣ አንዳችን ሌላችንን በጉዟችን ለማበረታታት፣ እርስ በርስ ለመደጋገፍ፣ እና አዲስ ባገኘው እምነታችን በአንድነት እንድናድግ ለማድረግ የሐረሪዎች ኅብረት ልናቋቁም ስለምንችልበት ሁኔታ ተወያየን። ሐረሪዎች በጥቅሉ ማኅበራውያን፣ ሐቀኞች፣ ደግ፣ ጨዋታ

አዋቂ እና በሕይወት ውስጥ ደስታ እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ናቸው። በጥቅሉ፣ "ለቀቅ ያለ" የሕይወት አኳኋንን የማድነቅ ዝንባሌ ስላለን፣ እንዲህ ላለ የሕይወት ዘይቤ ሥርዓት የያዘ መሰጠትን ማድረግ ከባድ ሊሆንብን ይችላል። እነዚህ ጥሩ ባሕርያት እንደ ሆኑ እናውቃለን፣ ነገር ግን ገደብ ከተነሣላቸውና እቀባ ከሌለባቸው ለክርስቲያን ሕይወታችን ጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን ከግምት በማስገባት በእኔ ቤት በሳምንት አንድ ቀን የሚገናኝ ኅብረት ለማድረግ ወሰንን።

ስለዚህም የሐረሪ ኅብረት በእኔ አፓርታማ ላይ ጥቂት ሆነን ተጀመረና ብዙም ሳይቆይ ዜናው በመናኘቱ ከሰው መቀላቀል የሚወዱት ሐረሪዎች በጋራ ሆነው መትመም ያዙ። በመንግሥት ከተዘጉትም ሆኑ ካልተዘጉት የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት የሆኑ ሐረሪ ክርስቲያኖች መምጣትና ከእኛ ጋር ማምለክ ጀመሩ። በዋናነት ከአይኢሲ የሆኑ ሰባኪዎች፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሰባኪዎችን እንዲመጡና የጌታን ቃል እንዲያካፍሉን እጋብዛለሁ። ምንም እንኳን በእነዚያ ዘመናት መምጣቱ የሚያስቸግር ቢሆንም፣ ከእኛ አካባቢ የሆኑ ሰባኪዎችን መጋበዙን እንወደዋለን። በመካከላችን የሚገኙና ቃሉን ለማካፈል ይችሉ የነበሩ ሰዎችንም ማግኘት ቻልን። ጉርሱም ውስጥ የልጅነት ጓደኛዬ የነበረውና የረጅም ጊዜ ክርስቲያን የሆነው ዶ/ር ጥላሁን መጽሐፍ ቅዱስን ጥሩ አድርጎ ያውቅ የነበረ ግሩም አስተማሪ ሲሆን፣ በመዘመር እና አምልኮ በመምራት ስጦታው ያላቸውን የብሬ እኅት ኤልሣ ዓይነቶቹን ሐረሪዎችንም አግኝተን ኅብረቱን በሙዚቃ የበለጠ ጸጋ አላብሰውት በእጅጉ ባረኩን። ኅብረቱ በመጠኑ ሊደገና በጣም ታዋቂ መሆን ስለ ጀመረ ማንም ሰው እንዲያመልጠው አይፈልግም ነበር።

የአባላት ወይም ታዳሚዎች ቍጥር በፍጥነት እያደገ ስለ ነበረ የድርጅት መልክ እንዲኖረው ኅብረቱን የሚያስተባብሩ ኮሚቴዎችን ስለ ማቋቋም ሐሳብ ካቀረብኩ በኋላ ኮሚቴው ወዲያውኑ ተቋቋመና እንደ ጌቾ፣ ዳኒ፣ መኩ እና እኔ ያለነው የኮሚቴው አባላት ሆንን። ምንም እንኳን የመጀመሪያው ፍላጎት በክርስቲያናዊ እምነታችን እርስ በርስ መበረታታት እና ማደግ ፈልገን ለነበርነው እንደ መድረክ እንዲሆነን የነበረ ቢሆንም፣ በኅብረቱ ላይ የጸሎት እና ወንጌል ስርጭት አገልግሎቶች እንዲኖሩበት ወሰንን። በእነርሱ ላይ ብዙ ጫና ሳናበዛ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና የማዳን ጸጋውን ያልተለማመዱ የሐረር





ጓደኞቻችንን ለመጋበዝ ራሳችንን በመስጠት ለእንዲህ ያሉቱ ጓደኞቻችን አካሄዳችንን እና የኅብረቱን ድባብ በተመለከተ ለእንግዶቻችን ምቹ ድባብ እንዲሆን እንጂ፣ ከእኛ እንዳያሸሻቸው በቂ የሆነ ጥንቃቄ አደረግን። ከዚህ የተነሣ፣ መደበኛ በሆነ መልኩ ባይሆንም፣ የእኔ የሆኑትን ጨምሮ አያሌ ወዳጆቻችን ኅብረቱን ታድመው የኢየሱስን የማዳን ወንጌል ሰምተዋል፣ አንዳንዶቹም እምነታቸውን በጌታ ላይ አድርገው የክርስትና እምነትን ኮስታራ በሆነ መሰጠት ቀጥለዋል። ሌሎች ለማመን ወስነው አዲሱን ጎዳና ለመከተል ግን የምራቸውን የተጓዙ አይመስሉም። አሁንም ሌሎች እንዲሁ ለጨዋታ እና ከእኛ ጋር ለመሆን የሚመጡም ነበሩ። ፍቅርን አሳየናቸው፣ ለእነርሱ መጸለያችንን ቀጠልን፣ ደግሞም የእምነት መሰጠቱን የማድረጉንም የመጨረሻ ውሳኔ ለእነርሱ ተውንላቸው። ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ምቾት የማይሰማቸውን የሐረሪ ወዳጆቻችንን ካለን ማኅበራዊ ትስስርና የወዳጅነት ጥምረቶች አኳያ በጥሩ አቀባበል አድርገን ቢያንስ የእግዚአብሔርን ቃል የመስማቱን ዕድል ማግኘታቸውን እርግጠኞች መሆን እንፈልግ ነበር።

## *ወደ አሜሪካ መምጣቴ - ከፍታዎች እና ዝቅታዎች*

ኅብረቱ በጥሩ ሂደት ላይ ሳለ፣ በቅርብ ለሞቱት ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ መልካም ሥራ ምስጋና ይግባቸውና ለፒኤች.ዲ ጥናት ወደ ሚሺጋን ስቴት ዩኒቨርስቲ መጣሁ። የዲኑ *የሪክሪዩትመንት ፌሎውሺፕ አዋርድ* ተሰጥቶኝ የአፍሪካ ታሪክ ላይ አውራ ትኩረት አድርጎ በሚያጠና የታሪክ ትምህርት ክፍል ውስጥ ገባሁ። የመጣሁት ብቻዬን ከመሆኑም በላይ፣ አየር-ንብረቱን፣ ባህሉን እና በፍጥነት የሚገሰግሰውን ሕይወት መላመዱ ቀላል አልነበረም። በዚህኛው የዓለም ጥግ ላይ ሁሉም ነገር በከፍተኛ ፍጥነት ይሄድ ስለ ነበረ፣ ከዚያ ፍጥነት ጋር አብሮ መብረሩ ለእኔ ከባድ ሆነብኝ። በዚያ ላይ ደግሞ ከውድ ቤተሰቤ መለየቱ ችግሬን አባብሶት መቸገር ጀመርኩ። በአሜሪካ ታሪክ ላይ የሁለተኛ ደረጃ አውራ ጥናት ለማድረግ ተስፋ ሰንቄ የአፍሪካን ታሪክ እና የአሜሪካንን ታሪክ ትምህርቶች ወሰድኩ። በሁለቱም የትምህርት ዓይነቶች ጥሩ ውጤት ቢኖረኝም፣ 'የአሜሪካ ታሪክ' የተባለው የትምህርት ዓይነት ከባድ ጫና ያለው ጉዳት አደረሰብኝ። አስተባብረው የነበረውንም

የሐረሪዎች ኅብረት በማጣቴ፣ ከጓደኞቼ ይደርሰኝ የነበረው ዜና እየከሰመ ሄደ። ኮስተር ባለ ውይይት እና የውስጥ አመኔታ ውስጥ ሳልሆን እያቅማማሁም ቢሆን የመረጥኩት ምርጫ ስለ ነበር፣ ራስ ወዳድ ለሆነ የትምህርት ዕድል ወደ አሜሪካ በመምጣቴ የበደለኝነት ስሜት ይሰማኝ ጀመር። በዚህ ምክንያት፣ ከሞላ ጎደል ለሰባት ወራት በእያንዳንዱ ቀን በከፍተኛ ሥቃይ ኖርኩኝ።

እነዚያን አስቸጋሪ ወራት ያለ ፕሮፌሰር ማርከስ እና የትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን አባላት ድጋፍ ባይሆን ኖሮ ፈጽሞ አልቋቋማቸውም ነበር። አሜሪካ ከደረስኩበት የመጀመሪያው ሳምንት ጀምሮ አፍሪካውያንም ሆኑ ኢትዮጵያውያን ኅብረቶች ውስጥ ወንድሞችን እና እኅቶችን እንዳገኝ ስል ይህችን ቤተ ክርስቲያን በመደበኛነት እታደምባት ጀመር። በውጤቱም፣ የጨለማ ቀናቴን ጸንቼ የተወጣሁባቸው የኢትዮጵያውያን እና አፍሪካውያን ወንድሞቼ እንዲሁም እኅቶቼ ጸሎት እና ኅብረት ብርታትን ሰጠኝ።

ከትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለይም የዓለም አቀፍ ኅብረቶች ላይ የሚሳተፉትን እንደ ጂም ጌትስ፣ ኢርቪን እና ሩሜሊያ፣ ደግሞም ዶናልድ ዎልፍ ያሉ አንዳንድ አሜሪካውያንን እንዲሁም ሌሎች እንደ አንድሬያ፣ ሬክ እና ቫንጊ ያሉትን የዓለም አቀፍ ሰዎች በጥሩ ጓደኝነት አፈራሁ። ከቦትስዋና የሆነውና ለትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለአፍሪካ ኅብረት ያስተዋወቀኝ ፑዞ ሰኮላ በአፍሪካ ኅብረት ውስጥም አዳዲስ ጓደኞችን እንዳፈራ ረዳኝ። በአፍሪካ ኅብረት ውስጥ  እንደ ጆርጅ እና አን ሙኛይ ከኬንያ፣ ሳም ከጋና ያሉ ብርቱ የሆኑ ክርስቲያኖችን አገኘሁ። በዋናነትም ከምዕራብ አፍሪካ የሆኑ በመንገዴ የገጠሙኝም ጥሩ ክርስቲያን ጓደኞችም ነበሩ። የኢትዮጵያውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረትም (በአብዛኛው ሳምሶን፣ ማቴዎስ እና መሲን ያካተተው) መጽሐፍ ቅዱስን በጋራ ስናነብ እና በገዛ ቋንቋችን ስንጸልይ፣ ከዚያም በኋላ፣ ኅብረት ስናደርግ ትልቁን ክፍተት ሊሞላልኝ ቻለ። በምድረ በዳ ልምምዴ ውስጥ በማልፍበት ጊዜ እንዲህ ያሉ ጓደኞችን መተዋወቁ እና ከእነርሱም ጋር መጸለዩ የትልቅ መጽናናት ምንጭ ሆነልኝ። በእያንዳንዱ አርብ ላይ በመደበኝነት ልጾምና ልጸልይ ቁርጠኛ ውሳኔ ካደረግሁ በኋላ፣ ይህንን ምሥጢሬን የሰሙት ፕሮፌሰሬ አንድ ጊዜ፣ "አርብ ላይ ጥበበን አትፈልጉት፣ ወደ መስጂድ ይሄዳልና" ሲሉ ቀልደውብኛል።

ወደ አገሬ መመለስ እንዳለብኝ ለበርካታ ጊዜያት የምር ይሰማኝ ስለ ነበር፣





አገሩ ከፉኛ የናፈቀው ወይም ባህሉንና የትምህርት ድባቡን በጥሩ ሁኔታ መላመድ ያልቻለ አድርገው አንዳንድ ሰዎች አስበውኝ ያውቃሉ። እውነት ነው፣ በግምገማቸው ውስጥ ሚዛን የሚደፋ እውነታ አለ። ምክንያቱም፣ ወደ ጌታ ከመምጣቴ በፊት ባሉት ዘመናት እንደ ነበረው ዓይነት የድሮ ተማሪ አልነበርኩም፣ ኤምኤስዩ (ሚሺጋን ስቴት ዩኒቨርስቲ)ን ከመቀላቀሌ በፊት የአፍሪካ ቀንድ ችግሮችን በተመለከተ ለምሁራኑ ዓለም የበኩሌን አስተዋጽዖ ያደረግሁኝ ታታሪ ሠራተኛ ነበርኩኝ፣ በትምህርት ሕይወት ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ተሳክቶልኛል ብዬ የማስብ ሰው ነኝ። በአዲሱ ሁኔታ ውስጥ ስገኝ ግን ለመማር ምንም ያክል ራሴን ብሰጥ የመሳቡን ነገር አጥቼው ስለ ነበር፣ ያለማቋረጥ ይረብሸኝ የነበረ አንድ ነገር ተፈጠረብኝ። የኋላ ኋላ፣ ከዚህኛው የሕይወት ጥግ ውስጥ የሚወጣ ምንም ዓይነት ጉተታ እንደሌለ፣ ከዚያ ይልቅ ጉተታው ይሰማኝ የነበረው ከአገሬ እንደ ሆነ ገባኝ። እዚያ እንኝ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ ስለሚሰማኝ፣ ለፒኤች.ዲ ትምህርት መምጣቴን አስጨናቂ ስሕተት አድርጌው መቍጠር ጀመርኩኝ። በመጨረሻም፣ አንዳንድ ጓደኞቼ እና ፕሮፌሰሬ ያ ይሆን ዘንድ ባይፈልጉም፣ ልቤ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር መፍታት ሳልችል በመቅረቴ የፒኤች.ዲ. ትምህርቴን አቋርጬ ወደ አገሬ ለመመለስ ወሰንኩኝ። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ ሳለሁ፣ ባለቤቴ ወደ አሜሪካ የመምጣቷን ነገር በጽኑ አቋም ገለጸችልኝ፤ ደግሞም ትምህርቴን እንዳላቋርጥና እንድገፋበት በመገፋፋት ተቆጣችኝ።

በትምህርቴ ለመቀጠል እያቅማማሁም ቢሆን ግፊቱን ተቀበልኩኝና ሁለተኛው መንፈቅ ዓመት ላይ ቤተሰቤ ተቀላቀለኝ። እነርሱ ሲመጡ የተቀላቀለ ስሜት የነበረኝ ቢሆንም፣ እነርሱን በመቀበሌ ደስተኛ ነበርኩኝ፤ ነገር ግን አልፌበት የነበረው ስሜት ቢቀጥልስ የሚል የዘለቀ ፍርሃት ነበረኝ። በተለይ ወንድ ልጄን ሳምን እና ሴቷ ልጄን ሔሉን ስላየሁ ደስ ተሰኝቼ የነበርኩ ብሆንም፣ ነገሮች ህልውናቸውን ባይቀይሩ ኖሮ ግን ጭንቀቴን ያባብሱት ነበር። በልቤ ጥልቀት ውስጥ "ጥሩ አይሆንልህም" የሚለኝ ላብራራው የማልችለው ነገር በመኖሩ፣ የከረረ ጥብቅነት የነበረው የፒኤች.ዲ ትምህርት ታክሎበት በዚያ ውጥረት ለአንድ ዓመት ቆየሁ። ልጆቼ ትምህርት ለመጀመር ገና ልጆች ስለ ነበሩ፣ በተለይ በጋ ላይ ቀኑን ሙሉ ቤት ሲውሉ ማየቱ ለእኔ ትልቅ ጭንቀት ሆነብኝ። ከሥራ በመጣሁ ቍጥር እዚያ ጭብጥ ብለው ሳያቸው፣ "የእኔ

እምቦቃቅሎች፣ እስረኞች እንድትሆኑ እዚህ አመጣኋችሁ አይደል" በማለት ከሞላ ጎደል በየቀኑ ስጠይቃቸው፣ ወንዱ ልጄ አንደኛው ቀን ላይ፣ "አባቴ አትጨነቅ፣ ፀሐዩዋ ትወጣለች፣ አቧራው ይጠፋል፣ ሣሩም ይበቅልና እብቦ ያን ጊዜ ልንጫወት ወደ ሜዳ እንወጣለን" ሲል መለሰልኝ። በሕይወቴ ላይ ብዙ ነገር እየሆነብኝ ስለ ነበረ፣ ምንም እንኳን ባይሳካለትም ሊያጽናናኝ እየሞከረ እንደ ነበር አስተዋልኩ።

ምንም እንኳን የምንጠብቀው ነገር ባይሆንም፣ በሌላ ልጅ የባረከን ጌታ ትልቅ የሆነ እኛን የሚያስደንቅበት የልጅ ስጦታ ነበረው። ይህ ተቃርኗዊ ነገር ቢመስልም፣ በእነዚህ የተወሳሰቡ ሁኔታዎች ውስጥ ሌላ ልጅ ለማግኘት አላቀድንም ነበር። በሆነ መንገድ በሥነ-ተፈጥሯዊ መንገድ ያ እንዳይሆን የምንችለውን ሁሉ እያደረግን የነበርን ብንሆንም፣ አዜብ ራሷን እርጉዝ ሆና አገኘች። ጾታው ምንም ቢሆን ጌታን አመስግነን ስጦታውን ለመቀበል ወስነን ለሁለቱም ጾታዎች ሊሆን የሚችል ስም ለማግኘት ሞከርኩኝ። ያገኘሁት ያ ስም "ጸጋ" የሚለው ነበር፣ ስሙም ያው ሆነ።

የሆነ ነጥብ ላይ ስደርስ ወደ አገሬ መመለስ በሚለው ሐሳብ ፈጽሞ ተጥለቀለቅሁኝ። ቀናቱ በገፉ ቍጥር ሌላ ነገር ማሰብ እስከቸገር ድረስ የመመለሱ ሐሳብ የናኘ ሆነ። ለመመለስ ጽኑ የሆነ ውሳኔ አድርጌ ለትምህርት ክፍሌ፣ ለዓለም አቀፉ ኅብረት፣ እና ለሌሎች ዜናውን ለማወጅ ብርታት አገኘሁ። እድሜያቸው አራት እና ሦስት ዓመት የሆኑት ልጆቼ በአእምሮዬ ውስጥ እየሆነ ያለውን እና ወደ አገራቸው ልመልሳቸው እንደ ሆነ ባያውቁም፣ ለባለቤቴ ግን ውሳኔዬን ግልጽ አደረግሁላት።

ስለዚህ ውሳኔ ከእኔ ጋር አብረው የጸለዩ በርካታ ጓደኞች ነበሩኝ፣ በተለይ ከዓለም አቀፉ እና የአፍሪካ ኅብረታችን። እንደ ጂም ጌትዝ ካሉት ጋር ስለ ወደ ፊት ሁኔታዬ የጌታን ምሪት እየጠየቅን፣ በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ጌታን ለማገልገል አዳዲስ ዕድሎች እንዲከፈቱ ጸለይን። የእኔ ግልጽ የጸሎት ጥያቄ በአዲስ የሕይወት ጥሪ ወይም ሥራ ውስጥ እንደ አገልግሎት እንድገባ ለትርፍ ባልተቋቋመ ሰብዓዊ የክርስቲያን ድርጅት ውስጥ እንድሠራ ጌታ በሩን እንዲከፍትልኝ ነበር። የጥሪዬ ስሜት በዚያ ነጥብ ላይ ግልጽ ስላልነበረ በጠራ ሁኔታ ልለየው አልቻልኩም፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ካለችው ቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዘ ነገር እንደ ነበረው ግን ለቅንጣትም ጥርጥር አልነበረኝም።





መጋቢት 28 ቀን 1987 ዓ.ም ላይ ከቤተሰቤ፣ ከባለቤቴ፣ ከሦስቱ ልጆቼ እና ከራሴ ጋር ሚሺጋንን ለቅቀን ወጣን። ጸጋ ያን ጊዜ ሁለት ወር ዕድሜ ብቻ ነበረው። ከትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን ከፊል የቤተሰቡን የመጓጓዣ ወጪ ለመደገፍ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ አገኘሁ። ያን ጊዜ የሚሽን ዳይሬክተር የነበረውን ካሮል ዊልሰንን እንዲሁም ኢርቪን እና ሩሜሊያን ከዚህ አኳያ ለተጫወቱት ወሳኝ ሚና ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። ጂም፣ ዶን እና አበባን ጨምሮ በግላቸው መዋጮ ያደረጉትን ግለሰቦችንም አመሰግናለሁ።

በለንደን አድርገን ወደ አዲስ አበባ መጣንና የአዜብ ታናሽ እኅት በሆነችው ተናኜ እጅ አደራ ትተነው ወደ ነበረው አሮጌ አፓርታማችን ተመለስን። ወደ አፓርታማችን በደረስንበት ቅጽበት ውስጥ ያልተጠበቀ አጋጣሚ ተፈጠረ። በጉዞው ሁሉ ውስጥ ሲጫወት የነበረው ሳም ወደ አገሩ እንደ ተመለሰ፣ በማስተዋል ምርር ብሎ እያለቀሰ ወደ አፓርታማው ለመግባት አሻፈረኝ አለ። ምን እየተከናወነ እንደ ሆነ ያውቃል ብዬ ፈጽሞ አልገመትሁም ነበርና ያ ያልተጠበቀ አጋጣሚ ልቤን ሰበረው። ወይም ልጆቼ በአሜሪካ ውስጥ ካለው ሕይወት አንዳች ዓይነት ነገርን ይወዱታል ብዬ ለቅጽበትም አላሰብኩም ነበር። ማልቀሱን ቢቀጥልም፣ ወደ አፓርታማው እንዲገባ በሆነ መንገድ አሳመንነው። ምን ማድረግ እንዳለብኝ እስከማላውቅ ድረስ ይህ በጣም አስደንቆኛል።

ልጆቼ በአዲስ አበባ መቆየቱ ምቾት እንዲሰጣቸው ማድረጉ እና መንከባከቡ የእኔ ኃላፊነት ሆነና ቲቪ ከነዴኩ ገዝቼ ከአሜሪካ ያመጣናቸውን አንዳንድ ቪዲዮዎች እንዲመለከቱ አደረግሁኝ። ትልቅ ማቀዝቀዣ አምጥቼ አንዳንድ በብልቃጥ የተዘጋጁ ጭማቂዎችን ሞላሁባቸው፣ የውጭ ዜጎችን ከሚያስተናግዱ ልዩ ገበያ ማዕከላት ሴሪያሎችን ገዛሁላቸው። መጀመሪያ ላይ በአሜሪካ የተሠራ ሴሪያል ገዛሁላቸው፣ ከዚያም እነዚያ ውድ ሲሆኑብኝ፣ ኬኒያ ውስጥ ወደ ተመረቱት ዞርኩኝ።

እጅግ ትልቅ ጥረት የሚጠይቅ ሙከራዎችን ባደርግም፣ ሳምን ደስተኛ ላደርገው አልቻልኩም፣ ያም ደግሞ በእኔ በኩል አንዳች ዓይነት ጭንቀትን ፈጠረብኝ። ከላንሲንግ ጋር ሲወዳደር አዲስ አበባም እንዲሁ ጥሩ የሆኑ መገልገያዎች እንዳሏት ለማሳየት ወደ ዋቢ ሸበሌ እና ጊዮን ሆቴሎች ወሰድኳቸው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆናቸው ያጡት በጣም ትንሽ ነገር እንደ ሆነ ላረጋግጥላቸው የምችለውን ሁሉ ሞከርኩኝ፣ ከእኛ ጋር እንድትኖር እናቴን

ከሐረር ይጥት መጣሁ፣ እርሷም ብትሆን ሳምን ደስተኛ ለማድረግ የምትችለውን ሁሉ አደረገች፣ ነገር ግን ወደ አገሩ መመለሱን ለመቀበል ለእርሱ በጣም ረጅም ጊዜ ወሰደበት። አንዳንድ ጊዜ የሚያስደስቱት እንደ ኬኔዲ ያሉ በዚያው የአፓርታማ ቤቶች አጎራባች የሆኑ ሌሎችም ስለ ነበሩ አንድ ቀን ለሳም እንዲህ አልኩት፣ "አየህ አያትህ እኮ አለችህ፡፡ አዲሱ ጓደኛህ ኬኔዲ ደግሞ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ሕይወትን ደስ ልትሰኝባት ይገባል።" የእርሱ መልስ፣ "እኮ ሴሪያል ልትሆን ትችላለች? ኬኔዲ ጭማቂ ሊሆን ይችላል? አጥንቶች ሥጋ ሊሆኑ ይችላሉ?" ከዚያ ቀን ጀምሮ ሳምን እና ብዙም ግድ ያልሰጣት የምትመስለውን ሔሉን ማጽናናቱ የማይሠራ እንደ ሆነ ተገነዘብኩኝ። በእጅ ያለው ምርጥ አማራጭ ሕይወታቸውን ለጌታ በጸሎት አሳልፎ መስጠት ሆነ።

ከቤተሰቤ ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን አንድ አስደናቂ አጋጣሚ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ። አንድ ቀን፣ ልጆቼን ከባለቤቴ እንጀራ እናት ጋር ለእራት ወደ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ለመውሰድ ዐቀድኩኝ። ወደ ሥራ ከመሄዴ በፊት ባለው ማለዳ ላይ ከሥራ እንደ ተመለስኩ ወዲያውኑ እንድንሄድ ልጆቹን ታዘጋጅልኝ ዘንድ ለባለቤቴ ነገርኳት። ሆኖም ግን፣ በዚያ ቀን በቢሮዬ እያለሁ ለቅጽበት እንኳን የማያቋርጥ ያልተለመደ የራስ ምታት ሕመም ይንጠኝ ጀመር። ወደ ቤት ሄጄ የማስታገሻ መድኃኒቶች ወሰድኩኝና ወደ 9፡00 አካባቢ ተኝቼ ስነቃ ከምሽቱ 1፡00 እንደ ሆነ አስተዋልኩኝ። ባለቤቴ እና የእንጀራ እናቷ ወደተቀመጡበት ክፍል በፍጥነት አመራሁና እውነተኛ የሆነ ይቅርታ ጠየቅሁኝ። ከዚያም የረፈደ ቢሆንም ለእራት እንዲለባብሱ ሳጣድፋቸው እነርሱ ግን ከረፈደ ከመሄድ ይልቅ በቀጣዩ ቀን መሄድ እንደሚመርጡ እንጀራ እናቷ ጎተጎቱ። ላሳምናቸው የምችለውን ሁሉ አድርጌ ነገር ግን ምንም ጥቅም ስላልነበረው እራት ግብዣውን በሚቀጥለው ቀን ለማድረግ ወሰንን። እስከዚያም ቀን ድረስ እያመመኝ ስለ ነበር በሚቀጥለውም ቀን ሙሉውን ቀን ቤቴ ዋልኩኝና ምሽቱ ላይ ወደ ዋቢ ሸበሌ ታክሲ ይዘን ሄደን እቦታው ስንደርስ ወረድን። ወደ ሆቴሉ እየተራመድን እያለ፣ ወደ ውስጥ እንዳንዘልቅ ፖሊስ ሲያስቆመኝ ተደነቅሁኝና በምግብ ቤቱ ውስጥ እራት ልንበላ እንደ ሆነ ለአንደኛው ፖሊስ ነገርኩት። መልሱ አስደናቂ ነበር፣ "የምትኖሩት ከዓለም ውጪ ነው እንዴ? ትላንትና ምን እንደ ተፈጠረ አልሰማችሁም?" ሲል ስለ ምን እያወራ እንደ ሆነ ምንም ፍንጭ ሳይኖረኝ ወደ ኋላ ተገፍተን መለሱን። ኋላ ላይ መረጃ ሳሰባስብ ከሶማሊያ የመጡ እስላማዊ





አሸባሪዎች እራት ልንበላ በነበረበት ምሽት ላይ ሆቴሉ ውስጥ ፈንጂ ጠምደው እንደ ነበረ ሰማሁ። የሚያስደንቀው ነገር ብዙ ሰዎችን የገደለው ፍንዳታ ተከስቶ የነበረው ምሽት 1፡00 አካባቢ መሆኑ ነበር። ነገሮች እንዳቀድናቸው ቀደም ባለው ቀን ተከናውነው ቢሆን ኖሮ፣ ቤተሰቡ - በተለይም ሕጻናቱ በከፉ አደጋ ውስጥ ይሆኑ ነበር ማለት ነው። "ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" (ሮሜ 8፡28) የሚሉት ዓይነት አነጋገሮች የእውነት ትርጉም የሚሰጡት አንድ ሰው በእንዲያ ያለ እውነተኛ የሕይወት ተሞክሮ ውስጥ ሲያልፍ ነው። ደስተኛ እንዲሆኑ ለማድረግ ስል ሕጻናቱን ወደ ምግብ ቤቶች በወሰድኳቸው ጊዜ ሁሉ ልጆቼ በቀዥቃዣ ባሕርያቸው፣ እና አንድ ቦታ ረግተው ባለመቀመጣቸው ይታወቃሉ። በአብዛኛው በሆቴሉ ክፍሎች ዙሪያ እየሮጡ ዝም ብለው ዙሪያ ገባውን ይዞሩ ስለ ነበር፣ የጥቃቱ ሰለባ ሊሆኑ ይችሉ እንደ ነበረ ግልጽ ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩኝ በኋላ በአዲሱ ሕይወቴ ላይ ትልቁ ጉዳይ የሥራ ጉዳይ ነበር። በ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ከሆነ በኋላ በከፍተኛ ትምህርት ባለ ሥልጣናት ኮሚሽን መኮንንኖች እንድሸጋገር የተደረግሁበት ኮሌጅ፣ ማለትም የኮተቤ መምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራዬ መልሶኛል። ያ ያለ ምንም ጥርጥር የዋስትና ስሜትን ሰጥቶኛል። ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሴ ቀደም ብሎ በላንሲንግ ሳለሁ፣ በክርስቲያን ድርጅት ውስጥ እንድሠራ አዲስ ዕድሎችን እንዲከፍትልኝ እግዚአብሔርን ጠይቄው ነበርና ከኮሌጁ የቀረበልኝን የሥራ ዕድል ወዲያውኑ ላለመቀበል ቆረጥኩ። ከዚያ ይልቅ፣ ወደ ተወሰኑ ቦታዎች ማመልከት ጀመርኩኝ። አንደኛው ኮምፓሽን ኢንተርናሽናል ሲሆን፣ ዳይሬክተሩ ጋሽ ሽፈራው ከሚፈለገው የትምህርትና የሥራ ልምድ በላይ እንደ ሆንኩኝ ስለ ነገረኝ ድርጅቱ ለእኔ የሚሆን የሥራ ቦታ አልነበረውም። ያመለከትኩበት ቀጣዩ ድርጅት ወርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል/ኢትዮጵያ ነበር። ብሔራዊ ዳይሬክተሩን ሙሉርን የማውቀው ሰው ሆኖ አገኘሁት። አዲስ የምርምር ቢሮ እየከፈቱ እና የአስተዳደር ቡድኑ አስተባባሪ የሚሆን ሰውን በጸሎት እያፈላለጉ ባሉበት በዚያው ሰዓት ላይ እኔ ስላመለከትኩበት አጋጣሚ እጅግ ሲበዛ ተደነቀ።

በዚያው ሳምንት ውስጥ ቃለ መጠይቅ ተደረገልኝና ሥራው ተሰጠኝ። እግዚአብሔር ጸሎቴን አክብሮ ለቤተሰቡ መተዳደሪያ የሚሆን እርሱንም

የማገለግልበትን አዲስ የዕድል መስኮትን እንደ ከፈተልኝ አመንኩኝ። ምንም እንኳን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ የሚንቀሳቀሱበት ድባብ ከትምህርቱ ዓለም የተለየ ቢሆንም፣ ስለዚያ እያንዳንዱን ነገር ለመማር ወሰንኩኝ። የመሥሪያ ቤቱን የምርምር ቢሮ ከባዶ ማደራጀት፣ ቢሮውን ለመምራት የጽንሰ-ሐሳብ ወረቀት ማዘጋጀት፣ የጥሪት ማዕከል ማደራጀት እና ጎን ለጎን ደግሞ በአስተዳደር ቢሮው እንደ ተጠየቅሁት አድርጌ ሌሎች ነገሮችን መሥራት ነበረብኝ። በተጨማሪም፣ በአብዛኛው ኤዲፒ (ADP) ተብለው በቅጽል ስማቸው የሚታወቁትን በርካታ የአካባቢ ልማት ፕሮግራሞች መጎብኘት ነበረብኝ።

የወርልድ ቪዥን ሠራተኞች በአመዛኙ የተለያዩ ቤተ እምነቶችን ከሚወክሉ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ቡድን የሆኑ ክርስቲያኖች በመሆናቸው፣ በበርካታ ብርቱ ክርስቲያኖች መካከል በመሆኔ ተባርኬያለሁ። አንዳንዶቹ የየቤተ ክርስቲያኖቻቸው ሽማግሌዎች ስለ ነበሩ፣ ራሳቸውንም ወዲያውኑ ለአዲስ የሥራ ባልደረባ የማይከፍቱ ሰዎችም መኖራቸው ግልጽ ነበር። በጥብቅ የተሳሰሩ ማኅበረሰቦች በመሆናቸው፣ መጀመሪያ ላይ በጥሩ ሁኔታ መዋሃዱን ከባድ ሆኖ አገኘሁት። ነገር ግን፣ እነዚሁ ሰዎች አንድ ጊዜ ካወቋችሁ እናንተን ለማስተናገድ በጣም ክፍት ናቸው።

በዛው ጊዜ ላይ የቤተ ክርስቲያኔ (አማኑኤል ባፕቲስት) ሽማግሌዎች ከሚሆኑት ጋር አንደኛው ሆኜ ተመረጥኩኝ። በተመለስኩበት ጊዜ ላይ ቤተ ክርስቲያኔ በአመራር ቀውስ ውስጥ አልፋ የነበረ መሆኑ እና በአንዳች ዓይነት መልሶ የማደራጀት ሂደት ውስጥ የነበረች መሆኑ ያስደንቃል። በእርግጥ፣ የቀድሞዎቹ የቦርድ አባላት ሥራቸውን ጨርሰው ለአዳዲስ ሽማግሌዎች የምርጫ ሂደቱን የሚያስተባብር ኮሚቴ በሥራ ላይ ነበር። ሽማግሌ እንድሆን የተጠቆምኩት በአበረ አማካኝነት ሲሆን፣ ለዚያ ስፍራ እንደማልመጥን ተሰምቶኝ፣ ደግሞም ለማቆም እያሰብኩ ሳለሁ ጌታን በየትኛውም ቦታ፣ በየትኛውም አቅም እና እርሱ በሚከፍተው የትኛውም በር ላገለግለው በሙሉ ልቤ ቃል ገብቼ እንደ ነበር ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቴ በፊት የገባሁትን ቃል አስታወስኩኝ። በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ ማጽዳት ወይም በአንድ ጥግ ውስጥ መጸለይ እንኳን ቢሆን በየትኛውም ደረጃ ላለ የአገልግሎት በር ዕድል እንዲሰጠኝ ጌታን መጠየቄንም አስታወስኩኝ። ያ በአእምሮዬ ሳለ ነበር ወደ





ዕጩዎች ዝርዝር ውስጥ በመግባት ኮሚቴው ተመራጮችን አጣርቶ ከሃያ በላይ የምንሆነውን የመረጠው። ከዚያ በኋላ፣ በአንደኛው እሑድ ላይ እያንዳንዳችንን ለማኅበረ-ምእመናኑ አስተዋወቁንና ዲሞክራሲያዊ በሆነ አካሄድ ምርጫው ተካሂዶ ስምንት ሰዎች ተመረጥን።

በደንብ የሚታወቀው ነገር ወደ አሜሪካ ከመሄዴ በፊት እንኳን ለተወሰነ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለመኖሬ ሲሆን፣ ወደ አሜሪካም ሄጄ የቆየሁበት ጊዜ በመኖሩ ለመመረጥ የሚኖረኝ ዕድል ጠባብ መሆን ነበረበት። ሁሉም ነገሮች በአዎንታ ከግምት ውስጥ ገብተው፣ እግዚአብሔር የገባሁትን ቃል ስላከበረ፣ የመመረጤ ሁኔታ ጉድለቶቼን ችላ ብሎ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ ነገር ሆነ። እርሱም ከለመንኩበት በላይ እና በሚልቅ ጸሎቴን መለሰልኝ።

እንዲሁም ደግሞ፣ ከሞላ ጎደል ቆሞ ነበር ሊባልለት የሚችለውን የሐረሪዎች ኅብረት መልሼ አቋቋምኩት። በአፓርታማዬ ውስጥ ኅብረት ማድረጉን ስንቀጥል፣ ጌታም አባላቶቻችንን በፍጥነት አበዛልን። በዚህ ጊዜ፣ ከአደሬ የሙስሊም ቤተሰብ ወደ ጌታ የመጡትና ከፉለር ሴሚናሪ የተመረቁት እንደ ዶ/ር ቢንያሚን ያሉ አዳዲስ ሰዎች ተቀላቀሉን። ኅብረቱን የሚመሩ ጠንካራ ኮሚቴዎችን ካቆምን በኋላ፣ ስም ሰጥተነው እንደ ሚኒስትሪ እንዲንቀሳቀስ ፈለግን። የሚያሳዝነው፣ እንዲያንቀሳቅሱት ተመርጠው ከነበሩት ውስጥ ስለ ኅብረቱ የወደፊት አቅጣጫ ሙሉ መስማማት አልነበረም። ዶ/ር ቢንያሚን ሐረሪዎችን ለመድረስ ያለመ ቀለል ያለ ወንጌል ስርጭት-ነክ የሐረሮች ኅብረት እንዲሆን ፈለገ። የእርሱ ዓላማ ትንሽ ሆኖ በመጀመር የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በራሱ አካሄድ ትልቅ እየሆነ እንዲሄድ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ጌች እና ዳኒ ኅብረቱ የአፍሪካ ቀንድን የመድረስ ዓይነት ትልቅ ዓላማ እንዲያሳካ ፈለጉ። ልዩነቱ የተፈጠረው በኅብረቱ የምሥረታ እርከን ላይ መሆኑ ያሳዝናል። እኔ በሁለቱ መካከል ብወጠርም፣ የወንጌል ስርጭት አድማሳችን ሶማሊያ እና ጅቡቲን ሊያካትት ስለ ሆነ ትልቁን ሐሳብ ወደድኩት፣ ነገር ግን ያ እናሳካው ዘንድ በጣም የሚበዛብን ትልቅ ራእይ ነበር። አነስተኛው ዕቅድ ፍሬ እያፈራ ሲሄድ እያየነው ስለ ነበረ ተግባራዊ ደግሞም የሚሻል ሐሳብ ሆነ። ወደ ጌታ የሚመጡ አያሌ የሐረሪ ወዳጆች ነበሩን፣ ደግሞም አብዛኞቻችን በተመሳሳይ የትምህርት እና መንፈሳዊ ተፈጥሮ ውስጥ ያለን የዩኒቨርስቲ

ምሩቃን እንደ መሆናችን አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ሆነን በአንድነት እንድናድግ ሲረዳን ቆየ።

ብዙም ሳይዘልቅ፣ ልዩነቶቹ ወደ ትልልቅ ጭቅጭቆች ያመሩ ጀመር። በሁለቱ አቋሞች መካከል በመሆን ሳስታርቃቸው የምችለውን ሁሉ ባደርግም፣ እንዳያደርገው እየለመንኩት ዶ/ር ቢንያምን ከኮሚቴ አባልነቱ ለቀቀና ኅብረቱን ትቶ ሄደ። የትልቅ ልምድ እና ጥሪቶች ሰው በመሆኑ የእርሱ መልቀቅ ለኅብረቱ ትልቅ ጉዳት ሊሆን ቻለ።

ኅብረቱ ማደጉን ስለ ቀጠለ፣ ተጨማሪ ሰዎችን የሚይዝ ሌላ ቦታ አስፈለገን። ከዚያም ሌላ፣ የእኔ ቤት በሌሎች ቤቶች መካከል የምትገኝ አንድ ቤት በመሆኗ እና በቤታችን ውስጥ በሚደረገው አምልኮ በተለይም በዝማሬው የሚረበሹ ጎረቤቶች በመኖራቸው አፓርታማዬ ነጻ እና ዘና ያለ አምልኮን ለማካሄድ አመቺ አልነበረም። ውድ እኅታችን በላይ ከጉርሱም የመጣች ስትሆን ያን ጊዜ በካዛንቺስ አካባቢ ከወላጆቿ ጋር ስለምትኖር፣ ቤቷን ለኅብረቱ ሰጠችና የጸሎት አገልግሎትን ለኅብረቱ ጨመርንበት። በእያንዳንዱ ሐሙስ ምሽት ለመላው የአፍሪካ ቀንድ ክልሎች ለመጸለይ መገናኘታችንንም ቀጠልን።

በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ የነበረኝ ሥራ ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ኅብረት መሪዎች ጋር ያገናኘኝ ጀመር። ጌታ በትልቅ ኅብረት ላይም እንዳገለግል ሌላኛውን ዕድል ከፈተልኝ። መጋቢ አሳየኸኝ የወንጌል ተልዕኮ እና የወንጌል ስርጭት ኮሚሽን በሆነው በፋሚሊ ላይፍ ኮሚሽን ላይ እንዳገለግል ጋብዞኝ በደስታ አገለገልኳቸው። የትኛውንም ዘላቂ የሆነ ቅርስ ትቼ ለመሄድ ጊዜ አላገኘሁም እንጂ፣ በኢትዮጵያ ያለችውን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ትልቁን ሥዕል ለማስተዋል ችያለሁ።

እንደ ሽማግሌ ሆኜ በማገለግልባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጌታ አገልግሎቴን ባረከልኝ። ምንም እንኳን በሕዝብ ፊት ቆሞ የመስበክ ልምድ ያልነበረኝ ብሆንም፣ ሽማግሌ የመሆን አንደኛው ኃላፊነት የአልፎ አልፎ ስብከት ማድረግ እንደ ሆነ ተነግሮኝ ነበርና አንድ ጊዜ በእሑድ አምልኮ ላይ እንድሰብክ ተጠየቅሁ። እንደ እግዚአብሔር አንደበት በመሆን ምስባክ ላይ መቆም ትልቅ ኃላፊነት ስለ ሆነ፣ ጥሪውን መቀበል ለእኔ ከባድ እስኪሆን ድረስ የሰባኪነትን ጥሪ የማየው በጣም ትልቅ ጥሪ አድርጌ ነው። ስለ ሰባኪነቴ ጸለይኩበትና ለመጀመሪያው ስብከት ሰፋ ያለ ዝግጅት አደረግሁኝ። ይህም ስብከት





በመዝሙር 46፡10 - "ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፤" ላይ አተኮረ። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንድሰብክ በተጋበዝኩበት በሚቀጥለው ጊዜ መልእክቴን ያቀረብኩት የግጥም መልክ ባለው ርእስ ሥር ነበር። "የእነሆኝ መጨረሻ እግዚአብሔር በቃ ሲል ነው።" መልእክቱም በዋናነት ያተኮረው በዘፍጥረት 22፡12 ላይ ነበር። ተጨማሪ ብርታቶችን ባገኝሁ ቍጥር፣ በተመረጡ ስልታዊ ርእሶች ላይ ተዘጋጅቼ የእሑድ አምልኮ ዝግጅቶች ላይ ተከታታይ ትምህርቶችን ማስተማሬን ቀጠልኩ። የማኅበረ-ምእመናኑን ፍላጎቶች ከገመገምኩኝ በኋላ ርእሶችን እመርጣለሁ። ባላደራነት የሚለው ርእስ ከሦስት ተከታታይ ሳምንታት በላይ የሰበኩበት ታዋቂ እና ጠቃሚ ከነበሩት ርእሶች አንደኛው እንደ ነበር ሰምቻለሁ። በማስተማር ቢሆን በመስበክ ደረጃ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ማገልገሌ ክብር እና ትልቅ በረከት ሆኖልኝ ነበር።

## *የወርልድ ቪዥን ተሞክሮዬ*

በወርልድ ቪዥን ውስጥ ለአራት ዓመት ግድም እንደ ጥናትና ምርምር አስተባባሪ እንዲሁም የሥልጠና መኮንን ሆኜ ሠርቻለሁ። በሁለተኛው ሹመቴ ውስጥ የነበረው ተግባሬ በምሕጻረ ቃል ኤዲኤስ (ADS) "አክሬዲትድ ዴቨሎፕመንት ስተዲስ" (እውቅና የተሰጠው የልማት ትምህርት) የተባለውን የሁለተኛ ዲግሪ መርሐ-ግብር ማስተባበር ነበር። ኤዲኤስ በዋናነት የኤዲፐ ሥራ አስኪያጆችን የሚያሠለጥን መርሐ-ግብር ሲሆን፣ ይህም ከነገረ-መለኮት ትምህርት ጋር ለተጠላለፈ የልማት ትምህርት መስክ የሚበቁ ሆነው እንዲገኙ የሚያደርጋቸው ነበር። መርሐ-ግብሩ ከኦክስፎርድ ሴንተር ፎር ሚሽን ስተዲስ (ኦሲኤምኤስ/OCMS) ጋር የተጣመረ ጥናት ሆኖ በውጤታማ ሁኔታ መርሐ-ግብሩን እንዳስተዳድረው በኦሲኤምኤስ እና በፉለር ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ ውስጥ ከመርሐ-ግብሩ ጋር በተገናኘ ጥቂት የሥልጠና ዕድሎችን አግኝቼበታለሁ። የሥራ መስኬ ወርልድ ቪዥንን ከትምህርት ዓለም ጋር፣ በዋናነትም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር እንዳገናኝ ጥቂት ሰፋ ያለ ዕድልን ስለ ሰጠኝ፣ ዘለቄታዊነት ያለው ልማት፣ የምርምር ዘዴዎች፣ የአገርኛ እውቀት፣ እና የሠራተኞችን አቅማስ የሚያሰፉ በርካታ ርእሶች ላይ የሚናገሩ ፕሮፌሰሮችን በመጋበዝ ተከታታይ የሆኑ የመድረክ ውይይቶችን አዘጋጅቻለሁ። ምንም

እንኳን ይሄኛው ሥራ መምህራኑ ከአንዳይነት የወንጌላውያን ዳራ የመጡ ሊሆኑ ይገባል የሚል ጉትጎታ ከነበረው ከቅርብ አለቆቼ በአንደኛው ያልተወደደልኝ ቢሆንም፣ በትምህርት ዓለም ካላቸው በጎ ስም አንጻር ከዚያው የመጡ አስተማሪዎችን መለመልኩኝ።

ዚ ዌይ (መንገዱ) በሚል ርእስ ሥር ለድርጅቱ የልማት ትምህርት ላይ ያተኮረ ትምህርታዊ መጽሔት ለመመሥረት ፈለግሁኝ። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ የአርታኢያን እና አማካሪ ቦርድ በመሆን የሚደራጁ ሰዎችን ለማግኘት ብዙ ሥቃይ አየሁ። ውጥን-ሥራውን ሥራ ለማስጀመር ጥቂት ቀርቶኝ ሳለሁ፣ ከአስተዳደሩ ዘንድ ትምህርታዊ መጽሔቱ ሲበዛ ትምህርታዊ ሆነ የሚለውን አስተያየት ተቀበልኩ። በዚያ ላይ ደግሞ፣ የገንዘብ ጉዳይ እንደ መቀጣጫ ትምህርት የነበረ አንዱ ችግር ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ ውጥን-ሥራው የድጋፍ እጥረት ስለ ነበረበት ብዙም ሳይገፋ ተቋረጠ።

በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ መሥራቴ አስደስቶኛል። የስም ዝርዝራቸውን እዚህ ማካተቱ በጣም ብዙ ይሆናል እንጂ፣ ከብዙ ሰዎች ጋር ዘላቂ የሆነ ጓደኝነቶችን አዳብሬያለሁ። ብሔራዊ ዳይሬክተሩን ሙለርን በጣም ብሩህ ጭንቅላት ያለው፣ ብርቱ ጉልበት ያለው፣ እና የራእይ ሰው ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እርሱ ሁልጊዜ ከብዙዎቻችን ቀድሞ የሚያስብ ሰው በመሆኑ፣ ለድርጅቱ ያለውን ራእይ እንዲያሳካ የምሬን ተመኝቼለት አውቃለሁ። መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሥራ ድባብ ጋር ለመላመድ የምችለውን ሁሉ አድርጌ ነበርና በሂደቱ ውስጥ ብዙ ተማርኩኝ። በውጤቱም፣ አብዮተኞች በነበርን ጊዜ "ሰፊው ሕዝብ" ብለን እንጠራው ስለ ነበረው ቡድን እውነተኛ ሁኔታዎች ብዙ እንድማር ያስቻለ ከትምህርት ዓለም ካለው የተለየ ረጅም ተለዋጭ መንገድ ሰጠኝ። እነርሱም በገጠራማ አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ በድህነት የተመቱና ወርልድ ቪዥን በወሳኝ መልኩ ዕጣ ፈንታቸውን ሊያሻሽልላቸው የሚጣጣርላቸው ነበሩ። ወርልድ ቪዥን አጋዥ የሆኑ ተግባራዊ ሥራዎችን በምሳሌያዊ ድርጅትነት ለማከናወን እየሞከረ ስላለበት ስለ ሁለንተናዊ አገልግሎት ብዙ ተማርኩኝ። በበርካታ ዓይነን በሚያበሩ የሥልጠና ዝግጅቶች እና ዓውደ-ጥናቶች ውስጥ ከመሳተፌ ጎን ለጎን ሥልጠናና ዓውደ-ጥናቶች ከቦርዱ በተሻገረ የምጣኔ-ሐብት፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ መንፈሳዊና የመሳሰሉትን ለውጦች ከሚያስተዋውቁ ሰብዓዊ ድርጅቶች ጋር ለመሥራት እንድላመድ





አድርገውኛል። ከሁሉም በላይ፣ ከበሰሉ እና እግዚአብሔርን ከሚወዱ ክርስቲያኖች ጋር መቀላቀሉ እና መገናኘቱ በእምነቴ ጥልቀት ሥር እንድሰድድ እና ጌታንም በተሰጠ ሕይወት እንዳገለግል በር ከፍቶልኛል። ሥራ ከመጀመሩ በፊት በእያንዳንዱ ቀን የሚካሄደው የማለዳ ጥሞና ጊዜ የበለጸገ ይዘት አለው (እንደ ጸሎት፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማድመጥ እና ምስክርነቶችን መከፋፈል ያለ)፣ ደግሞም በመንፈሳዊ ከፍታ ላይ አስቀምጦኛል።

ነገር ግን ያኔም እንኳን፣ በጥሪዬ ላይ የበለጠ ተጨባጭ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ የሆነ ቦታ ላይ ይሰማኝ ነበር። ወደ አሜሪካ ከመመለሴ በፊት ለራሴም እንኳን ይህንን የተቀበልኩት በችግር ቢሆንም ሁኔታውን በመረዳቴ አሰብኩበት። ለተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ጥያቄ እና ጫናዎች ተገዢ ሆኖ በዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ መሥራቱ ጭነትን የሚያሸክም ኃላፊነት ሲሆን፣ በዛ ውስጥ የሁሉም ንግዶች ከሪከ እና ማናቸውንም ግን ያልተቆጣጠረ የሆንኩ ያክል ራሴን አግኝቼዋለሁ። ከእኔ በኋላ ድርጅቱን የተቀላቀለችውና አሁን በሕይወት የሌለችው በጾታ እና ልማት ክፍል ላይ ኃላፊ የነበረችው ጽዮንም እንዲሁ ይሰማት እንደ ነበር አጫውታኛለች። አንድ ጊዜ በቀልድ ስትናገር፣ "አሁንስ አዝማሪ አደረጉኝ እንዴ?"[51] ማለቷን አስታውሳለሁ።

ምንም እንኳን በፍጻሜ ሥራ ላይ ባይውሉም፣ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ሳለሁ ነበር ሁለት የአገልግሎት ዕድሎች የመጡት። በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዋና ጸሐፊ በነበሩት በመጋቢ አሳየኸኝ ኅብረቱን ለማጠናከር አብሬው እንድሠራ ተጠየቅሁ። ያን ጊዜ እርሱ፣ በርካታ መምሪያዎችን እና ኮሚሽኖችን በመመሥረት በጣም አዎንታዊ በሆነ አቅጣጫ መልሶ ሊያደራጀው በመሞከር ላይ ነበር። መጋቢ አሳየኸኝን በርቀት አውቀዋለሁ፣ ነገር ግን፣ ሁለታችንም በኦክስፎርድ ሴንተር ፎር ሚሽን ስተዲስ (ኦሲኤምኤስ) የተደራጀውን የሦስት ሳምንታት ዐውደ ጥናትን ኦክስፎርድ ውስጥ እንወስድ የነበረ ጊዜ የቅርብ ግንኙነትን ለማዳበር ቻልን። ጥሪውን ለመቀበል ፈቃደኛ ነበርኩኝ፣ ነገር ግን ባለቤቴ ለዚህ የሰጠችው ምላሽ ቀዝቃዛ ሆነ። በእርግጥ ደመወዙ ትንሽ ነበር፣ ደግሞም ምንም የጤና እና የመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች አልነበሩትም። እኔ ሐሳባዊ ስሆን እርሷ ደግሞ በአንጻሩ በጣም ተግባራዊ በመሆኗ፣ እንዲሁም ቤቱን ታስተዳድር ስለ ነበረ፣ ከቁሳዊ ነገሩ አንጻር ከግምት ሳታስገባው አልቀረችም። ከዚህም ሌላ፣ እንቅስቃሴ ከማድረጌ

በፊት ኮስተር ያለ የግራ ቀኝ ምልከታ እንዳደርግ ይመክሩኝ የነበሩ ጓደኞችም ነበሩኝና በተከፋፈለ ልብ ሆኜ ሐሳቡን ተውኩት።

ቀጣዩ ዕድል አሜሪካ በነበርኩኝ ጊዜ ከማመልከባት ከትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን የመጣ ሲሆን፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ፣ በተለይም ከአመራሮቹ ከመጋቢ ኤመርሰን እና ከወንጌል ተልዕኮ አገልግሎት ዳይሬክተሩ ስቲቭ ዋለን፣ ጋር ግንኙነት ነበረኝ። በወቅቱ፣ ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በሚስፋፋ መልኩ ቅርንጫፎችን የሚከፍትና አዲስ አበባ ውስጥ ዋና ቢሮ የሚኖረው ሁለ-ገብ የክርስቲያን ወጣቶች ማዕከልን የመክፈት ራእይ ነበረኝ። በጥቅሉ፣ ዕቅዱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው መጥተው ዘና ሊሉበት፣ ወንጌላውያን መጥተው ሊታደሱበት እና ልጆቻቸው መጥተው ደስ ሊሰኙበት የሚችሉበትን ማዕከል መክፈት ነበር። ማዕከሉ በተለይ ዒላማ ያደረገው ወጣቶችን ሲሆን፣ ማዕከሉ የቪዲዮ እና ቤተ መጻሕፍት ክፍሎች ፍላጎታቸውን የሚያሟላ እንዲሆን ተነድፏል። የማዕከሉ ሌሎች ገጽታዎች ካፍቴሪያ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ እና የመሳሰሉትን ጭምር ይዟል። 1989 ዓ.ም ላይ ለሥልጠና ወደ ፉለር ሴሚናሪ ስሄድ ወደ ምሥራቅ ላንሲንግ ተለዋጭ መንገድ ወስጄ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪዎች በማግኘት በልቤ የነበረውን አካፈልኳቸውና የቀረውን ዝርዝር ራእይ በመጻጻፍ ለመጋቢው አካፈልኩት። እነርሱ ሐሳቡን ደግፈው ካበረታቱኝ በኋላ ከእኔ ጋር እንደሚቆሙ ተስፋ ስለ ሰጡኝ፣ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ከትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መገናኘቱን ገፋሁበት።

በወቅቱ የማዕከሉ መመሥረት በፊቴ እንዳለ ሆኖ ጌታን ለማገልገል ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ለመግባት የምወስን ከሆነ፣ የትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን ለእኔ እና ለቤተሰቤ የገንዘብ ድጋፍ ልታደርግልኝ ትችል እንደ ሆነ ጠይቄ ነበር። ጥያቄዬ ተቀባይነት አገኘና አብሬያቸው በጥምረት የምሠራባቸው ክርስቲያናዊ ድርጅቶችን እንዳፈላልግ ተጠየቅሁኝ። በጊዜው፣ ሁለት አማራጮችን ከግምት ያስገባሁ ሲሆን፣ አንደኛው ብሔራዊ ዳይሬክተሩን ማቴዎስን ለማገዝ በከፍተኛ ሁኔታ እሳተፍበት የነበረው የክርስቲያን ንግድ ሥራ ሰዎች ኮሚቴ (ሲቢኤምሲ/ CBMC) እና ሌላኛው ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ረጅም ታሪክ የነበረው ዩዝ ፎር ክራይስት (ወጣት ለክርስቶስ) የሚባለው ድርጅት ነበሩ። ምንም እንኳን ከማቴዎስ ጋር ጥሩ ትውውቅ የነበረን እና ከእርሱ ጋር ለመሥራት ምቾት የሚሰማኝ ቢሆንም፣ አንዳንድ መርሐ-ግብሮቻቸው ላቋቋመው ተስፋ





ከማደርገው ማዕከል ራእይ ጋር አብሮ የሚሄዱ ስለ ነበረ ልቤ ወደ ዩዝ ፎር ክራይስት አዘነበለ። እንዳልከን ከዚያም ብሔራዊ ዳይሬክተሩን እና የቦርድ አባላቱን አገኘሁና ሐሳቡን ከእነርሱ ጋር ተነጋገርኩኝ፤ ደግሞም ሁሉም ነገር ጥሩ የሚሄድ መሰለ። ለሙሉ ጊዜ አገልግሎቱ የዝግጅት አካል እንዲሆን ያገለገለች ቮልስዋገን መኪና ገዝቼ ራሴን ወደዚህ አገልግሎት ለማስገባት ዝግጁ ሆንኩኝ። በዚህ መሃል አንድ ነገር ወደ ብርሃን መጣ።

በ1989 ዓ.ም በሐጋይ ኢንስቲትዩት ውስጥ የአመራር ሥልጠና ለአንድ ወር ለመውሰድ ስሄድ ኢንስቲትዩቱ የጉዞ እና የማረፊያ ወጪዎቼን፣ ትሪኒቲዎች ደግሞ የምዝገባ ወጪዬን ሸፈኑልኝ። ያንን አስደናቂ የአመራር ሥልጠና እንድወስድ ጌታ ስለ ሰጠኝ አስደናቂ ዕድል አመሰግነዋለሁ። በክርስቲያን እምነት እና የቤተ ክርስቲያን አመራር ጉዳይ ላይ ከተገኙባቸው ምርጥ ሆነው ከተደራጁ እና በውጤታማ ሁኔታ ከተካሄዱ ዝግጅቶች አንደኛው ያ ሲሆን፣ ከምላ ጎደል ከሁሉም ዓለም ከመጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር እንድገናኝ እና እንድግባባ ዕድል ሰጥቶኛል። በተለያዩ ርእሶች ላይ ከነገረ-መለኮት አዋቂዎች እና ክርስቲያን ምሁራን ስላገኘሁት ትምህርት በእጅጉ ተደንቄያለሁ።

ወደ አገሬ ስመለስ ሚሺጋን ካለው የትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው 'በል ቀጥል' የምትለውን መግለጫ እየተጠባበቅሁ ነበር። ለወራት ያክል ስላስጠበቁኝ መዘግየታቸው ማብራሪያ ሊሰጠው የማይችል ሆኖ አገኘሁት። ተሳስቼም ይሁን ልክም ልሁን ብቻ በውስጤ ብዙ ገፋፍቼያቸውና ከእነርሱም ብዙ ጠይቄያቸው ሊሆን እንደሚችል ገባኝ። መዘግየታቸው በረዘመ ቍጥር የበለጠ ልክ እንደ ሆኑ ይሰማኝ ጀመር። ከዚያም፣ ይህ ሐሳብ "ምናልባት ከእግዚአብሔር ይልቅ የራሴን አጀንዳ በጣም እየገፋሁበት ይሆናል" ወደሚል ሌላ ሐሳብ ተለወጠ። አእምሮዬን የነካው ሌላው ሐሳብ ምናልባት ትሪኒቲ በእኔ እና ላካሂደው ባለው ውጥን ሥራው ላይ በቂ የሚባል እምነት አልጣለም ማለት ነው የሚል ሲሆን፣ እስከ ዛሬ ድረስ ያሰብኩት ልክ የነበረ ይሁን ወይም አይሁን እርግጠኛ አይደለሁም፤ እግዚአብሔር ብቻ ያውቃል። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ ሳለሁ ነበር ሕይወቴ አዲስ አቅጣጫን የተከተለው።

የቀድሞ አማካሪዬ ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ከሚሺጋን ስቴት ዩኒቨርስቲ የመምጣታቸውን ዜና ሰማሁ። ከአሜሪካ ከተመለስኩኝ ወዲህ ፕሮፌሰሬ በእኔ ተቆጥቶ እና የትኛውንም መልእክቴንም

ሆነ የሰላምታ ካርዶቼን መልስ ሰጥቶባቸው አያውቅም ነበር። የእውነት በእኔ የሚያምን የነበረ ደግ ሰው ስለ ነበረ፣ የእኔን ስኬታማነት ይፈልገው ነበር። በኤምኤስዩ ውስጥ እኔ የእርሱ ተማሪ በመሆኔ ሁልጊዜም ይኮራ የነበረ ሲሆን፣ መርሐ-ግብሩን ማቋረጤ እና ወደ ኢትዮጵያ መመለሴ ከፉኛ ተስፋ አስቆርጦት ሳለ፣ አንድ ሌሊት ላይ ቤተሰቤ እና እኔ ሆቴሉ ድረስ ሄደን ልንጎበኘው ደፈርን። እኔን ስላየኝ ተደንቆ በድንገተኛ መገኘቴ የተቀላቀሉ ስሜቶችን አሳየንና አስፈሪ ከነበሩ ጥቂት ቅጽበቶች በኋላ ስላለሁበት ሁኔታ መነጋገር ጀመርን። በዚያን ጊዜ የት መሄድ እንደምፈልግ በትክከል የማላውቅበት እና ለመወሰን የተቸገርኩበት ሁኔታ ውስጥ ገብቼ ከእርሱ ክፍል ስንወጣ እርሱ እና እንግሊዛዊ ጓደኛው ከሬሲዳ ሸኙን። እርሱም የእኔ እና እርሱ ግንኙነት የፒኤች.ዲ ጥናቴን በኤምኤስዩ ካላጠናቀቅሁ ትርጉም-አልባ እንደ ሆነ በድንገት አስታወቀኝና ያንን ማድረግ እፈልግ እንደ ሆነ ጠየቀኝ። እኔም፣ ቀደም ብዬ ያሰብኩበትና በሚገባ ያሰላሰልሁበት መልስ ባይሆንም፣ በሚያነቃቃው ቅጽበት ውስጥ መማር እንደምፈልግ ነገርኩት። "እርግጠኛ ነህ?" ሲለኝ፣ እኔም "አዎን" ብዬ በመለስኩለት ቅጽበት ውስጥ፣ "ሳትጨርስ እንደማትመለስ ቃል ትገባልኛለህ?" የሚለው ጥያቄው ተከተለ፤ ቃል ገባሁለት። ባለቤቴን ጨምሮ ሁላችንም በተደነቅንበት መልኩ ውይይታችን እዚያ ላይ አበቃ፣ ስምምነቱም አለቀ፤ ተለያየን።

ከዚያም ባለቤቴ "የምርህን ነው ወይስ እንዲያው ስትቀልድ?" ብላ ስትጠይቀኝ መጨረሻ ላይ የሄደውን ዓይነት ያንን ውይይት ለማድረግ ዕቅድ እንዳልነበረ፣ ግን ወደ ኤምኤስዩ ለመመለስ እና ፒኤች.ዲ ጥናቴን ለማጠናቀቅ ቃሌን እንደ ማከብር ነገርኳት። እርሷም፣ "ይሄ የዓመታት የጸሎት ጥያቄዬ መልስ ነው" ስትል አከለችበትና ለበርካታ ዓመታት ስትጸልይ እንደ ነበረ እና በተለይም እግዚአብሔር ልቤን ለውጦ ወደ አሜሪካ የመመለሱን ፍላጎት በውስጤ እንዲያደርግ ትጠይቀው እንደ ነበረ በመግለጽ አስደነቀችኝ። እነዚህን ሁሉ ዓመታት ይህንን ለምን ምሥጢር አድርጋ ለብቻዋ እንደ ደበቀችው ስጠይቃት፣ ይሄ በእርሷ እና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ጉዳይ እንደ ሆነ ገለጸችልኝ። ስታከልበትም፣ "ነግሬህ ቢሆን ኖሮ፣ ሐሳቡን አትወደውም ነበር ወይም ታጠፋብኝ ነበር፣" አለች። ምናልባት እርሷ ልክ እኔ ደግሞ ስሕተት ልንሆን፣ አሊያም ምናልባት ተገላቢጦሹ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ በዚህ





ጉዳይ ላይ ፍጹም እርግጠኛ ስላልነበርኩኝ፣ የይሆናል ግምት ማበጀት አልፈልግም። ሁኔታዎች ለራሳቸው እንዲናገሩ እንፍቀድላቸው።

እርግጠኛ ሆኜ አውቀው የነበረው ወደ ኢትዮጵያ ለመመለሴ ምንም ጥርጥር እንዳልነበረኝ እንጂ፣ የፒኤች.ዲ ጥናቴን ለመጨረስ ወደ አሜሪካ የመመለስ ምንም ሐሳብ አልነበረኝም። እንደውም ከዚያ በፊት ሰምቼው የማላውቀው የነበረውን፣ "ጥበበ እንደ ዕድል የሚቆጠሩልህን መሸጋገሪያ ድልድዮች አታቃጥል!" የሚለውን ንግግር በመናገር የመከሩኝን የመምሪያው ሰብሳቢ የነበሩትን የዶ/ር ሲግለባምን ምክር ለመስማት ተከላክያለሁ። ኢትዮጵያ ስደርስም የመመለሴን ደስታ ለመግለጽ መሬቱን ስሜ እንደ ነበረ፣ እንዲሁም የተግባራቴ ማዕከል አድርጌው ጌታን ብቻ ከሙሉ ግለት ጋር ለማገልገል የእውነት ፈልጌ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። ይህንንም ለማድረግ ሞክሬ የነበረው ልክ ከላይ እንደ ገለጽኩት ያለውን የተለያዩ ኅብረቶችን የመመሥረት ዓይነት ተግባራትን በማስጀመር ነበር። ድኆችን ለመርዳት "መና" የሚባል የአነስተኛ የገንዘብ ተቋም ለማቋቋም ሞከሬ፤ እንደ ሲቢኤምሲ እና በምሥረታው ውስጥ ድርሻ ያገኘሁበት የኪንግደም ሚኒስትሪ ዓይነት በርካታ የቤተ ክርስቲያን ደጋፊ ድርጅቶች ውስጥ ተሳትፌያለሁ። እንደዚያም ሆኖ፣ ለጌታ ከዚያ በላይ ማድረግ እየፈለግሁ ጌታን ማገልገል ብዬ የገመትኩት ነገር ግን ተጠቃልሎ ያበቃበት ነጥብ ላይ ሳይደርስ ቀረ። ደግሞም አገልግሎቴ በጣም ውጤታማ እንዲሆን እና ለእኔ የሚያረካ እንዲሆን ስልታዊ በሆነ ቦታ ላይ እንዳልተቀመጥኩኝ እገምታለሁ። በድጋሚ፣ ስሜቶቼ ምንም ያክል እውነተኛ ቢሆኑም፣ የእነዚህ ስሜቶች ምንጩ ምን እንደ ሆነ እርግጠኛ አልነበርኩም።

ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ ወደ አሜሪካ ተመለሰና ቃል እንደ ገባው በኤምኤስዩ ውስጥ ተመልሼ የምገባበትን ሂደት ስላስጨረሰ፣ እኔም እንዲሁ ዝግጅት ማድረግ ጀመርኩኝ። ተመልሰን ወደ አሜሪካ ልንሄድ እንደ ሆነ ለልጆቼ ነገርኳቸውና ደስተኛ የሆኑ መሰሉ። የወርልድ ቪዥን አስተዳደር ወደ ፊት ልለያቸው እንደምችል ማሳሰብ ሲጀምር ቦታዬን እንዲተካ ጥሩ ጓደኛዬ የነበረውን ተስፋሽን ጠቆምኳቸው። ሐሳቡም በቅርብ አለቆቼ ዘንድ በጥሩ ሁኔታ ተቀባይነት አገኘ።

ይሁን እንጂ፣ አንድ ቀን ከኤምኤስዩ የታሪክ ትምህርት ክፍል ደብዳቤ ደረሰኝ። ደብዳቤውም ይገልጽ የነበረው የትምህርት ክፍሉ በገንዘብ እጦት

ምክንያት ሊቀበሉኝ እንደማይችሉ እና ሌላ ጊዜ ለማመልከት እንድሞክር ነበር። በጣም ተስፋ ቆረጥኩኝ ደግሞም ለራሴ "የምንቀሳቀሰው ጌታን እየሰማሁ ነው ወይስ በገዛ ምኞቶቼ እና ግልጽ ባልሆኑ የፍላጎት መቀያየሮች ነው?" ስል ራሴን ጠየቅሁኝ። ደብዳቤው በልቤ ውስጥ ቅዝቃዜን ፈጠረ፤ ደግሞም በጸጸትና በበደለኝነት ሞላኝ። በዚያ ቀን ከኤ.ዲ.ኤስ በተያያዘ ለሥራ ጉዳይ ወደ ዩኒቨርስቲ እየሄድኩኝ ነበርና በመልክዐ-ምድር ትምህርት ክፍል ውስጥ ያስተምር የነበረውን ጓደኛዬን ተስፋዬን አገኘሁት። በጭንቀት የተሞላውን ፊቴን አይቶ አንዳች ነገር አንብቦ ነበርና በሠራተኞች ከበብ ውስጥ ለሻይ ይዞኝ ሄዶ ምን እንደ ተፈጠረ ለመስማት ፈለገ። እኔም፤ "በዚህ ጊዜ ልገልጸው በማልፈልገው ነገር ላይ እንድትጸልይልኝ እፈልጋለሁ" ብዬው እንደውም ከመጽሐፍ ቅዱስ የማበረታቻ ቃል እንዲያካፍለኝ ለመንኩት። ወደ ቢሮው መሄድና መጸለይ እንደምንችል ነገሮኝ ወደ ቢሮው እየሄድን ሳለ፤ ከኢሳይያስ መልእክት ወደ አእምሮው የሚመጣ ጥቅስ እንዳለ ነገረኝ። ነገር ግን ከየትኛው ምዕራፍ እንደ ሆነ በትክክል ሊያስታውስ ሳይችል ቀረ። "የተናገርኩትን አደርጋለሁ፣ ደግሞም የምሻውንም እፈጽማለሁ" የሚል ቃል ያለበት ክፍል ነው" ብሎኝ፤ ወደ ቢሮው ስንደርስ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አንሥቶ ገጾችን አገላበጠና በአእምሮው ይመላለስ የነበረውን ጥቅስ ኢሳይያስ 14፡24 ላይ አገኘው። ጥቅሱም እንደሚከተለው ይነበባል፡-

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ምሎአል።

እንደ ተናገርሁ በእርግጥ ይሆናል፥

እንደ አሰብሁም እንዲሁ ይቆማል።"

ከዚያ በኋላ የሆነውን ነገር ነግሬው በቃሉ እንድበረታታ መክረኝና ቢሮውን ትቼ ወጣሁ። አስቀድሞ ስለ ኢሳይያስ 32 የነበረኝን የሕልም ተሞክሮ የነገርኩት የመጀመሪያው ክርስቲያን ጓደኛዬ ተስፋዬ መሆኑን አስታውሱ። በዚያ ቀን የተናገረውን መቼም አልረሳውም፤ "ጥበበ እግዚአብሔር ለአንተ ትልቅ ዕቅድ አለው።"

በዚያ ቀን የትምህርት ክፍሉ የላከልኝን ደብዳቤ ለባለቤቴ ለአዜብ አሳየኋት። እኔ የቱንም ያክል ተስፋ ብቆርጥ፣ ለእርሷ ግን ነገሩ ምንም ማለት አልነበረም። ባሕርይዋ በሆኑ ያልተጠበቁ መልሶቿ ታስደንቀኛለች፡ "የሁሉም





መጨረሻ እና የመጨረሻው ሁሉም ይሄ አይደለም። ምን ሊሆን እንደሚችል ማን ያውቃል? ተስፋ አትቁረጥ። ውሳኔያቸውን ሁሉ ቀልብሰው ሌላ ደብዳቤ ሊልኩልህ ይችላሉ፣" አለችኝ። ከጓደኛዬ እና ካካፈለኝ የእግዚአብሔር ቃል እንኳን እንዲያ ያለውን እምነት አላገኘሁም። በእምነት ላይ የተመሠረተውን አቋሟን ከማድነቅ ይልቅ፣ በቍጣ ሆኜ የለውጥ ተቃዋሚ እና እውነተኝነት የሌላት መሆን እንደሚቀናት መለስኩላት። ደብዳቤውን አንብቤው ከገጽታው ባለው መልእክቱ ወስጀው የነበረ ሲሆን፤ እርሷ ግን ከዚያ ያለፈ አንዳች ነገር አይታበታለች - እምነት።

የአዜብ እምነት እና በእግዚአብሔር ላይ ያላት ንጹሕ እንዲሁም ያልተወሳሰበ እምነቷ ሁልጊዜ ያስደንቀኛል። ያስደነቀኝ ነገር፣ በሚቀጥለው ቀን ከሥነ-ጥበብ እና ፊደላት ትምህርት ክፍል ፋክስ ደረሰኝ። ፋክሱም የረዳት አስተማሪነት ዕድል እንደ ተሰጠኝ የምስራች የሚያበስር ስለ ነበር፣ ያ ሁኔታ ሁሉን ነገር ቀየረው። ያ ማለት ረዳት የመሆኑ ዕድል ካለኝ፣ ለትምህርት የምከፍለው ክፍያ ይነሣልኛል፤ ደግሞም፣ የመድን ወጪዬ ይሸፋናል ማለት ስለ ሆነ ለፒኤች.ዲ ትምህርቴ በይፋ ተቀባይነት አገኘሁ ማለት ነው። በመደነቅ ሆኜ ዜናውን ምሽት ላይ ለአዜብ ሳካፍላት፣ ያለችኝ ብቸኛ ነገር፣ "አየህ፣ በቂ እምነት እንዲኖርህ ነገሬህ ነበር፣" የሚል ብቻ ሆነ።

ቀጣዩ ያልተጠበቀ ነገር ተገለጠ - አንድ ቀን ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ቪዛ ለመጠየቅ መላውን ቤተሰብ ይዤ ወደ አሜሪካ ኤምባሲ ሄድኩኝ። ሁላችንም ቪዛ እንደሚሰጠን ተማምኜ የነበረ ቢሆንም፣ እስከደነቅ ድረስ በቆንጽላ ጽሕፈት ቤት ውስጥ የነበረው መኮንን ለእኔ ቪዛ ሰጥቶ ለባለቤቴና ለቤተሰቡ ከለከለ። ያ ያልተለመደ ነገር በመሆኑ፣ ወዲያውኑ ውሳኔውን እንደማልቀበል በመናገር በቆንጽላ ጽ/ቤቱ ለነበረችው ሴት ያለ ቤተሰቤ እንደማልሄድ አረጋገጥኩላት። የጀርባ ታሪኬን፣ የገንዘብ እና የሥራ ሁኔታዬን ጨምሮ ያቀረብኳቸው ሰነዶች ሁሉ ከእኔ አይታ አኳያ ያለ ምንም ችግር ቪዛ ለማስጠት በቂ ማስረጃ ነው ብዬ አስቤ ነበር። ሏቆንጽላው ሠራተኛ ቀደም ሲል አሜሪካን አገር እንደ ነበርኩኝ እና ወደ አገሬም የተመለስኩት በፈቃዴ እንደ ነበር አብራራሁላት። እንዲሁም ደግሞ በሚሺጋን ግዛት ተወልዶ የአሜሪካ ፓስፖርት ያለው ወንድ ልጅ እንዳለኝ ገለጽኩላት። የትኛውንም ያክል ክርክር ቢደረግ ሴትየዋ ሐሳቧን እንድትቀይር ማድረግ አልተቻለም። በእያንዳንዱ

ቆንጽላውን በረገጥንበት አጋጣሚ አሜሪካ ከተወለደው ጸጋ በቀር ለእያንዳንዳችን የተወሰነ መጠን ገንዘብ መክፈል ስለ ነበረብን፣ በከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ለቤተሰቡ ቪዛ ለማግኘት ሦስት ጊዜ ያክል ጣርን።

የሚያስደንቀው፣ ጥያቄያችን ተቀባይነት ባጣ ጊዜ ሁሉ ቤተሰቡን ወደ አካባቢው ኬክ ቤት ወስጄ የሚወዱትን ኬክ እጋብዛቸውና ወደ ቤት ወስጄያቸው ጌታን እናመሰግን ነበር። እቤታችን ሆነን ለእኛ ታዋቂ የሆነውን "*ክብር ለኢየሱስ ይሁን፣ እየን አሸናፊነቱን፣ ኃያል እንደርሱ የለም፣ ይነግሥ ለዘለዓለም››* (2) የሚለውን መዝሙር እንዘምራለን። በቆንጽላው ሠራተኛ ውሳኔ መጥፎ ስሜት ተሰምቶንም አያውቅም፤ ደግሞም ነገሮች አሁንም ድረስ ጥሩ እየሄዱ እንደ ሆኑ በማመን ወደተለመደው ሥራችን ተመልሰናል።

በመጨረሻም፣ ኤምኤስዩ ከሚገኘው ፕሮፌሰሬ በበልግ ለሚጀምረው የትምህርት መንፈቀ-ዓመት እንድመጣ የሚመክር መልእክት ደረሰኝ። የነበርኩበትን ሁኔታ አስታውቀው ስለ ነበረ ሁሉንም ነገር በጥሩ ሁኔታ አውቋል። ትምህርቱ ሳያመልጠኝ መጓዝ እንድችል በምችለው ፍጥነት ሁሉ ብቻዬን እንድመጣ መከረኝና የቤተሰቡን ጉዳይ ዘግየት ብሎ እርሱ እንደሚወጣው ቃል ገባልኝ። ሐሳቡን ባለመቀበሌ ብቻዬን መሄድ አልፈለግሁም። የሚያስደንቀው እና ከጠበቅሁት በላይ የሆነብኝ ነገር፣ እንድሄድ የሚደረገው ግፊት የማይታክት እምነት ካላት ከባለቤቴ ከአዜብ ጭምር መምጣቱ ነበር። ወዳጆቼም እንዲሁ እንድሄድ ስለ መከሩኝ በመጨረሻ በጣም እያቅማማሁ ለመሄድ የሠጋሁበትን ትልቁን እርምጃ ወሰድኩ። ወደ አሜሪካ ኤምባሲ ሄጄ ቪዛዬን ካገኘሁ በኋላ ወደ አገሪቱ በረርኩኝ።

## *ወደ አሜሪካ መመለስ - መሰናከሉን ማሸነፍ*

በኤም.ኤስ.ዩ. ትምህርቴን ለመቀጠል ለበልጉ የትምህርት መክፈቻ መድረስ ቻልኩ። አሰፋ የሚባል ረጋ ያለ ሰው እና እርሱም በአግሪካልቸራል ኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ውስጥ ለፒኤች.ዲ ሊማር ዕጩ የሆነ የክፍል ተጋሪ ባገኘሁበት በስፓርታን መንደር አንደኛው አፓርታማ ውስጥ ተመደብኩ። ነገር ግን፣ ጓደኞቼ የነበሩትን ልጆቼን ስለ ናፈቅሁ፣ አገሩው ዘንድ ሕይወት ለእኔ ሲበዛ አስቸጋሪ ሆነብኝ። በሥራ ወይም አገልግሎት-ነክ በሆኑ ነገሮች ካልተጠመድኩኝ





በቀር አብዛኛውን ጊዜዬን የማሳልፈው ከእነርሱ ጋር በመሆኑ፣ ከእነርሱ ርቆ መኖር ከባድ ሆነብኝ። እንደ ቤተሰብ አብረን እንሄድ የነበረበት ቤተ ክርስቲያን ብቻዬን መሄድ አስጠላኝ፣ ለግብይትም ወደ ገበያ ስፍራ መሄዱን ጠላሁ። ትክክልም ይሁን ስሕተት ብቻ የብቸኝነት ሁኔታዬ የተሳሳተ ውሳኔ እንዳደረግሁ ያስታውሰኝ ጀመር። በድጋሚ በበደለኝነት እና ጸጸት ስሜት ውስጥ ተሞላሁ። ያ ብቻ አይደለም፣ አእምሮዬን የሚንጠው ሁሌም ያለው ትልቁ ጥያቄዬ፣ "በሕይወቴ ውስጥ የእግዚአብሔርን አቅጣጫ እና ምሪት ስቼው ይሆንን?" የሚለው ሆነ።

በንቃት እሳተፍበት የነበረና በሳም ቤት በየሳምንቱ ይገናኝ የነበረ አነስተኛ የኢትዮጵያውያን ኅብረት በላንሲንግ ይካሄድ ነበር። ምንም እንኳን ኅብረቱ ጥቂት መጽናናት የሰጠኝ ቢሆንም፣ የቤተሰቤ አለመገኘት በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ችግር ሆነ። ባለቤቴ ለራሷ እና ለልጆቹ ቪዛ ለማግኘት ሁለት ጊዜ ስትሞክር፣ እኛም ከዚህ ወገን ልናደርግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል። ይህም የድጋፍ ደብዳቤን ከትምህርት ክፍሉ እና ከትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን ወደ አዲስ አበባው የአሜሪካ ኤምባሲ መላክ ሲሆን፣ ምንም ነገር ሊሠራ ባለመቻሉ ትምህርቴ ላይ ትኩረት ማድረግ አልቻልኩም።

ችግሩን ያከፋው ደግሞ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል የነበረው የጦርነት ደመና በመባባሱ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ በጣም አስቀያሚ መሆኑ ነበር። ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ እንዲወጡ እየተደረገ የነበረ ሲሆን፣ በሌላኛውም ወገን ደግሞ እንዲሁ ዓይነት አጸፋ ተደርጓል። ባለቤቴ ኤርትራዊ መሆኗ በዘመኑ የፖለቲካ አየር ንብረት ውስጥ አንዳች ድንጋጤን ፈጠረብን። ሁሉም ነገር ከግምት ገብተው የፒኤች.ዲ ትምህርቴን ለመከታተል ስል ቤተሰቤን መለየቴ ትክክለኛ ውሳኔ እንደ ሆነ ራሴን ለማሳመን ከባድ ሆኖ አገኘሁት። በእርግጥ፣ ራስ ወዳድ የሆነ እንቅስቃሴ በማድረጌ ራሴን እየወቀስኩ ወደ ባለቤቴ ደወልኩኝና ለቤተሰቡ ቪዛ ለማግኘት አንድ ጊዜ ደግሞ እንድትሞክርና ያ ደግሞ ካልሠራ የመጨረሻው እንደሚሆን፣ ትምህርቴንም አቋርጬ በእርግጥ ወደ ኢትዮጵያ እንደምመለስ ግልጽ አድርጌ ነገርኳት። ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ሞከረች፣ እርሱም ሳይሳካ ቀረና ያ ለእኔ ስለ ቆረጠልኝ ለፕሮፌሰሬ ከገባሁት ቃል በተለየ ሕሊናዬ ጤነኛ መሆኑን በመተማመን ለመመለስ ወሰንኩኝ። ወደ አገሬ መመለሱ ከግብረ-ገብ አንጻር ትክክል እንደ

ሆነ እና ቃሌን ለማክበር ስል ብቻ በሚሽጋን መቆየቱ አደርገው ዘንድ ከባድ ነገር እንደ ሆነብኝ አረጋገጥኩ። ለመጓጓዣዬ በቂ የሆነ ገንዘብ አልነበረኝምና ውድ ጓደኛዬን ዘሮምን እንዲረዳኝ ስጠይቀው ሳያቅማማ ወጪዬን ሸፈነልኝ። እርሱ አሥመራ ሳለሁ የተዋወቅሁት ጓደኛዬ ሲሆን፣ በጣም ተወዳጅ እና የሚታመኑት ሰው ነበር። አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በርካታ ጊዜያት የጥንት ንግግር የሆነውን "ኤ ፍሬንድ ኢን ኒድ ኢስ ኤ ፍሬንድ ኢንዲድ" ("ለችግር ጊዜ የሚደርስ ወዳጅ የምሩን ወዳጅ ነው" እንደ ማለት) በትክክል በሕይወቱ ያስመሰከረ ሰው ነው።

ወደ አገሬ ስመለስ፣ መመለሴ በቤተሰብ፣ ጎረቤቶች እና ጓደኞቼም ጭምር ዘንድ መነቃቃትን ፈጠረ። አሁን ሥራዬን ስለ ለቀቅሁ እሠራበት የነበረው የሥራ መስክ ለጠቆምኩት ሰው ተሰጥቷል። ቤተሰቡን ለመደገፍ የሚያስችል የመጠባበቂያ ዕቅድም ሆነ የገንዘብ ጥሪት ስላልነበረኝ፣ በድንገት እንግዳ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ገባሁ። በ፳፣ የመጀመሪያው ያደረግሁት ነገር ራሴን ለአንድ ሳምንት ያክል መለየት እና መጸለይ እንዲሆን አድርጌ በሕይወቴ ላይ ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ መለየት እንድችል ጌታ እንዲረዳኝ ጠየቅሁት። የእኔ ሁኔታ በዚያ የሕይወቴ ቅጽበት ወቅት ትርጉም የማይሰጥ በጣም የተወሳሰበ እና በጣም ግራ የሚያጋባ ሆነ። ጓደኞቼን፣ በተለይም እንደ ዳኒ፣ ጌች እና ጥሌ ያሉትን ሐረሪዎቹን አገኘሁና ግልጽ በሆነ ውይይት እንዲሁም በጸሎቶች ምን እየሆነ እንዳለ ለመለየት የምንችለውን ጣርን። በዚያን ጊዜ፣ ወደ ወርልድ ቪዥን ደወልኩኝና ከአለቃዬ ጋር ተነጋግሬ መመለሴን ሳስታውቀው ደስ የማያሰኝ መደነቅን ነበር የመለሰልኝ። ኋላም፣ የአስተዳደር ቦርዱ ጥቂት ከተመካከሩ በኋላ "የሥልጠና መኮንን" በሚል መጠሪያ በድርጅቱ ሌላ የሥራ መስክ ውስጥ እንድሠራ ሌላ ዕድል ሰጡኝ። ዋናው ሥራዬ በእንግሊዘኛው ኤዲኤስ በሚል ምሕጻረ-ቃል ተጠርቶ እውቅና የተሰጠውን የልማት ትምህርት ማጠናከር ሆነ። እንድሠራ እና ለቤተሰቤ የሚሆን ገንዘብ እንዳገኝ ሁለተኛ ጊዜ ዕድል ስለ ተሰጠኝ መጀመሪያ ጌታን ቀጥሎም የአስተዳደር ቡድኑን ለማመስገን እወዳለሁ። አዚብ የማትሠራ መሆኑ ከግምት ገብቶ፣ በዚያ ወሳኝ ሁኔታ ውስጥ ጌታ በጊዜው ጣልቃ ባይገባ ኖሮ ምን ሊሆን ይችል እንደ ነበረ በእውነት አላውቅም። ከቪዛ ክፍያ እና የመጓጓዣ ወጪዎች ጋር በተያያዘ ለተለያዩ ፍላጎቶች ይዘናቸው የነበሩትን የገንዘብ ጥሪቶች ሁሉ አሟጠን ተጠቅመን ነበር።





ይፋዊ የሥራ መመለሴን ተከትሎ፣ የኤዲኤስ መርሐ-ግብሩን መልሶ ለማጎልበት ጠንክሬ መሥራት ጀመርኩኝ። ተማሪ ሆነው ይሳተፉ የነበሩት ወደዚያ ተመልሼ ስላዩኝ ተደሰቱ። መርሐ-ግብሩ በሙሉ እንቅስቃሴው በድጋሚ ሥራውን ጀመረ። ሁኔታውን እንዴት እንደምገልጸው ባላውቅም፣ እኔ እና ቤተሰቤ በተወሰነ መልኩ እንግዳ በሆነ ሁኔታ ውስጥ መኖር ጀመርን። እስከሚገባኝ ድረስ ከአሜሪካ ጋር በተያያዘ የነበረው የቤተሰባችን ሕይወት እርከን አብቅቶለታል። ለእኔ የመሰለኝ ሠነዱ እንደ ተዘጋ እና ከአሜሪካ ጋር በተያያዘ ያለው ጉዳይ በተደመደመበት ነጥብ ላይ እንደ ደረሰ ስለ ነበር፣ ነገሩን ፈጽመን ዘግተን ወደ ሌላው ነገራችን እንድንቀጥል ቆርጫለሁ። ባለቤቴ ምክንያቱ ባልገባኝ ሁኔታ ያንን ምክንያት ስላልተቀበለች እንዳላበቃለት በማመኗ በእምነቷ ላይ ቀለድኩና እንዲያውም አቋሟን እንደ ግትርነት እና ያለመሸነፍ ምልክት አድርጌ ወሰድኩት። አንዳንድ ጊዜ እንደውም እበሳጭባትና፣ "ይሄ ነገር ለማለቁ ከዚህ ሌላ ምን ዓይነት የሚያሳምንሽን ማስረጃ ፈለግሽ?" ብዬ ተናግሬ አውቃለሁ። ለእንዲህ ያለ ከባድ ጥያቄ ምላሽ አትሰጥም። እንደ እኔ ከሆነ፣ ነገሩ አልቆለታል። *አሮማይ! ሠነዱም ተዘግቷል!*

ከተወሰኑ ወራት በኋላ፣ ከአሜሪካ ኤምባሲ ቆንጽላ ጽ/ቤት ደብዳቤ ሲደርሰን ነገሮች በድጋሚ ሌላ ተውኔታዊ የአቅጣጫ ለውጥን ያዙ። በደብዳቤው ላይ እንድንመጣ እና ሂደቱን በጠበቀ መልኩ ለመላው ቤተሰብ ቪዛችንን እንድንወስድ ተነገረን። ይህ ያልተጠበቀ ማስደመሚያ ተዓምር ነበር ተብሎ ብቻ አይገለጽም። በእኔ በኩል ይህ ሁኔታ ያልተለመደ ቅይጥ ስሜቶችን ፈጠረብኝና በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ትልቁን ጥያቄ እንድጠይቅ አደረገኝ፤ "የገዛ ራሴን አምሮት እየተከተልኩ ነኝ ወይስ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ፈቃድና በጠላት ሤራ መካከል ትልቅ ጦርነት እየተካሄደ ነው - ወይስ ይሄ በገዛ ፈቃዴ እና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል የሚደረግ ጦርነት ነው?" ሁሉም ዓይነት ጥያቄዎች ጠንካራ እና የእርግጠኝነት መልስ ልሰጥ በማልችልበት መልኩ በአእምሮዬ ውስጥ ተነሡ። ይሄ በሰውኛ ቃላት ግልጽ አድርጎ ለመግለጽ በጣም የተወሳሰበና ይልተለመደ ታሪክ ነው። የቅርብ ዘመን ኃላፊ ጊዜያትን መለስ ብዬ ስመለከታቸው፣ ሥዕሉ ግልጽ ያልሆነ እና ውስብስብ ነበር።

አዜብና ልጆቹ ዜናውን በመስማታቸው ተደሰቱ። ስሜቷን ለራሷ አምቃ የያዘች ቢሆንም እንኳን፣ ጫናው ከገዛ ራሷ የኤርትራዊ ወንድ ዘመዶቿ ሲመጣ

ተሰምቷታል። ለሕይወቷ አንዳች ዓይነት ማምለጫ እንዲኖር በገዛ ራሷ የተለመደ የግል መንገድ ስትጸልይ ቆይታለች። አሜሪካ የመጨረሻው ማምለጫዋ ሆኖ፣ ደግሞም በሁሉም ጠማማ ነገሮች መካከል ሆና እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረጓን ቀጥላበት ነበር። በእኔ በኩል፣ እኔ ከተመለስኩኝ በኋላ ፍጥነቱን ጨምሮ የነበረው የኤዲኤስ መርሐ-ግብር ሙሉ እንቅስቃሴውን እያደረገ ስለ ነበረ እለየው ዘንድ የከበደኝ ነገር ሆኖብኛል። ስለዚህም፣ ለተማሪዎቼ እና ትልቅ ውለታ ለዋለልኝ ለድርጅቱ ሌላኛው የተስፋ መቁረጥ ምንጭ መሆን አልፈለግሁም። ከዚህም ሌላ፣ የገንዘብ ጉዳይም ሌላው ችግር መሆኑ አይካድም። ለመጓጓዣ የሚሆነውን ገንዘብ ለማግኘት ወደ የት እንሄዳለን? ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት እናውቃለን? ምንም እንኳን ልረታቸው የሚገቡኝ ችግሮች ያሉብኝ ብሆንም፣ ከትቢያ አንሥቶ ሕይወቴን የለወጠልኝን ጌታዬን እንደምወድድ በጣም አድርጌ አውቃለሁ። ለእኔ ያለው የእርሱ ፍቅር ማብቂያ እንደሌለውና ዘላለማዊ እንደ ሆነ ጥርጥርም አልነበረኝም። ብርቱ በሆነችው እጅ እንዴት እንደ ደረሰልኝና ኤርምያስ 31፥3-4 እንደሚናገረው ከነበርኩበት ማቅ እንዳወጣኝ ጠንቅቄ አውቃለሁ።

ምንም እንኳን ጥልቅ የሆኑትን ጥያቄዎች መመለስ ባልችልም፣ ደግሞም አሁን ባለሁባቸው የተጠላለፉ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማግኘት መታገሌን ብቀጥልም፣ የቀሩት ቴክኒካዊ ጥያቄዎች መፍትሔዎችን አገኙ። የወርልድ ቪዥን አስተዳደር የኤዲኤሱን ጉዳይ ተረከበኝ - በዚህ አጋጣሚ፣ አቶ ጌታቸውን አመሰግናለሁ። አሁን በሕይወት የሌለው የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ ቱህ የገንዘብ ሸክሜን ተቀበለኝ። ወደ አሜሪካ ለመሄድ የሚያስፈልገንን ከሞላ ጎደል ሁሉንም የገንዘብ ፍላጎታችንን እርሱ ስለ ሸፈነልን፣ ዝግጅቶቻችንን አጠናቀቅንና ከአዲስ አበባ በሉፍታንዛ አድርገን ወደ አሜሪካ በረርን። በዚያም ታኅሳስ 13 ቀን 1990 ዓ.ም ላይ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በአሜሪካውያን እንዲሁ ሞቅ ያለ አቀባበል ተደረገልን።

ለቤተሰቡ አፓርታማ እስኪገኝ ድረስ ለጊዜው ለአንድ ሳምንት ያክል በሳም ቤት ውስጥ አረፍን። በኤምኤስዩ የቤቶች አስተዳደር ዘንድ ሄጄ ቤት እንዲሰጠኝ አመለከትኩ፣ ምንም እንኳን እንደ ደንቡ ለጸደይ የትምህርት መንፈቅ-ዓመት ያልተመዘገብኩ ብሆንም፣ እነርሱ በቸርነት ስፓርታን መንደር





ውስጥ የሚገኘውን 1540 ኤፍ ሰጡኝ። ይህች በራሷ ትንሿ ተዓምራት ስትሆን፣ ጥር 24 ቀን ዓ.ም 1991 ላይ ወደ አዲስ አፓርታማ ተዘዋወርን። እንደ አንድሪያ እና ክሪስ ያሉ ጓደኞቼ አዲስ ፍራሾችን ለቤተሰቡ በማምጣት ሲጐበኙን፣ ከእኛ ጋር ጸሎት በማድረግ እና አንድሪያ ትወደው የነበረውን ቡና በመጠጣት ኅብረት በማድረግ ስለ አዲሱ ቤት እግዚአብሔርን አመሰገንን። ቀጣዩ አውራ መሰናክል ለጸደይ መንፈቅ-ዓመት እንዴት አድርጌ የረዳት አስተማሪነቱን ሥራ እንደማገኝ ሆነ። አንድ ሰው ራሱ ለራሱ የሚከፍልበትን ገንዘብ ካላቀረበ በቀር የረዳት አስተማሪነቱ ዕድል በሌለበት ሁኔታ ክፍል ገብቶ ለመማር የሚያስችል ምዝገባ ማካሄድ የማይታሰብ ነው ማለት ይቻላል። ለነገሩ በእኛ ሁኔታ መደበኛ የሆነ የትምህርት ምዝገባ ሳያደርጉ አሜሪካ ውስጥ መዝለቁ የማይቻል ነገር ስለ ነበር፣ አዲስ በሮች እንዲከፈቱ አጥብቀን ጸለይን። የመጀመሪያው በር በተዓምራት ተከፈተ።

በአንደኛው ጥሩ የሰኞ ማለዳ ላይ ከ2፥00 በፊት፣ ከአይኤኤች (ኢንተግሬቲቭ አርትስ ኤንድ ሂዩማኒቲስ) ዳይሬክተር ዘንድ የስልክ ጥሪ ደረሰኝ። ቀደም ሲል የቤተሰቤ ብርቱ ደጋፊ የነበረችውና ሲበዛ በትሕትናዋ የምትታወቀዋ ዳይሬክተር "ምን እንደ ሆነ ገምት" አለችኝ። ለእኔ የሚሆን የምስራች እንዳላት አውቄያለሁ። "ምን እንደ ሆነ ገምት" በማለት "ቲኤ (ቲቺንግ አሲስታንት) በአይኤኤች ውስጥ ኮርስ መስጠቱን አቁሟል፣ ያም የሥራ ቦታ ክፍት ነው። ማመልከት ትፈልጋለህ?" አለችኝ። ለቤተሰቡ በጣም ግድ የሚላት ይህች ሴት የምስራቹን ስትነግረን ደስ ያላት ብትሆንም፣ መረጃውን ይፋዊ በሆነ የሥራ ድምፀት በማስተላለፍ ስሜቷን ጨቁናዋለች። ይሁን እንጂ፣ ይህ ያልተጠበቀ ዕድል ለእኔ ክፍት በመሆኑ እርሷ ሲበዛ ተደስታ እንደ ነበረ በጣም ግልጽ ሆነልኝ። ይህ ዕድል ባይከፈት ኖሮ የቤተሰቡ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ምንም እውቀቱ የለኝም። የአይኤኤች ዳይሬክተር የእኔ ደጋፊ በመሆኗ ሁልጊዜም ቢሆን ሳመሰግናት እኖራለሁ።፡

ቤተሰቤ እና እኔ ቸር የሆነችውን የእግዚአብሔርን ክንድ እንመሰክራለን፣ ደግሞም ይህንን ተሞክሮ መቼም አንረሳውም። ቀጣዩ ትልቅ ተግዳሮት ሁለት ጊዜ ያስቀየምኩትን አማካሪዬን እንዴት እንደማገኝ ነበር። አንድ ቀን ደውዬለት ከቤተሰቤ ጋር እንደ ተመለስኩኝና በስፓርታን መንደር ውስጥ እንዳረፍን በመንገር አስደነቅሁት። ቤተሰቡን ማየት እስኪፈልግ ድረስ በጣም ተደስቶና

እጅግ ተደንቆ፣ "ያ እንዴት ሊሆን ቻለ?" ሲል ጠየቀኝ። ሊያየን ወደ ቤት መጣና መደሰቱን ገለጸልን፣ እኔም ረክቼ መደላደሌን በማየቱ ተደሰተ። ያን ጊዜ፣ ከጅማሬ እንሥቶ እስከ ፍጻሜ ድረስ ወደ አገሬ ለመመለስ ያደረግሁትን ውሳኔ እና ወደ አሜሪካ መመለሴንም ቀደም ብዬ ልነግረው ያልፈለግሁበትንም ምክንያት ጨምሮ ሁሉንም ነገር ነገርኩት። አንድ ነገር ልነግረው አቅም አጣሁ፣ ሁለተኛ ነገር ደግሞ ሁለት ጊዜ ያክል ትቼው ከሄድኩ በኋላ እንዳልመለስ ያሳምነኛል የሚል ፍርሃት እንደ ነበረብኝም ጨምሬ አስረዳሁት። ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ ነገሮችን እኔ ካየሁበት አቅጣጫ አንጻር ያላያቸው ፍጹም የተለየ ሰው፣ ከእግዚአብሔር ለእኔ የተሰጠ ጓደኛዬ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ አሠልጣኝም ጭምር ነው። የእርሱ ብቸኛ የውስጥ ሐሳብ ትምህርቴን ጨርሼ በሕይወት ውስጥ ስኬታማ ስሆን ማየት ነበር። በ1985 ዓ.ም ወደ ኤምኤስዩ ለመጀመሪያ ጊዜ ስመጣ፣ 12ኛውን የኢትዮጵያ ጥናት ጉባዔ ለማዘጋጀት የቡድኑ አንድ አካል በመሆን ከእርሱ ጋር ስሠራ ያለኝን ነገር መቼም አልረሳውም - "ጥበበ ለሚቀጥሉት ሃያ አምስት ዓመታት ሕይወትህን ልለውጠው ነው።" ደፋር በነበረው አገላለጹ ተደንቄ ለፕሮፌሰሬ እንዲህ አልኩት፣ "ያንን እንዴት ልትል ቻልክ? ያንን ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ እንጂ፣ እንዳንተ ያለ የትኛውም ሰብዓዊ ፍጡር አይደለም።" ይሁን እንጂ፣ ለዚያ አነጋገሩ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ብቻ ከምሩ የተናገረው ነገር እንደ ነበረ ለማወቅ ቻልኩ።

አሁን ምንም ሰበብ የለኝም፡- እጅጌዬን ሰብስቤ ፒኤች.ዲ ጥናቴን ማጠናቀቅ ነበረብኝ። ቲቺንግ አሲስታንስ የምንለውን የማስተማር ሥራዬን በተመሳሳይ እየፈጸምኩ በጸደዩ ወራት ላይ ትምህርቴን ስቀጥል እድሜው ለትምህርት ካልደረሰው፣ ከጸጋ በቀር ሁሉም ልጆችም እንደዚሁ ወደ ትምህርት ቤት ገቡ። ከትምህርቱ ጎን ለጎን፣ በትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን እንዲሁም በንቃት እሳተፍባቸው የነበሩት የኢትዮጵያ ኅብረት አገልግሎቶች ውስጥ በመግባት የክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ተቀላቀልኩኝ፣ የኅብረቱ አስተባባሪ በመሆንም ለተወሰነ ጊዜ አገለገልኩ። በአፍሪካ ቀንድ ስለ ነበረው የሚዋልል እና የማይተነበይ የፖለቲካ ሁኔታን በተመለከተ የታመመ እና የደከመው ያክል ሆኜ ስለ ነበር፣ በዚያ ዙሪያ የፒኤች.ዲ ጽሑፍ ላዘጋጅ እችል እንደ ሆነ ስለ ርእሱ በጥንቃቄ ማሰብ ጀመርኩኝ። የኦጋዴን እና የኢትዮ-ሶማሌ ግንኙነት ላይ ስላለው የድንበር ጉዳይ ቀደም ሲል የነበረኝ የምርምር መስክ ላይ ፍላጎት





ያጣሁ መስሎ ተሰማኝ። በሌላ አንጻር ደግሞ፣ ክርስትና በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አቅጣጫ ማሰብ ስጀምር ይኼኛው የተሻለ የሚያስኬድ የምርምር አቅጣጫ እንደ ሆነ በራልኝና ልቤ ወደዚህ አዲስ ርእሰ-ጉዳይ አደላ። ቀደም ሲል ለወርልድ ቪዥን እሠራ በነበረ ጊዜ፣ በማርክሲስት አገዛዝ ሥር ስለ ነበረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ባለ ሙሉ ሚዛን ምርምር ሳደርግ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዋና ጸሐፊ የነበረውን የመጋቢ አሳየኸኝን ድጋፍ ለማግኘት በማለም ረቂቅ-ሐሳብ (ፕሮፖዛል) ጽፌ ነበር። ያለመታደል ሆኖ፣ የወርልድ ቪዥን አስተዳደር ረቂቅ ሐሳቡን በሁለት መነሻዎች አላጸደቀልኝም ነበር - 1) በቂ ባጀት አልነበራቸውም፣ 2) ርእሰ-ጉዳዩ ከድርጅቱ አጠቃላይ ግብ አኳያ ወዲያውኑ ትኩረት የሚስብ ነገር አልነበረም። ነገሩን በዚያው ተውኩት፣ ገፍቼበትም ሳልሄድ ቀረሁ።

አንድ ቀን ከፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ ጋር ስብሰባ ተቀምጬ የምርምር ውጥን-ሥራዬን ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ክርስትና አዲስ አቅጣጫ ታሪክ ልጽፍ እንደ ፈለግሁኝ ነገርኩት (ይህ ምርምር ዚ ኢቫንጀሊካል ሙቭመንት ኢን ኢትዮጵያ/የወንጌላውያን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ተብሎ ይታወቃል)። ወዲያውኑ፣ "ይህ የተባረከ ውጥን-ሥራ ነው፣ ግፋበት ደግሞም ከአንተ በተሻለ ይህንን ሥራ ሊሠራ የሚችል ማንም የለም። ኦጋዴን ምንድን ነው? ትንሽዬ አጨቃጫቂ መሬት ናት። ይሄኛው ርእስ የበለጠ ዓለም አቀፍ ፋይዳ ይኖረዋል" ብሎ ሲናገረኝ፣ በመልሱ ተደንቄ መንደርደር ጀመርኩ። ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ ነገሮችን በሰፊው ገጽታቸው ማየት ይችል የነበረ ፈጥኖ የመረዳት ችሎታ ያለው ሰው ስለ ሆነ፣ ሌላው ቢቀር ያን ጊዜ ያልተረዳኋቸውን ነገሮች በርእሰ-ጉዳዩ ውስጥ ማየት ችሎ የነበረ ሰው ነው።

በዚያ ቀን በዕለታዊ ውሎ መመዝገቢያዬ ላይ ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ አዲሱን የመመረቂያ ጽሑፌን "የተባረከ ውጥን-ሥራ" ነው ካለው፣ ትኩረት አደርግበት እና ጊዜዬን በዚህ ውጥን ሥራ ላይ አውል ዘንድ ግልጽ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማሳያ ምልክት ነው ብዬ ጻፍኩኝ። በኮምፒዩተሬ ላይ አዲስ ፋይል ከፈትኩኝና "የእግዚአብሔር መንግሥት ውጥን-ሥራ" ብዬ ሰየምኩት፤ ንዑስ ርእስ አድርጌው የነበረው "የተዘረጋችው የእግዚአብሔር ክንድ" የሚል ነበር (2ኛ ነገሥት 17፡35-36)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጥቅሉ በሃይማኖት እና ክርስትና ዙሪያ በሰፊው በማንበብ የምሬን መዘጋጀት

ጀመርኩኝ። በትምህርት ክፍሉ ውስጥ በዚህ ርእሰ-ጉዳይ የሚሰጥ ትምህርት ስላልነበረ፣ ከፕሮፌሰር ሮቢንሰን፣ ፕሮፌሰር ኤሚ ዴሮጌቲስ፣ ፕሮፌሰር ዴቪድ ቤሌ እና ፕሮፌሰር ሂናንት ጋር ገለልተኛ ትምህርቶችን ወሰድኩኝ። ከተነደፉት ትምህርቶች እና ውይይቶች እንዲሁም ከእነርሱ የግል ምክር ብዙ በመማሬ ለሁሉም ምስጋናዬ ጥልቅ ነው። ከሞላ ጎደል የበለጸገ ልምድ እና በጥቅሉ በዓለም ሃይማኖቶች ላይ ብሩህ ሐሳቦችን ያገኘሁበትንም የረዳት አስተማሪነት የሥራ ዕድል በሃይማኖት ትምህርቶች ክፍል ውስጥ አገኘሁ።

በሕይወቴ ውስጥ እመኛቸው ከነበሩት የትምህርት ዓይነቶች ሃይማኖት ከሁሉም ያነሰው ሆኖ ሳለ፣ አሁን ግን በዚያው ውስጥ መገኘቴ ምጸታዊ ጉዳይ ሆነብኝ። በእርግጥ፣ እንደዛ አስብ የነበረው ከእብሪተኛነቴ እና ገራገርነቴ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዳራ የነበራቸውን የአካባቢያችንን የታሪክ ምሁራን ምንም እንኳን የጠሩ እና በከፍተኛ ሁኔታ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው የታሪክ ሰዎች ቢሆኑም፣ እኔ ግን እንደ ደብተራ እና የገድል ጸሐፍት የሆኑ ያክል ቆጥሬያቸው አውቃለሁ። አዲሱ የክርስትና እምነቴ፣ ወርልድ ቪዥን የሠራሁበት ተሞክሮዬ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እሠራ በነበረ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ለመገንባት የቻልኳቸው ግንኙነቶች፣ እንዲሁም የወንጌላውያን እምነት እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ውስጥ በፍጥነት ይስፋፋ የነበረበት ጥቅል ምልከታዬ አዲስ ወደ ሆነው የጥናት አቅጣጫ ጠልቄ እንድገባ ዳራ እና ዐውዱን ፈጠረልኝ። እንዲሁም ደግሞ፣ አንዳንድ የተነጣጠሉ ሥራዎች እዚህ እና እዚያ ያሉ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባለው ሰው ታሪኩን እና ተፈጥሮውን እንዲሁም ያልተጠበቀ እድገቱን የሚመረምር ከሞላ ጎደል በአድማሱ ሰፋ ያለ ጥናት ስለ ወንጌላውያን እምነት እንቅስቃሴ እንዳልተደረገ ለማስተዋል ቻልኩ።

ጥብቅ በሆነው የፒኤች.ዲ ትምህርት መርሐ-ግብር ውስጥ ማለፉ - ረቂቅ ሐሳብ መጻፉ፣ ውጥን ሥራውን በተመለከተ ለሚነሡ ጥያቄዎች መልስ መስጠቱ እና የመሳሰሉት ቀላል ነገሮች አልነበሩም። ለበርካታ ዓመታት ብዙ እሠራበት ከነበርኩበት የተላመድኩት ርእስ ወደ አዲስና እምነት-ነክ ርእሰ ጉዳይ መሸጋገሩም እንዲሁ አስቸጋሪ ሆኖብኛል። "ወደ ፊት ቀጥል፣ ግፋበት" ይል የነበረው መፈክሬ እና እኔ ከፊቴ ባለው የምርምር ጉዞ ላይ ሊታወስ የሚገባው ነገር በኮምፒዩተሬ ላይ ተጻፈ።





ሰፋ ያለ የመስክ ምርምር ማድረግ የሚያስችለኝን የገንዘብ ድጋፍ ከኮምፕተን ፌሎውሺፕ የማግኘት ዕድል ስላገኘሁ፣ ምርምሬን በጣም በተመቻቸ መልኩ ማድረግ በመቻሌ ዕድለኛና ደስተኛ ነበርኩኝ። በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ የነበረኝ ተሞክሮ እና ከተለያዩ ቤተ እምነቶች መሪዎች ጋር የነበረኝ ሰፊ ግንኙነቶቼ ብዙ ቦታ የሚሰጣቸው ኢጋዦቼ ሆነው አገለገሉኝ። በርእሰ-ጉዳዩ ላይ በቂ የሆኑ የተጻፉ ሥራዎች አለመኖራቸውን በማወቅ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እና ኬንያም ጭምር ወደ በርካታ ቦታዎች የወሰደኝን ቃለ መጠይቆች በሰፊው አድርጌ በዚያ ላይ መነሻ ካደረግሁ በኋላ፣ ኬንያ ውስጥ ወደሚገኙ ስደተኛ ማኅበረሰቦች ዘንድ በመሄድ በዋናነት ኢትዮጵያ በነበረው ኮሚዩኒስት መንግሥት ውስጥ የቀድሞ መኮንኖች የነበሩትን ቃለ መጠይቅ ማድረግ ነበረብኝ። በኬንያም ቆይታዬ ያሳለፍኩት ከጥንቱ ወዳጄ ከጢቆና ከውድ ባለቤቱ ከአልሚ ጋር ነበር። በዚህ አጋጣሚ ሳልፈው የማልችል አስደናቂ ታሪክ ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። ጢቆና አልሚ ምንም ልጅ አልነበራቸውም። በአንድ ወቅት ፓስተር ሠይፉ በናይሮቢ ተገኝቶ በመልእክቱ መደምደሚያ ምእመኑን በአንድ ወሳኝ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲጸልይ ተማጸነ። እኔም ጉዳዬን ሁሉ እርግፍ በማድረግ ጌታ ኢየሱስን ልጅ እንዲሰጣቸው ተማጸንኩ። አዲስ አበባ ከተመለስኩ በኋላ አስገራሚውን ተዐምር ሰማሁኝ - አልሚ ማርገዝዋን አበሠረችኝ። ይህ ብቻም አይደለም። አልሚ ጌታን ብታውቅም፣ ስሌ ውሳኔ ያላደረገ ነገር ግን በመልካም ስብዕናውና በበጎ አድራጊነቱ በእጅጉ የሚደነቅ ሰው ነበር። ጌታም ጸሎታችንን ሰምቶ እርሱንም ማረከልን። በመጨረሻም ታማኙ ንጉሥ ሬቤካን የመሠለ ውብ ሴት ልጅ ሸለማቸው።

በዚያን ጊዜ፣ አማካሪዬና የማይነጥፈው ደጋፊዬ ሐሮልድ ማርከስ ኢትዮጵያ ውስጥ ምርምር እያደረግሁኝ እያለሁ በድንገት ሕይወቱ የማለፉን ልብ የሚሰብር ዜና ሰማሁ። ያ ልቀበለው ያልቻልኩት አሳዛኝ እና የሚያሠቃይ ክስተት ስለ ሆነብኝ ወደ አሜሪካን ለመመለስ ወስኜ እያለሁ፣ በባለቤቱ እና በሌሎች ጓደኞቼ ባለሁበት ቆይቼ የመስክ ሥራዬን ከጨረስኩ በኋላ እንድመለስ ተመከርኩኝ። በመላው ውጥን ሥራ ላይ ተሰፋ ላጣ ምንም አልቀረኝም ማለት በሚያስችል መልኩ እያጉረመረምኩም ቢሆን ሐሳቡን ተቀበልኩ። የተወዳጁ ፕሮፌሰር ሞት ለእኔ ትልቅ ጡጫ ሲሆን፣ አሁን ድረስ እርሱን እናፍቀዋለሁ።

ሲሰማቸው ይደሰትባቸው የነበሩትን በመስክ ላይ ያሰባሰብኳቸውን ትልልቅ እና አስደሳች ታሪኮች ልነግረው አስቤ ባለመሳካቱ ሥራዬ ለተወሰነ ጊዜ ተስተጓጎለ፤ ነገር ግን፣ በድጋሚ እጅጌዬን ሰብስቤ ከፊቴ ያለውን ተግባር ለመጨረስ ወሰንኩኝ።

የፒኤች.ዲ ትምህርቴን በጽናት ለመጨረስ በምገፋበት ወቅት በሕይወት ከሌለው ፕሮፌሰር ጋር የነበረኝን ብርቱ ቁርኝት ሁሉም ያውቁ ስለ ነበረ፣ ከፕሮፌሰር ዴቪድ ሮቢንሰን እና ኤምኤስዩ ውስጥ ካለው የታሪክ ትምህርት ክፍል ከፍተኛ የሆነ ማበረታቻ እና የተቻላቸው ድጋፍ ሁሉ ተሰጠኝ። ፕሮፌሰር ዴቪድ ሮቢንሰን በተፈጠረው ክፍተት ውስጥ በመቆም እና በጥሩ ሁኔታ እንድጨርስ በማበረታታት በእጅጉ ረዳኝ። እርሱ እንዲሁም ከቦስተን ዩኒቨርስቲ ጂም ማከካንን በማስመጣት በሞቱት ፕሮፌሰር የምርምር ሥራ ምክር ይሰጣቸው የነበሩትን ተማሪዎች እንዲረዳ በማስደረግ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። መጀመሪያ ላይ፣ እርሱ እኔ በማጠናው ርእሰ-ጉዳይ ላይ በጣም የተላመደ ስላልነበረ ለፕሮፌሰር ጂም ማከካንም ሆነ ለእኔ ራሱ እንናበብ ዘንድ ቀላል አልነበረም። ነገር ግን፣ ብዙም ሳንቆይ አብረን መሄድ፤ እርስ በርስም በጥሩ ሁኔታ መተዋወቅ ቻልንና ለሥራዬ ስኬት ይሄ ነው በማይባል መልኩ አስተዋጽዖ አበረከተ። የእርሱ ተቺ የሚመስሉ፣ ነገር ግን ገንቢ የነበሩ ጥቆማዎች የመመረቂያ ጽሑፉን ከፍተኛ ግምት በሚሰጠው መልኩ አበለጸገው። ሁለቱም ፕሮፌሰሮች ምሁራዊ አድማሶቼን አሰፉልኝ፣ ደግሞም የወንጌላውያንን እንቅስቃሴ ሰፊ በሆነው የማኅበራዊና ባህላዊ እንዲሁም የፖለቲካ መቼቱ ከብሔራዊ እና አፍሪካ ደረጃ አንጻር እንድመረምረው አገዙኝ።

የመመረቂያ ጽሑፉ ተጠናቀቀ ደግሞም እኔ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ላይ አማካሪዎቼ ፕሮፌሰር ኤሚ ዴሮጌትስ፣ ፕሮፌሰር ሬይ ሲልቨርማን፣ ፕሮፌሰር ዴቪድ ቤይሌ፣ ፕሮፌሰር ዴቪድ ሮቢንሰን እና ፕሮፌሰር ጂም ማከካን ባሉበት ለተነሡልኝ ጥያቄዎች መልስ ሰጠሁ። 'ዲፌንስ' ተብሎ በሚጠራው በዚህ የጥያቄና መልስ ፈተና ላይ ጥሩ እንድሠራ በጥብቅ እና በጽናት ከአንድ ወር ለሚያልፍ ጊዜ ጸልዬ ነበር። ከዚህም ሌላ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ጽናት ባለው መልኩ የሚጸልዩልኝ የጸሎት ተዋጊዎች ነበሩኝ። እንዲያውም፣ በስልክ የጸሎት ማንጊያ አድርገንም እናውቃለን። ምንም እንኳን ይደግፉኝ እና ይረዱኝ የነበሩ ፕሮፌሰሮች ቢኖሩኝም፣ ደግሞም ከሁላቸውም ዘንድ አዎንታዊ የሆነ ግብረ-






ከፒኤች.ዲ ፈተናዬ እንደ ወጣሁ-ለቅሶና ደስታ

መልስ የነበረኝ ቢሆንም፣ ከእምነት ጋር በተያያዘ ለነበረው ርእሰ-ጉዳዬ ምን ያክል ጥሩ ሥራዬን የመከላከል አቅም ሊኖረኝ ይችላል የሚል ጭንቀት ነበረኝ። "እምነት-ተኮር ውይይቶች በጥያቄና መልሱ ወቅት ቢነሣ በገሃዳዊነት የምወጣቸው እንዴት ነው?" የሚሉት ዓይነቶቹ በአእምሮዬ ውስጥ ይመላለሱ የነበሩ የከረሩ ጥያቄዎች ነበሩ።

በእንግሊዘኛው "ኤ ዲፌንስ ኢዝ ኤ ዲፌንስ" (ጥያቄን በበቂ የሚመልሱበት መከላከል የምር መከላከል ሊሆን ይገባል) እንደ ማለት ሲሆን፣ አባባሉ ራሱ ግልጽ እንደሚያደርገው ከባድ ፈተና ነበር። ስለዚህም፣ በሁለት ግንባሮች ዝግጁ መሆን፣ ርእሰ-ጉዳዩን ላለው ሃይማኖታዊ ባሕርይ ጥንቁቅ መሆን፣ እንዲሁም ምንም ኮስታራ የሆነ ያልተጠበቀ ውስብስብ ነገር ሳይገጥመው ጥሩ ሆኖ እንዲያልቅ እየጸለይኩበት ከምሁራዊ አቀራረብ አኳያ ልከላከልበት ይገባኝ ነበር። በዚህ ዝግጅት ውስጥ እያለሁ፣ በኪንግደም ሚኒስትሪ ውስጥ ያገለግሉ ከነበሩት የጸሎት ተፋላሚ አባላት መካከል በመጋቢ እሸቱ በኩል "ሠልፉ የእኔ ነው" (2ኛ ዜና 20፡15-16) የሚለው ቃል ተሰጥቶኝ ከጌታ ዘንድ የማበረታቻ ቃል አገኘሁ። ጥናቴን ከምፈተንበት ቀን አንድ ቀን ቀደም ብሎ ፈተናው ይካሄድበት በነበረው ክፍል ውስጥ ገብቼ ስኬታማ መከላከል እንዲኖር በቁም ነገር ጸለይኩኝ። ጌታ ጸሎቴን ሰምቶኝ እንደ ነበረ እምኜ ከወጣሁ በኋላ ከሁለት ሰዓታት በላይ የተካሄደው ፈተና ምንም ሳልቸገርበት ተጠናቀቀ። ይህንን ስኬት እያከበርን የነበረበትን አንደኛውን ምሽት ላይ ከአማካሪዎቼ አንደኛው፣ "ጥበበ፣ ዛሬ ባልተለመደ መልኩ በጋለ ስሜት ተነሣሥተህ ነበር" በማለት አንደኛው አማካሪዬ አስተያየት መስጠቱ ትውስ ይለኛል። በዚያን ቀን እንደተባለው በልዩ ሁኔታ ተነሣሥቼ እንደ ነበረ አውቄ የነበረ ሲሆን፣ ሌሎች ጓደኞቼም ኋላ ላይ እንዲሁ ሁኔታውን አረጋገጡልኝ።

በጥቅሉ፣ ንቁ እና ደፋር መንፈስን በመስጠት ጌታ ረድቶኝ እንደ ነበረ ምንም ጥርጥር አልነበረውም። ለስኬታማ የመከላከል ሂደት እንዲህ ያሉ አጋዥ እና ግሩም ፕሮፌሰሮችን ወደ ሕይወቴ አምጥቷቸው ስለ ነበረ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በዚያን ቀን ከጌታ ዘንድ አገዛን አግኝቼ እንደ ነበር ምንም ጥርጥር አልነበረኝም።

## *ያልተለመዱ የፈተና ጊዜያትን መጋፈጥ*

ከሁለት ወራት በኋላ፣ ጌታ አስደናቂ የሆነ የሥራ ዕድልን በሚዙሪ ስቴት ዩኒቨርስቲ ከፈተልኝ። የሥራ ዝርዝር የያዘውን ቅጽ በቦርሳዬ ውስጥ ሳገኝ ዛሬ ድረስ ያንን ቅጽ እንዴት ወይም ማን እንደ ከተተው ግን ላውቅ አልቻልኩም። የትምህርት ክፍሉ ሰብሳቢ የነበሩትን ዶ/ር ሚካኤል ሻንግ ደወልኩላቸውና የሥራ ቦታው አሁን ድረስ ክፍት እንደ ሆነ ስጠይቃቸው፣ አዎንታዊ መልስ ሰጡኝ። ወዲያውኑ አመለከትኩኝና ከሳምንት በኋላ ስሜ ቃለ መጠይቅ ከሚደረግላቸው ዝርዝር ውስጥ መካተቱ ተነገረኝ። ለቃለ መጠይቁ ዝግጅት አድርጌ ሚዙሪ ውስጥ ወደሚገኘው ስፕሪንግፊልድ ሄድኩና በእግዚአብሔር ጸጋ ጥሩ ቃለ መጠይቅ አደረግሁኝ። ከሳምንት በኋላ ትምህርት መምሪያው የሥራ መስኩን እንደ ሰጠኝ መልካሙን የምስራች ሰምቼ በአሜሪካን ታሪክ እና አፍሪካ ታሪክ ከፍተኛ ኮርሶችን በዳሰሳ መልክ አስተምር ጀመር። ለዘጠኝ ወራት ያክል እንደ ተመላላሽ ፕሮፌሰር ሆኜ ዩኒቨርስቲውን ካገለገልኩኝ በኋላ በዓመቱ በዛው ዩኒቨርስቲ ውስጥ የቋሚ መምህርነት የሥራ መስክ ተሰጠኝ።

በሚዙሪ ስቴት ዩኒቨርስቲ የነበረኝን ቆይታ የምር ወደድኩት፣ አስደናቂ የሥራ ባልደረቦችንም፣ በተለይም ደግሞ ክርስቲያን ሆነው ያገኝኋቸው ጆርጅ ሂዩማንትሲ፣ ጆን፣ ቶም እና ዎይን ባትሪክ ተዋወቅሁኝ። በእያንዳንዱ ሐሙስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረት አብሬያቸው ለማድረግ የምችላቸውን የተወሰኑ ኢትዮጵያውያንን በማግኘቴም ዕድለኝነት እየተሰማኝ ተማሪዎቼን በእጅጉ ተድላ አደረግኋቸው። ለእኔ ትልቁ ተግዳሮት የነበረው የቤተሰቤ ከእኔ ጋር አለመገኘት ቢሆንም፣ የስፕሪንግፊልድ አስደናቂ ማኅበረሰብን በቀላሉ ስለ ተላመድኩኝ ለዘላለም እዚያ የምሆን መስሎኝ ነበር።

የምርምር ሥራዬን ከመፈተኔ ጥቂት ሳምንታት በፊት በኢስት ላንሲንግ





ውስጥ ለልጆቹ ብለን የገዛነው ቤት በመኖሩ እንደገናም ደግሞ፣ ልጆቻችን ከተለያዩ አገራት የመጡ ጓደኞቻቸው ጋር በኢስት ላንሲንግ በሚገኘው ትምህርት ቤት መቆየቱን ስለ ወደዱት፣ ቤተሰቤ ከእኔ ጋር ሊሆን አልቻለም። ኤምኤስዩ ከየትኛውም አኅጉር የመጡ የዓለም አቀፍ ሰዎችን ስለምትስብ፣ ከተለያዩ የዓለም ክልሎች - ከእስያውያን፣ አፍሪካውያን እና አፍሪካ-አሜሪካውያን ሁሉንም ዓይነት ጓደኞች ነበሯቸው። ደግሞም የምሥራቅ ላንሲንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሰጠውን ያንን የብዝሃ-ባህል ሁኔታ የወደዱት ይመስላል። 1998 ዓ.ም ላይ፣ ቤተሰቤ *ታንክስጊቪንግ* ተብሎ በሚጠራው በዓል ወቅት እኔን ሊጎበኙኝ ያለሁበት ድረስ ሲመጡ ላስደስታቸው እና ቦታውንም እንዲወዱት ላደርጋቸው የምችለውን ሁሉ አደረግሁኝ። እንዲያውም በሚዙሪ ግዛት ውስጥ በሳምንት ማብቂያው ላይ ጥሩ ጊዜ ወደሚያሳልፉባት በዓለም ታዋቂ ወደ ሆነችው ብራንሰን በተባለችው የጐብኚዎች መዳረሻ ብዙ ወጭ በማውጣት ወሰድኳቸው። ይህ ሁሉ ጥረት እነርሱን ስቦ ለማስቀረት ነበር፤ ፋይዳ ባይሰጥም። ያለመታደል ሆኖ፣ ላሳምናቸው ያደረግሁት ጥረት በስቅጣጭ ሁኔታ ሳይሳካ ሲቀር ጊዜ ልክ እንደዚህ ተለያይተን የምንኖረው እንዴት ነው፣ ደግሞስ እስከ መቼ? የሚለው ትልቁ ጥያቄዬ ሆኖ ቀረ። ሴት ልጄ በዚህ ወቅት ወደ ታዳጊነት እድሜ ውስጥ እየገባች እንደ መሆኗ፣ አንዳንድ የሽግግር ችግሮች እየገጠሟት በመሆኑ፣ ያ ሁኔታ ይህ ነው በማይባል መልኩ አስጨነቀኝ። ያን ጊዜ ሚሽጋን ውስጥ በሚገኘው ሜይጀር ትሠራ የነበረችውን ባለቤቴን ልጆቼን አሳምና በተቻለ መጠን እንዲቀላቀሉኝ እንድታደርግ በቁምነገር ጠየቅኋት። እርሷም እንዲሁ መምጣት የማትፈልግ ስለ ነበረች ምንም ልትረዳኝ ባለመቻሏ፣ ብዙውን ጊዜ ሕይወቴ ለምን በመስቀለኛ መንገድ ላይ እንደሚቆምብኝ ተደንቄ ጠየቅሁ። አንዳች ዓይነት አካሄድን አይቼ ነበር ነገር ግን ለዚያ ማብራሪያ ላገኝ አልቻልኩም።

በዚህ ዓይነቱ አጣብቂኝ ውስጥ ሳለሁ ነበር ካልቪን ኮሌጅ በ1999 ዓ.ም ላይ የማስተማር ሥራን በሁለት ዓመት የኮንትራት ስምምነት የዓለምን ታሪክ በዳሰሳ ትምህርትነት እንዳስተምር የተሰጠኝና እኔም ደስ ብሎኝ የሥራ ዕድሉን የተቀበልኩት። ይህ ትምህርት ዓይነት እኔ የሠለጠንሁበት ክልል ባለመሆኑ መጀመሪያ ላይ ተግዳሮታዊ ቢሆንብኝም፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ያንን ድል

ማድረግ ቻልኩኝ። የትምህርቱን ዓይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማርኩት ጊዜ ለዝግጅቱ እጅግ ሲበዛ መሥራት ነበረብኝ። ነገር ግን፣ በቀጣዮቹ መንፈቅ ዓመታት ላይ በጥሩ ሁኔታ ትምህርቱን መወጣት ስለ ቻልኩኝ፣ ካልቪን በቆየሁ ጊዜ የአፍሪካ ታሪክን ካስተማርኩት በላይ ያንን የትምህርት ዓይነት ማስተማሬን ወደድኩት።

የክርስቲያን ዩኒቨርስቲን ስለ መቀላቀል ጸልዩ የነበረው ከመመረቁ ሁሉ በፊት ከመሆኑ ባሻገር ወደ ሚዙሪ ስቴት ዩኒቨርስቲ ከመዘዋወሬ በፊት ሚሺጋን ውስጥ በነበርኩኝ ጊዜ ለጥቂቶቹ አመልክቻለሁ። ነገር ግን ማናቸውም መልስ ስላልሰጡኝ በዚህኛው የክርስቲያኖች ኮሌጅ ውስጥ እንዳስተምር ለተሰጠኝ ዕድል በደስታ ምላሽ ሰጠሁ፣ እንደውም የጸሎቴ መልስ አድርጌ ጭምር ወሰድኩት። ክርስቲያን ምሁር እንደ መሆኑ በጥልቀት የማከብረውና በካልቪን ሲያስተምር ለተወሰኑ ዓመታት የማውቀው ፕሮፌሰር ጆኤል ካርፔንተር በጥሩ ጓደኝነት አብረን ልንዘልቅ ቻልን። ምንም እንኳን እንደ ጓደኛ፣ እና ባለው አቅም እንደ መካሪ አድርጎ ራሱን ያቀረበ ቢሆንም፣ በሞት አጥቼው ለነበረው አማካሪዬ ምትክ እንዲሆነኝ እግዚአብሔር በመንገዴ ላይ ያመጣው ሰው እንደ ሆነ አመንኩ፤ ደግሞም እርሱ ይሠራበት በነበረው ኮሌጅ ውስጥ ማስተማሬ ትልቅ ጉርሻ ሆነልኝ።

በወርልድ ቪዥን እሠራ በነበረ ጊዜ ጓደኛዬ የነበሩ አቶ ዮሴፍ የሚባሉ ሰው "ሕይወት የእምነት ጉዞ ናት" ለሚሉበት ጥልቅ ለሆነው ንግግራቸው ራሴን በመነቅነቅ መስማማቴን እገልጽላቸው ነበር። የዚያ አነጋገር እውነትነት በአጋጣሚው ውስጥ ስገኝ ብቻ በግልጽነት የሚታይ ነገር ሆነልኝ። ምንም እንኳን በካልቪን የነበረኝ አጭር የማስተማር ተሞክሮ አመርቂ የነበረ ቢሆንም፣ ለአጭር ጊዜ ብቻ እንዲቆይ ያደረገው ነገር ምን እንደ ሆነ ዘርዝሮ ማስቀመጡ አስፈላጊ አይደለም። ብቻ፣ ሥራዬ አበቃና ወደ ሌላ ተቋም መዘዋወር ስላስፈለገኝ የሥራ ባልደረባዬ በቤይሎር ዩኒቨርስቲ ለወጣው የአሶሽየት ፕሮፌሰርነት ሥራ እንዳመለከት ጠቆመኝ። የቤይሎር ዩኒቨርስቲ በወንጌላውያን እንቅስቃሴ ላይ የተጻፈውን መጽሐፌን በ2001 ዓ.ም ላይ አሳተመልኝ። ለቃለ መጠይቅ ከተያዙት በርካታ ጥሩ ዕጩዎች መካከል አንደኛው እኔ በመሆኔ ኒው ዮርክ ውስጥ ለሚካሄደው ቃለ መጠይቅ ሄጄ ከናይጄሪያ ከመጣ አንድ ዕጩ ጋር ለግቢው ቃለ መጠይቅ ደረስኩኝ። የግቢው ጉብኝቴ እንዲሁም ቃለ





መጠይቁ ካሰብኩት በላይ በጥሩ ተከናወነ፣ ደግሞም እያንዳንዱን ክፍል ወደድኩት። ያን ጊዜ፣ ምላሻቸውን ለማግኘት ረጅም ጊዜ ከጠበቅሁ በኋላ፣ መጨረሻ ላይ ትሑት የሆነ፣ ነገር ግን ተስፋ አስቆራጭ ደብዳቤ ከትምህርት ክፍሉ ሰብሳቢ ደረሰኝ። ደብዳቤውም ሥራው ለሌላኛው ዕጩ የተሰጠ መሆኑን ይገልጽና የትምህርት መምሪያው ያንን ውሳኔ ያደረገው በብዙ መጨነቅ እና መቸገር እንደ ነበረ ያክልበታል። ኋላ ላይ የተባለው አሸናፊ ዕጩ ቀድሞውኑም በሌላ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የአሶሽየት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ የነበረውና ቤይሎርን መቀላቀል ፈልጎ የነበረው ናይጄሪያዊ የታሪክ ምሁር እንደ ነበረ መረጃ አገኘሁ። ለሰብሳቢው በጻፍኩት ደብዳቤ ላይ አጭር የሆነችውን "የእግዚአብሔር ሌላኛው ስሙ ማስደነቅ ነው" የምትለውን ማስታወሻ አከልኩባት።

የቤይሎሩ አዲስ መንገድ በማያስደስት ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ማብቂያዬ የት ይሆን እያልኩ በምጠይቅበት ሰዓት ላይ ለበልግ መንፈቅ-ዓመት የሃይማኖት ትምህርት እንዳስተምር ከመምሪያው የተጠየቅሁበት ያልተጠበቀ ዕድል ከሚሺጋን ስቴት ዩኒቨርስቲ መጣ። ነገሩ የሆነው እንዲህ ነበር - አንድ ቀን ከኤምኤስዩ ሕንጻዎች በአንደኛው ዳር በእግሬ እያለፍኩ እያለሁ ፕሮፌሰር ማክኪንሌይን አገኘሁት። እርስ በርሳችን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በትንሹ ለማውራት ባገኘሁት ዕድል ያለሁበትን ሁኔታ በፍጥነት ነገርኩት። እርሱም በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ላስተምር የምችለው ነገር ሊኖር እንደሚችል ነገረኝና ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ከሰብሳቢው ዘንድ ማስታወሻ ደረሰኝ። በአፍሪካ ሃይማኖቶች ላይ ኮርስ መስጠት እችል እንደ ሆነ ለቀረበልኝ ጥያቄ አልችልም የምልበት ምንም ሁኔታ አልነበረም። ይሄ ልክ እንደ ንፋስ ሽውታ ሲሆን፣ በእንዲህ ያለው የሕይወቴ እርከን ላይ የትኛውንም ነገር ለማስተማር ፈቃደኛ ነበርኩኝ። የማሳድጋቸው ሦስት ልጆች ነበሩኝ፣ እንዲያውም አንደኛው በኤምኤስዩ ጀማሪ ተማሪ እና ሌሎቹ ደግሞ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እየተማሩ ያሉ ነበሩ። በተጨማሪ ደግሞ ጥቂት ቁጠባ ባለበት የወለድ አገድ ከፍያ ለገዛሁት ቤቴ የምከፍለው ነገር ነበረብኝ። ርእሱ በተለይም በአፍሪካ ጥንታዊ ሃይማኖቶች ላይ ያለው ክፍል ለእኔ አዲስ ቢሆንም፣ ሥራውን አንዴ ከተቀበልኩ በኋላ፣ ለማስተማር ሰፋ ያለ ዝግጅት አደረግሁኝ። ትምህርቱ በበልግ መንፈቅ-ዓመት ላይ ሲጀምር ያለ ስስት በውስጡ ተነከርኩበት። በዚያው አጋጣሚ ውስጥ በኢትዮጵያዊ ጓደኛዬ በሶል አማካኝነት

በሴንትራል ሚሽጋን ዩኒቨርስቲ ለአንድ መንፈቅ ዓመት የአፍሪካን ታሪክ እንዳስተምር ሌላ ዕድል ተከፈተ። እንደ ዕድል ሆኖ የማስተማር ድልድሉ በማይጋጭ መልኩ የተቀመጠ ስለ ነበረ፣ ቤተሰቤ እና እኔ ለአንድ መንፈቅ ዓመት ያክል በሕይወት መቆየት ቻልንና ሁለቱም ዕድሎች በታኅሳስ ወር ላይ አበቁ።

ከአምስት ወራት በላይ ለሚሆን ጊዜ ሥራ ለማግኘት ባደረግሁት ጥረት ከዚህ በፊት አድርጌው በማላውቀው መልኩ በርካታ ለሆኑ ዩኒቨርስቲዎች አመለከትኩኝ። ከላይ እንደ ገለጽሁት፣ በቀደሙት ጊዜያት ውስጥ ሥራ ማግኘት የተመቻቸ ነገር በመሆኑ ጥቂት መረጃ በነበረኝ ሰዓት ተቀጥሬ አውቃለሁ። አሁን የበለጸገ ልምዴን እና ያሳተምኳቸው ጽሑፎቼን፣ በርካታ የምርምርና የጥናት ጽሑፎች ውጤቶች በእጄ እያለኝ የሚገርመው ሥራ አለመገኘቱ ነው። በዚህ መልኩ መቆየቱና ኑሮን መግፋቱ ተራራን የመውጣት ያክል እየሆነብኝ ሄደ። ለአምስት ወራት ያክል ያመለከትኩባቸው ተቋማት ሁሉ በደብዳቤዎቻቸው ላይ፣ "ባለህ የትምህርትና የሥራ ልምድ ተደንቀናል" ብለው ይጀምሩና ከዚያም ደብዳቤው ሲያበቃ "የሚያሳዝነው ግን ..." በማለት ስለ ነበረ ተመሳሳይ ምላሾች የያዙ አንድ ዓይነት ደብዳቤዎችን መቀበል ሰለቸኝ። የማይቀረውን ተመሳሳይ መልሳቸውን በመጠበቅ ከዩኒቨርስቲዎች የሚመጡ ደብዳቤዎችን ማንበብ ተውኩኝ።

ታማኝነቱን ተጠራጥሬው ባላውቅም፣ በእነዚህ ወራት ውስጥ ከአንዳንድ ጉዳዮች ጋር ትግል ውስጥ ሆኜ እርሱን ያስቀየምኩበት የሕይወቴ ክፍል የትኛው እንደ ሆነ እንዲያሳየኝ እግዚአብሔርን ጠየቅሁት። ከትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን የሆኑ እንደነ ጆን፣ ዶን፣ ሬክስ እና ቫንጊ ያሉ ጓደኞች እንዲሁም እንደ ጥሩዬ፣ ደርጌ ያሉ ኢትዮጵያውያን ጓደኞቼ እና ከአፍሪካ የጸሎት ቡድን ያሉ ጓደኞቼ ሁሉ ያጽናኑኝ ነበር። እንዲሁም ደግሞ፣ የምወደው ጓደኛዬ የሆነው የሐረሩ የአብዲ ባለቤት እልፌ እና እንደ ወንጌላዊ ነጌ፣ ወንድም ነጋሽ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች በረጅም ርቀት ውስጥ ሆነው ባደረጉልኝ ጸሎቶች በእጅጉ ተበረታታሁ። ከጌታ ዘንድ በነጌ እና እልፌ በኩል በርካታ የሚያበረታቱ እና የሚያንፁ ቃሎችን ተቀበልኩ። ይህም ደግሞ እርሱ የመረጠውን አዲስ የቅጥር በር እስኪከፍትልኝ ድረስ እግዚአብሔርን በትዕግሥት እንድጠብቀው በጥብቅ ተከሎ ያዘኝ።





እንዲህ ያለ ሁኔታ ይፈጠራል ብዬ ጠብቄ ስለማላውቅ፣ በሕይወቴ ውስጥ እንዲህ ያለ ተግዳሮት ገጥሞኝ አያውቅም። ይሁን እንጂ፣ በመካከሉ ለአንድ ቅጽበት እንኳን ራሴን እንዳልተቀጠረ ሰው እንዳልቆጥር ስለ ወሰንኩ፣ ለራሴ የነገርኩት "በሥራዎች መካከል" እንደሚገኝ ሰው አድርጌ ነበር። ስለዚህም፣ ምርምሬን በማድረጉ እና ጌታን በማገለግልበት አገልግሎት ንቁ መሆኑን ገፋሁበት። ጌታ የማስተማርም ሆነ የመምራት፣ እንዲሁም ዐውደ-ጥናቶችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማዘጋጀትን፣ አሊያም በአንዳይነት መንደር ከልጅነት ጀምሮ ጓደኞቼ ከሆኑት እንደ ቴድ እና ብሬ ያሉ ሰዎች ጋር አዲስ ኅብረት የመመሥረት ዓይነት የአገልግሎት በሮች መክፈቱን ቀጠለ።

በዚሁ ጊዜ ላይ፣ ለአፍሪካ ቀንድ የሚማልድ የጸሎት ኅብረት በመመሥረት ራእይ ጌታ ባረከኝ። ራእዩ የመጣው ጌታን ከኅምሳ ዓመታት በላይ ሲያገለግሉ ከነበሩትና 'የከፍታ ዘመን ለኢትዮጵያ' በሚለው መጽሐፋቸው ይታወቁ ከነበሩት የእግዚአብሔር ሰው ከቄስ በሊና ጋር ከነበረኝ ትውውቅ የተነሣ ነበር። መጽሐፉን ያነበብኩት በሚዙሪ ስቴት ዩኒቨርስቲ አስተምር በነበረበት ጊዜ ሲሆን፣ አድናቆቴን ለመግለጽ ስል ደራሲውን አገኘኋቸው። በዚያ መጽሐፍ ውስጥ ቄስ በሊና ሊመጡ ባሉ ጥቂት አሥርት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ልትለማመዳቸው ስላላት ቀጣይነት ያለውና አስደናቂ ልማቶች ከበርካታ ዓመታት በፊት ጀርመን ውስጥ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ ያሳያቸውን መዝግበዋል። ሕዝቡ ያልተጠበቀ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ በረከቶችን ከሰማያዊው መንግሥት እንደሚለቀቅለት ጌታ በእርሳቸው በኩል መናገሩን ከልቤ አምኜው ነበር።

ቀደም ካሉት ጊዜያት ጀምሮ በውስጤ የነበረው የተራማጅነቱ ስሜት አልሞተም። በዚህ አጋጣሚ፣ ትልቅ ታሪክ እንዳለንና ኢትዮጵያውያን የተከበሩ ሕዝቦች እንደ ሆኑ የምናገረው በብዙ ትሕትና ነው። ደግሞም፣ በምእተ-ዓመት ውስጥ ወደ ምድሪቱ የተጓዙ ሰዎች ሁሉ ይህንን መስክረዋል ደግሞም ስለዚያም ጽፈዋል። ያለመታደል ሆኖ፣ በቅርብ ጊዜ በነበረን ታሪክ ውስጥ አገሪቱ ራሷን አስጨናቂ ወደ ሆነ ምስቅልቅል ጉዳዮች ውስጥ የከተተች ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር ኃይል ያንን ሊታደግ እንደሚችል ደግሞ ጽኑ የሆነ እምነት አለኝ። አገሬ ኢትዮጵያን በሚመለከት ስለ መጪው ጊዜ ሲበዛ አዎንታዊ አመለካከት ያለኝ ሰው በመሆኔ፣ ኢትዮጵያ የተስፋ ምድር እንደ ሆነች እርግጠኛ ነኝ፤ ቃሉም በመዝሙር 68፡31 ላይ ይሄንን በእጅጉ ግልጽ ያደርገዋል። ከዚህ

የተነሣ፣ ስለ ሕዝቦችዋ፣ እንዲሁም በእኔው የትውልድ ክፍል ውስጥ ያሉ ስለ ሆኑ በጣም በቅርበት ስለማውቃቸው መሪዎቿም እጸልያለሁ እንጂ፣ ፖለቲከኞቹ ነገሮችን እንደሚያዩት አላያቸውም። ይልቅ፣ ከኃላፊው ጊዜ ፍርስራሾች ውስጥ አዲሲቱ ኢትዮጵያ አብባ ስትወጣ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አዲስ ትውልዶች ሲነሡ፣ ደግሞም ታማኝነታቸው ለእርሱ ብቻ እንጂ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የጎሳ መገኛዎች ያልሆኑት ሲነሡ አያለሁ። በአገሬ ጉዳይ ላይ፣ ነብዩ ኤልያስ አይቷት የነበረችውን "ጥቂቷን ዳመና" አያለሁ። አሁን በእጃችን ላይ አዲስ ኃይል እንዳለን፣ ያም ኃይል ምሽጎችን ለመስበር እና አገሪቱንም ለማሳለፍ የሚያስችል ኃይለኛ ነገርን ማድረግ የሚችለው የጸሎት ኃይል ነው። ቻርለስ ስፐርጅን ሲናገር፣ "እንቅስቃሴ የሚጀምርበት ቦታ ጸሎት ነው።" ብሎ የተናገረ ሲሆን፣ ይህም ደግሞ 2ኛ ቆሮንቶስ 10፡3-6ን እና 2ኛ ዜና 7፡13-14ን መሠረት አድርጎ ያለ ድፍረት ነው።

ቄስ በሊና ወደ ምሥራቅ ላንሲንግ መጥተው ጌታ ያሳያቸውን ራእይ እንዲያካፍሉ ጋብዣቸው ከመጡ በኋላ ሚሺጋን ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም የኢትዮጵያውያን ኅብረቶች እና ቤተ ክርስቲያናት በመጎብኘት ራእዩን አካፈሉን። እርሳቸው ከሄዱ ከዓመት በኋላ *ዘ ሪዘረክሽን ኢንተርሴሰሪ ፕሬየር ፌሎውሺፕ ፎር ዘ ሆርን ኦቭ አፍሪካ ኤንድ ዩኤስ* (ትንሣኤ የምልጃ ጸሎት ኅብረት ለአፍሪካ ቀንድ እና ለአሜሪካ) በሚል መጠሪያ የጸሎት ኅብረት እንዳቋቁም ጌታ በልቤ ላይ ራእዩን አኖረው። በዚህ ኅብረት ውስጥ አሜሪካን የተካተተችበት ምክንያቶች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው፣ ለእኛ ብዙ የሰጠችውን አገር ለመባረክ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ አሜሪካ የምትጫወተው ዓለም አቀፍ ሚና፣ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ያላት ሚና፣ ጸሎትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነበር።

ግቦቹን ጻፍኩኝና ለትሪኒቲ ቤተ ክርስቲያን ካካፈልኩ በኋላ የዓለም አቀፍ ኅብረቱ ራእዩን ተቀብለው ክፍላቸውን እንድጠቀም ፈቀዱልኝ። አንዴ ክፍሉ እንደ ተገኘ፣ ሚሺጋን ውስጥ ካሉ መጋቢያን እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ሐሳቡን ተካፍዬ የጸሎት ኅብረቱ በእግዚአብሔር ጸጋ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ላይ ተከፈተ። በጥቂት ሰዎች ቢጀመርም፣ ጌታ ግን ቍጥሩን አብዝቶት ኃይለኛ የጸሎት ተፋላሚዎችን ወደዚያ አመጣ። ኅብረቱ እንዲሁም ሚሺጋን ውስጥ ላሉ ለተለያዩ የኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ቡድኖች የጋራ ግንባር እና





ምቹ ጥላ እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ የመባረካችን ምንጭ ሆነልን። አንደኛ ዓመቱን ግንቦት 2002 ዓ.ም ላይ ያከበርነው ኢትዮጵያ ውስጥ ለወንጌል ዝማሬዎች መሰራጨት የፈር ቀዳጅነት ሥራ በመሥራቱ በጣም ታዋቂ የነበረውን የእግዚአብሔርን አገልጋይ መጋቢ ታምራት ኃይሌን ተጋባዥ ሰባኪ በማድረግ ሲሆን፣ እርሱም በዝማሬዎቹ እንዲሁም በመንፈስ አንድነት መሠረቶች እና በረከቶች ላይ ኃይለኛ በሆነ ትምህርቱ ባረከን።

ይህ ክብረ-በዓል የተከናወነው የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት የሕይወት ምስክርነቱን በሰጠበት በዛችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። ታምራት የትውፊታዊ ማርክሲዝም ሰው፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የእስር ቆይታ ወቅት ተዓምራታዊ ከኢየሱስ ጋር መገናኘት ሆኖለት ባልተጠበቀው የጌታ ጉብኝት ሕይወቱ የተለወጠችለት ሰው ነው። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር 2000 ዓ.ም ላይ በካልቪን ኮሌጅ ውስጥ ንግግር ያደረገ ሲሆን፣ በሠራተኞች፣ ተማሪዎች እና በሰፊው ማኅበረሰብ ፊት ወደ ጌታ የመጣበትን ተሞክሮውን በተመለከተ የሕይወት ምስክርነቱን ሰጠ። በዚያ ፋኩልቲ አባል በነበርኩበት ጊዜ መላው ወጪው በኮሌጁ ተሸፍኖ የእርሱን መምጣት አስተባበርኩኝ። ለንግግር ወደ ካልቪን በመጣ ጊዜ የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ምስክርነቱን ለመስማት ዕድል ወዳገኘንበት ላንሲንግ ከተማ መጣ።[52]

ላንሲንግ ውስጥ በነበረው አጭር ጉብኝት ወቅት የተወደደችው እኅት ጥሩዬ የኢንተርናሽናል አውትሪች ቸርች መጋቢ ከሆነው አፍሪካ-አሜሪካዊ፣ ከመጋቢ ቻርለስ ቤንሰን ጋር አስተዋወቀችውና መጋቢው ከአፍሪካ-አሜሪካዊ ማኅበረ-ምእመናን ጋር ምስክርነቱን እንዲካፈል ጋበዘው። የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስቴር ጉብኝት ከጸሎት ኅብረታችን የመጀመሪያ ዓመት ክብረ-በዓል ጋር ስለ ተገጣጠመና ሁለቱ ታምራቶች ከእኛ ጋር እዚያ በመሆናቸው፣ እኛ ኢትዮጵያውያን እና አፍሪካ-አሜሪካውያን ኅብረት በማድረግ እና ጌታን ልዩ በሆኑ መንገዶች በእነዚያ የሳምንት ማብቂያዎች ላይ በጋራ ያመለክንበት ግሩም ጊዜ ነበረን።

የጸሎት ኅብረቱ ይልቁኑ ትልቅ ለሆነ ድርጅት መመሥረት በር ከፈተ። የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በሚሺጋን እንዲቋቋምና ለሁሉም በሚሺጋን ላሉ ኅብረቶች እና ቤተ ክርስቲያናት እንደ


ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ

ጥላ እንዲያገለግል ተደረገ። ምንም እንኳን ኅብረቱ በምስረታ ላይ ያለ ቢሆንም፤ አመራሩ አን አርበር ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ የመጀመሪያውን ኮንፈራንስ በማዘጋጀት የድፍረት እርምጃ ወሰዶ በጥሩ ሂደት ላይ ያለ ሥራ ነው። በኮንፈራንሱ ላይም ቄስ በሊና ከኢትዮጵያ ተጋብዘው ጠቃሚ በሆኑ ሦስት ጉዳዮች ላይ በኃይለኛ ሁኔታ አስተማሩን፤ "እኛ ማን ነን?" "እዚህ ያለነው ለምንድን ነው?" እና "ካለንበት ተሻግረን እንንቀሳቀስ።" የማይረሱ ትምህርቶች ነበሩ! ከግራንድ ራፒድስ፣ አን አርበር፣ ይፕሲላንቲ፣ ዴትሮይት፣ እና ላንሲንግ የመጡ ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድነት መጥተው ጌታን አመለኩ። ከአሃዮ የመጣው የወንጌል ዘማሪ ዳዊት ግሩም በሆነ የሙዚቃ ሥራው ኮንፈራንሱን ባረከው።

ስለዚህ፣ ሥራ ያላገኘሁባቸው እነዚያ አምስት ወራት እንዲሁ አልባከኑም። ከላይ ለተገለጹት ተግባራት ተሳታፊ መሆን እንድችል፣ ፊቴን እንድፈልግ፣ እና በገዛ ሥራዬ ላይ ያላለቁትን እንድጨርስ፣ ጅጅጋና አጋዴን ላይ የጀመርኩትን መጽሐፍ እንዳጠቃልል ደግሞም የገዛ ራሴን ታሪክ ለመጻፍ ጊዜ እንዳገኝ አደረገ።

እነዚህ ሁሉ በሮች የተዘጉ ሲመስሉና ሁሉ ነገር ያለቀለት ሲመስል፣ ታማኙ እግዚአብሔር በኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ ለማስተማር ዕድልን የማገኝበትን በር ከፈተልኝ። ክፍት የሥራ ቦታውን አንድ ቀን በክርስቲያን ድረ-ገጽ ላይ አየሁና ወዲያውኑ ለተቋሙ አመለከትኩኝ። በዚያው ቀን በኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ ሥራ እንዳለ እና ለማመልከት ፍላጎት የሚኖረኝ ከሆነ የድጋፍ ደብዳቤ በደስታ ሊጽፍልኝ እንደሚፈልግ የገለጸበት ኢሜይል ከፕሮፌሰር ጆኤል ካርፔንተር ዘንድ ደረሰኝ፣ ለኢሜይሉም የሰጠሁት መልስ "አዎን እባክህ" የሚል ነበር።

በሂደቱ ውስጥ ከኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ አስተዳዳሪ ዘንድ የተማሪዎቼን ግምገማዎች እንድልክ የሚጠይቅ ማስታወሻ ደረሰኝ። በእጄ የትኛውም ተማሪዎች ስለ እኔ የሰጡት ግምገማ ወረቀት ስላልነበረኝ ወደ ካልቪን ኮሌጅ ደወልኩኝ። አንደኛው ነገር ወደ ሌላኛው እያመራ የካልቪን ኮሌጅ አስተዳዳሪ





እንድትጽፍልኝ ሳልጠይቃት ደብዳቤን ስለ እኔ ለኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ አስተዳዳሪ ጻፈች። ይህ ከመሆኑ አንድ ሳምንት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የጸሎት አጋር ከሆነልኝ ወንጌላዊው ጓደኛዬ ነገዎ በኩል እግዚአብሔር የእኔ ተሚጋች እንደ ሆነልኝ ቃል ተቀብዬ ነበርና ጌታ እንደ ተናገረው ተሚጋቾችን አዘጋጀልኝ። ሁለቱ ተሚጋቾች ከካልቪን ኮሌጅ ብቻ የነበሩት ጆኤል እና ክላውዲያ ነበሩ።

አንድ ቀን፣ ለሥራ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግ ተጠይቄ ሳለሁ ወደ ግራንድ ራፒድስ ከተማ ልገባ ትንሽ ሲቀረኝ መንገዴ ላይ መኪናዬ ወደ ቁጥቋጦዎች ተንሸራትታ አነስተኛ የትራፊክ ማማን በመግጨት ቀለል ባለ ቁልቁለት ፊት ቆመች። መኪናዬ ማማውን ሲመታው ግጭቱን መስማት ስለ ቻልኩኝ እና በሰከንድ ውስጥ የሆነ ነገር ስለ ነበረ ደነገጥኩ፣ ደግሞም ግራ ተጋባሁ። ሕሊናዬን ሳረጋጋ፣ የመኪናው ሞተር እየሠራ እንደ ሆነ አስተዋልኩኝ። አጠፋሁትና ለቅጽበት ጊዜ አደጋው ሊያስከትለው ይችለው ስለ ነበረው ጥፋት እና ካለሁበት ወቅታዊ የገንዘብ ሁኔታ አንጻር መኪናውን ለማስጠገን የሚያስወጣኝ ወጪን በተመለከተ አሰብኩኝ። ከመኪናዬ ወጥቼ ተፈጥሮ ሊሆን የሚችል ጉዳትን ለማየት ስዞራት እስኪገርመኝ ድረስ መኪናዋ ጭረት እንኳን አልደረሰባትም ነበር። ስለዚህ ከረግረጉ ጎትቼ አውጥቼ ወደ ኋላ ነዳሁና ወደ ዩኒቨርስቲው ነዳሁ፣ ለቃለ መጠይቁም በሰዓቴ መድረስ ቻልኩ።

ከዩኒቨርስቲው አስተዳዳሪ እና ከሁለት የሥራ ባልደረባቸው ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ በጥሩ ሁኔታ ስለ ተካሄደ፣ የእውነትም ሰላም እና ቤቴ ያለሁ ያክል ተሰማኝ። ድባቡ ሞቃታማ እና ወዳጃዊ በመሆኑ፣ ቃለ መጠይቁ ሲጠናቀቅ ምሳ ሊጋብዙኝ ወሰዱኝና ከምሳ በኋላ አስተዳዳሪው፣ "ከጥቂት ቀናት በኋላ አገኝሃለሁ" አሉኝ። ይኸው ነበር፣ ምንም ሌላ ፍንጭም ሆነ ጥቆማ አልነበረም። ወደ ቤቴ መጣሁና ስለ ሁኔታው ጸለይኩኝ፣ ደግሞም ጌታን ስለ ሁሉም አመሰገንሁ፤ በተለይም ስለ መኪናው እና ደህንነቴ። ከዚያ በኋላ፣ ለሌሎች ምክንያቶች ኢሜይል እንደ ደረሰኝ ማየት ስጀምር፣ ኮሚቴው ውሳኔ ያደረገ መሆኑን እና ሥራውንም እንደ ሰጠኝ በማየቴ ተደነቅሁኝ፣ እጅግ ፈነደቅሁኝ፣ ለራሴም "ደረቁ ወቅት አበቃ" አልኩኝ።

ወዲያውኑ አብራኝ ረጅም ጸሎትን በስልክ ስታደርግ ወደ ነበረችው እልፌ ደወልኩኝ፤ በጸሎቱም መካከል ከአሜሪካውያን ጥንዶች ኢያን እና ሚሼል



ፕሮፌሰር ሐሮልድ ማርከስ

የመጣውንም ቃል አስታወስኩኝ። ለእኔ ይጸልዩ በነበረ ጊዜ መኪና ስነዳ እና በድንገትም በሕይወቴ የሆነውን የእግዚአብሔርን ተዓምራት እንዳስብ ስትተት ሚሼል በራእይ አይታ ነበር። የዕለት ውሎ መመዝገቢያዬን አወጣሁ፣ ቀኑንም አጣራሁ፣ ደግሞም አነበብኩት፣ ከዚያም ነጥቦቹን ላገናኛቸው ጀመርኩ። በእውነትም፣ ሌላኛው የእግዚአብሔር ስም **ማስደነቅ** ነው!

2001 ዓ.ም ላይ ኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ ገብቼ የዓለም ታሪክን እና የአፍሪካ ታሪክን ለአንድ ዓመት አስተምሬ ለቀቅሁ። እግዚአብሔር ለምን ኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ እንደ ወሰደኝ አላውቅም። ግሩም የእግዚአብሔር ሰው የሆኑትን እና መጽሐፋቸው ግሩም የመንፈሳዊ መነሣሣት ምንጮች የሆኑልኝን ፕሬዘደንቱን ጆ ስቶልን በግል በማወቄ ተባርኬያለሁ። ከአንዳንዶቹ ፋኩልቲዎች ጋር፣ በተለይም ከፊሊፕ ባክስትረም እና ባለቤቱ ቦኒ ጋር፣ ዘላቂ ግንኙነቶች ፈጥሬያለሁ። በዚህ ግንኙነት ውስጥ፣ ፊሊፕ እና ቦኒ ክፍል ሰጥተውኝ ከእነርሱ ጋር እንድኖር በቸርነታቸው ሲፈቅዱልኝ የክርስቶስን ፍቅር በጣም ተጨባጭ በሆነ መልኩ በሕይወታቸው ምሳሌ አድርገው አሳይተውኛል፣ ደግሞም ሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ውጤት አሳድረዋል። ከአንዳንዶቹ ተማሪዎቼ ጋር ዘላቂ የሆኑ ግንኙነቶችን መመሥረትም እስክችል ድረስ ግልጽ በሆነ መልኩ ታሪኬን አካፍያቸዋለሁ። በእርግጥ፣ በፊልም ቀረጻ ላይ አተኩሮ የሚማረው አንደኛው ተማሪ ታሪኩን መሠረት አድርጎ የፊልም ቀረጻ ውጥን ሥራ መሥራት እንደሚፈልግ መሻቱን ነግሮኝ ነበር። የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ ስለ ሰጠሁት ጌታ ነገሩን ከዚያ ወደ የት እንደሚወስደው አብረን ማየታችን አይቀርም። የጊዜ ሠሌዳዬ ውጥረት የሞላበት ሲሆን፣ ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ እየሄድኩ አስተምራለሁ። ከዚህም ሌላ፣ አንዳንዶቹ የማስተምራቸው ትምህርቶች አዳዲስ ሆነው ሳሉ በጥሩ ሁኔታ እንዳጠቃልላቸው ግን ጌታ ጸጋውን ሰጠኝ፣ ከ፲ኛ ዜና 18፡13-14 እና ኢያሱ 3፡4 ሊያበረታታኝ ቃሉን ሰጠኝ። በአጠቃላይ፣ ጌታ በእያንዳንዱ ትግል ውስጥ ድልን ሊሰጠው ከዳዊት ጋር እንደ ነበረው ሆነልኝ። በኮርነርስቶን በነበርኩኝ ጊዜ ልክ በካልቪን ኮሌጅ አድርጌው እንደ ነበረው፣ የቀድሞውን የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጉብኝት አመቻችሁና ተጋባዡ የወጣት ተማሪዎቹን ልብ የነካ አስደናቂ የሆነ ምስክርነትን ሰጠ። በመዝጊያ ንግግሩ ላይ ለተማሪዎቹ በሰጠው ምክር በጣም የማይረሳ ሰው እስኪሆን ድረስ፣ "ኢየሱስ ትርፍ ነገር አይደለም፣ የምራችሁን ያዙት፤" ነበር ያላቸው።





ይህች የንግግር ሐረግ አስተጋባች ደግሞም በተማሪዎች መካከል የበይነ-መረብ (ኢንተርኔት) ውይይት መነጋገሪያ ርእስ ሆነች። በኮርነርስቶን ዩኒቨርስቲ የነበረኝን የማስተማር ቅጥር አጠናቀቅሁና አንደኛውን እግሬን በሃይማኖት ትምህርቶች ክፍል ውስጥ በተከልሁበት ኤምኤስዩ ውስጥ በድጋሚ ማስተማሬን ቀጠልኩ። በመቀጠልም ለአንድ ዓመት ያክል የፋኩልቲ/የማስተማር ሥራ ኃላፊነትን ተቀብዬ ስፖኬን ውስጥ ወዳለው ዊዝዎርዝ ዩኒቨርስቲ በመዛወር ለአንድ ዓመት ያክል ሠርቼ ወደ ኤምኤስዩ በመመለስ በጎብኚ ፕሮፌሰርነት ደረጃ በማስተማር ላይ እገኛለሁ። ሁልጊዜም እንደምለው ሌላኛው የእግዚአብሔር ስም **ማስደነቅ** በመሆኑ ቀጣዩን የሕይወቴን ምዕራፍ ለማየት ጉጉ ነኝ። ምርጥ የሆነው ገና ሊመጣ ያለው እንደ ሆነ አሁን ድረስ አምናለሁ። መጪው ጊዜ በእምነት ብርሃን ውስጥ ሊታይ የሚችል ሲሆን፣ አዲሱ ጉዞዬን በጌታዬ እጅ ላይ እንደ ፩ኛ ዜና 29፡10-13 መሠረት እጥላለሁ።

## የማጠቃለያ አስተያየት

ይህንን አጭር መጽሐፍ የጻፍኩት የሕይወት ታሪኬን ለማስረዳት ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ግማሽ ምእተ-ዓመት ያክል ቆይታን በዚህች ምድር ላይ የተኖረበትን የገዛ ራስን ጉዞ ዘርዝሮ መጻፉ በእርግጥም የማይቻል ነገር ስለ ሆነ፣ ለማሳየት የሞከርኩት የጉዞዬን ዋና ዋና ገጽታዎች ብቻ ነው። ከጉርምስና ጊዜዬ ጀምሮ በተለያዩ የሕይወቴ ገጽታዎች ላይ ትኩረት አድርጌያለሁ። ከታዳጊነት እድሜዬ ጀምሮ እስከ ጎልማሳነት ሕይወቴ መግቢያ ድረስ ከማኅበራዊና ባህላዊ ሥረ-መሠረቴ ተነጥዬ በገዛ ተሞክሮዬ ላይ የገጠሙኝን ትርጉም-የለሽነቶችን እንዲሁም መከራዎች አሳይቻለሁ። ግልጽ ሆኜ ወደ ፖለቲካው ዓለም እንድገባ የሳቡኝን የተለያዩ ዐውዶች አስረድቻለሁ፣ ደግሞም የአቻ ግፊትን ከእነ ውጤቱ አሳይቻለሁ። ብዙ ጊዜ ይባል እንደ ነበረው፣ ሐሳቦች ውጤቶች አሏቸው፤ በዘመኔ እንደ ነበሩት እንደ ብዙዎቹ ጉጉ አንባቢ ነበርኩኝ። ጥሩም ሆነ መጥፎ ብቻ የንባብ ልማዴ እና ሁለገብ መሆን በዩኒቨርስቲ ሥርዓት ውስጥ ለነበሩት የእኔ ትውልዶች ተወዳጅ የሥነ-አእምሮ ባህል ነበረ። ፖለቲከኛ እንድሆን ያደረጉኝ አነበባቸው የነበሩ ሥነ-ጽሑፎች አስተሳሰቤን በተጽዕኗቸው መቅረጻቸው ብቻ ሳይሆን፣ ዓለምን በምመለከትበት እይታ ላይም ተራማጃዊ

ውጤትም ፈጥረው ነበር። ምንም እንኳን ሙሉ ለሙሉ ማርክሲሳዊ የሆንኩት መቼ እንደ ሆነ ባላውቅም፣ የፍልስፍናው የተጋጋለ ደጋፊ ሆኜ አያሌዎቹን የሐረሪ ጓደኞቼ እንዲቀበሉት ሳደርጋቸው ተጽዕኖ ፈጥሬያለሁ። ያ ሥር ወደ ጥፋት ጎዳና ወሰደኝ ደግሞም የወጣትነት የዋህነቴን ባበላሸበት መልኩ በአብዮቱ ጊዜ አገሪቱ ያሳለፈችው ፖለቲካዊ ብጥብጥ እኔን ከፋኛ መታኝ። የለውጡን አኳኋን ያየሁት እንዴትም ቢሆን፣ ለውጥ ለሕዝቡ እንዲመጣ እፈልጋለሁ። ራሴን የማየው ለውጥን በማስተዋወቅ ረገድ እና ለሰፊው ሕዝብ **ጉዳይ** ተራማጅ ከነበሩት መካከል አንደኛው እንደ ነበርኩ አድርጌ ነው። ስለዚህም፣ ለዚያ **ጉዳይ** መኖርም ሆነ መሞት በመፈለጌ ሞትን የተጋፈጥኩባቸው ሞትም እኔን የተጋፈጠባቸው ጊዜያት ነበሩ።

*‘ባንዳ’* የሚለው ስም ለምን እንደ ተለጠፈብኝ መቼም ማብራራት አልችልም። ባለኝ ጉልበት ሁሉ በጣም ለዘመትኩለት ነገር ተጻራሪ የሆነውን ተለጣፊ ጠልቼው ኖሬያለሁ። ምንም እንኳን አሁን ትርጉም ባይኖረውም፣ በሕይወት የቀሩ የእኔ ትውልድ አባላት አሁን ድረስ በዚያ ሥዕል ያስታውሱኝ እንደ ሆነና እንዳልሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ያንን ስም የማጥፋት ዘመቻ ማን እንደ ጀመረው ዛሬም ድረስ በእውነት አላውቅም፣ አስበውት የነበረውም ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል አይገባኝም፣ ሆኖም፣ ነገሩን ካለፈ በኋላ ሳየው ግን የእግዚአብሔር እጅ ከእኔ ጋር ነበረች። ልክ ከአየር ላይ እንደሚተኮሱ ድንጋዮች አድርጌ ስለማያቸው የእኔን ትውልድ ሰዎች አከብራቸዋለሁ፤ ደግሞም፣ ከፈጃቸው ሽብር ተርፌው ቢሆን ምናለ ብዬ እመኛለሁ። በዚያን ጊዜ የነበረውን ትውልድ አገሪቱ ማጣቷ አሁን ድረስ አገሪቷን መጉዳቱና ትልቅ ክፍተት መተዉ ለማንም ግልጽ ነው። በግልም ቢሆን እንደ ሽሜ ያሉ ብሩህ ጭንቅላት የነበራቸውን ጓደኞች ማጣት በእኛም ውስጥ አንድ የሚሞት ነገር ስለሚኖር ህልውናችንን ይቀጨዋል። አገሪቱ እንደዚያ ያለ ተወርዋሪ የሆነ ዝርያን ልታፈራ ስለ መቻሏ እስከጠራጠር ድረስ “ቀይ” እና “ነጭ ሽብር” በሚል ስም ሸፋን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የታረዱበት የትውልዱ ሁከት በታሪካችን ውስጥ አንደኛው ጥቁር እና አስቀያሚ ጠባሳ እንደ ሆነ ይዘልቃል። እንደዚህ ያለ ነገር ከዚያ በፊት አልነበረም፣ ወደ ፊትም አይኖርም። ለ**ጉዳዩ** በመሳተፍ ውስጥ የሚከፈለውን ዋጋ ጠንቅቄ የማውቀው በተወሰኑ መንገዶች ይህንን ዋጋ ከፍያለሁና ነው። በተፈጥሮ የተከሰተው “የገለልተኝነቴ” አቋም እና በአብዮቱ





ጊዜ በየትኛውም ተፎካካሪ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች መካከል ውስጥ መጠመዴ በሕይወቴ አንዳች ተጽዕኖ ማድረሱ ባይቀርም፣ የኋላውን ትቶ መልካሙን ለወደፊት እያሰቡ መዝለቅ ጥበብ ነው። እንዲሁም በእኔ በኩል የምወቀስበት አንድም የደም ማፍሰስ በደለኝነት እንዳይኖር አቋሜ አስመልጦኛል። ስለዚህም፣ ከጂው በነበረበት ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር ጠብቆኝ ስለ ነበረ በእጅጉ አመሰግነዋለሁ። የአንድ ሰው ደም በእጄ ቢኖር ኖሮ ስሜታዊ ሰው እንደ መሆኔ በዚህ ዓለም ላይ ለመኖር ፈጽሞ አቅም አይኖረኝም ነበር።

ስለ እኔ ለሞተውና ለወደደኝ ደግሞም ከጉድጓድ ላወጣኝ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ምስጋና አለኝ። “በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ (ኤር. 31:3-4)፡፡ የእርሱ ፍቅር አይገባኝም ነበር፣ በጭራሽ። ይልቅ፣ በሕዝብ ፊት ቀልጄበት ደግሞም ከጂው ስለ ነበረ ቍጣው ነበር ይገባኝ የነበረው። እርሱ **መንገድ፤ እውነት እና ሕይወት** እንደ ሆነ እንዳውቅ ለማድረግ አጋጣሚዎቼን ከታም ጋር እንድገናኝ ባደረገበት ሩቅ በሆነው የጉምላክ ስፍራ አመቻቸው። በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ያለ አንድ ሰው ጌታን እንዳምነው ጋብዞኝ ቢሆን ኖሮ ያንን እውነት ችላ ልለው እችል ነበር። ልቤን አዘጋጅቶ የማምነውን እና የምታመንበትን፣ ደግሞም በእኔ የአስተሳሰብ አኳኋን ያለን ሕይወቴን በዚያ ደረጃ ሊነካ የሚችልን ሰው ወደ ሕይወቴ አመጣና እግዚአብሔር ትኩረቴን ሳበው።

በትዕግሥት ወደ ሕይወቴ ጣልቃ የገባው እግዚአብሔር በፍጻሜውም በ1979 ዓ.ም ሕይወቴን ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ ሰስጠው አስደናቂ ወደ ሆነው ብርሃን አመጣኝ። በባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ የእርሱን ፍቅር፣ ምሕረት እና ሉዓላዊ የሆነች የምትመራ እጅ አይቻለሁ። ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለችው ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንድጽፍ ዕድሉን ሰጠኝ፣ ጌታ የምርምር ፍላጎቴን ወደ መንግሥቱ ሥራ ላይ እንዲሆን የመራበት አኳኋን አስደናቂ ነበር። 1989 ዓ.ም ላይ ወርልድ ቪዥን ውስጥ ከተከናወኑት የማለዳ ጥሞና ጊዜያት በአንደኛው ላይ ኩሪ የምትባል አንድ የጌታ አገልጋይ በምትጸልይልኝ ጊዜ ራእይን አየች። በራእዩ ውስጥ በምርምር ሠነዶች የተሞላ ቦርሳ በእጄ ተሸክሜ አየችኝ። ከዚያም አንድ ሰው ከኋላዬ መጥቶ ቦርሳውን ወሰደውና ሁሉንም ሰነድ ከውስጡ አወጣው። ያንን ካደረገ በኋላ ትንንሽ መጽሐፍ ቅዱሶችን በውስጡ አኖረና ቦርሳውን መልሶ ለእኔ ሰጠኝ። ያን ጊዜ፣ ጌታ ሕይወቴን ወደ እርሱ

አገልግሎት እየመራ ይሆናል ብዬ አስቤ የነበረ ቢሆንም፣ የራእዩን ፋይዳ አልተረዳሁትም ነበር። ከላይ እንደ ገለጽኩት፣ የምርምር ፍላጎቴ የነበረው የወንጌላውያን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ በሚለው ርእስ ላይ ሲሆን፣ ይህም እንቅስቃሴ ለበርካቶች የበረከት ምንጭ ሆኖ የነበረ ነገር ነው።

እዚህ ሚሺጋን ውስጥ ወደ አሜሪካ ሁለተኛ ጊዜ ከተመለስኩ በኋላ፣ ጓደኛዬ ሳም ተቀጣጥለው ይጸልዩ እና ጌታን ያመልኩት ወደ ነበሩ ትንሽ ቍጥር ወደ ነበራቸው የአሜሪካውያን ጓደኞቹ የጸሎት ኅብረት ዘንድ ወሰደኝ። አምልኮው እንደ ተጠናቀቀ ከመካከላቸው አንደኛው ስለ እኔ ያየውን ራእይ መጥቶ ነገረኝ። ያየውም በባሕር ዳርቻ ላይ ቆማ የነበረች ጀልባ በድንገት በሚፈጥን ነፋስ ስትመታ ነበር፣ እናም ይህ ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል መንፈስ ቅዱስን ጠየቀው። መንፈስ ቅዱስም ጀልባው እኔን እንደሚወክል እና ነፋሱም የእግዚአብሔር እጅ እንደ ሆነች፣ በመጨረሻም ጌታ ለእኔ አዲስ ዓላማ እና አቅጣጫ እንደሚሰጠኝ ነገረኝ። እነዚህ አጋጣሚዎች እና ክስተቶች ለክርስቲያን የተለመዱ ይሁኑ አሊያም የአልፎ አልፎ ክስተቶች ምንም አላውቅም። በዚህ ጉዳይ ላይ የክርስቲያኖች ነገረ-መለኮታዊ አቋም ምንም ሆነ ምን፣ ጥቂቶቹን በሕይወቴ ተለማምጃቸዋለሁ። ተስፋ በቆረጥኩባቸው እና ባልተረጋጋሁባቸው የሕይወት ቅጽበቶች ላይ የእግዚአብሔር የቸርነት ሆኖም ወሳኝ ጣልቃ ገብነት ሆነው አይቻቸዋለሁ። እነርሱም ሕይወቴን መልሰው ያነለበቱ፣ እንድጸና የረዱኝ እና ምንም እንኳን እርሱ በሕይወቴ ለነደፈው ነገር ፍጹም መሳካት ከፍታዎች እና ዝቅታዎች የነበሩ ቢሆንም፣ በዓላማዬ ላይ እንድቆይ ያደረጉ አጋጣሚዎች ናቸው። ብዙ ምሕረት እና ጸጋ በእኔ ላይ ያበዛው ጌታ በሕይወት ላኖረችኝ ፍቅሩ እና ለጌታዬ ምሪት የምስጋና መግለጫዬ እንድትሆንልኝ አስቤ በጻፍኳት በዚህች መጽሐፍ በኩል አንባቢዎችን ይንካቸው። ታሪኬን የሚያነቡ ሰዎች ይህንን መጽሐፍ "ዝብርቅርቁ ሕይወቴ እና መለኮታዊው ጸጋ" የሚለውን ርእስ ለምን እንደ ሰጠሁት እንደሚያስተውሉ ተስፋ አደርጋለሁ።





# የግርጌ ማስታወሻዎች

[1]ቶኛንቢራ በ19ኛው ምእተ-ዓመት በራስ መኮንን ጦር ሠራዊት የተገነባች ወታደሮች ከሚያርፉባቸው የተመሸጉ ከተሞች አንደኛዋ ከተማ ነበረች።

[2]እርሳቸው የወረዳው ዳኛ ሆነው ያገለግሉ ስለ ነበረ እሸቴ ቃዲ (የሙስሊም ፍርድ ቤት) ተብለው ይጠሩ ነበር። አባቴ አረብኛ አቀላጥፈው ይናገሩ ነበር። ጠጁ ተብለው የተጠሩት በአካባቢው ጠጅ እንዲሸጥ ያስተዋወቁት ከቀደምት ከነበሩ ሰዎች አንደኛው እርሳቸው ስለ ነበሩ ነበር። ደብተራ ተብለው ይታወቁ የነበረውም በቤተ ክርስቲያን ትምህርት እና አገልግሎቶች ከነበራቸው ተሳትፎ አኳያ ነበር።

[3]እርሷ እንደውም ወታደራውያኑ ገዢዎች በ1970ዎቹ ያስተዋወቁትን የፀረ-መሐይምነት ዘመቻ እንኳን አልተቀበለችም ነበር።

[4]ተስፋ ማተሚያ ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ካሉት የአካባቢው ዘመናዊ ማተሚያ ቤቶች አንደኛው ነበር። ተቀራራቢነት ያላቸውን ትምህርታዊ በራሪ ጽሑፎችን በቤተ ክርስቲያን ወይም በመንግሥት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚማሩ ለወጣት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያትም ነበር።

[5]ከሶማሊያ ጋር የነበረው የድንበር ጭቅጭቅ በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ መካከል ተመላላሽ ጦርነትን አስከትሏል። ትልልቆቹ ጦርነቶች በ1955 እና 1969 ዓ.ም ተደርገው የነበሩት ነበሩ።

[6]ነፍጠኛ የሚለው ቃል እንዲያው በቀላሉ ጠብመንጃ ታጣቂ ማለት ነው። የሚያመለክተው የሐረር ክልል ኢትዮጵያ ውስጥ ሲካተት እና የግዛቱ አንድ አካል ሲሆን፣ ከራስ መኮንን ጋር መጥተው የነበሩትን የምኒሊክ ወታደሮችን ነው።

[7]አቴቴ ከኦሮሞ የለምነት እማልክት ጋር የተያያዘ ሥርዓተ-አምልኮ ነው።

[8]የግሪ ቃጠሎ ብሪታኒያውያኑ ከኢትዮጵያና ጣልያን ጦርነት በኋላ ለጊዜው ኦጋዴንን በያዙ ጊዜ በግሪ ቆጨር የሰፈሩበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። እናቴ፣ እኅቴ እና ወንድሜ ጉርሱም ውስጥ ይኖሩ ከነበሩ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ጋር ሆነው ወደ ሐረር በእግራቸው የሸሹበት ነበር። ከላይ የተገለጸው የቤተሰብ መለያየት ለተወሰዱት የተለያዩ ጎዳናዎች ምክንያት ነበር።

[9]እኅቴ 8ኛ ክፍል ማለፍ አቅቶት ኋላ ላይ ፖሊስ የሆነውን ሌላኛውን ያኅቴን ልጅ እያመለከተ ነበር። "ጋላ" ሲል እያመለከተ የነበረው የራሱን የጎሳ መገኛ ነበር።

[10]ገብሩ ታረቅ አስተሳሰቤን ፋይዳ ባለው መልኩ የቀረጸ ተራማጅ እና ጥበብን የተካነ ክልቡ የሚያስተምር መምህር ነበር። ከብዙ ዓመታት በኋላ በአጋጣሚ ያገኘሁት ዓለም አቀፋዊ በሆነ ጉባዔ ላይ ወረቀት አቀርብ በነበረ ጊዜ ነበር። አወቀኝ ደግሞም ያበረከትኩትን አደነቀልኝ። የታሪክ ሰው እንድሆን ምን ያክል ተጽዕኖ እንዳሳደረብኝ እና እንዳነሣሣኝ ልነግረው የምችልበትን ዕድል ሳልጠቀምበት ቀረሁ።

[11]"የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ኅብረት" የሚለውን መጠሪያ ለማሳየት የተቀመጠ ምሕጻረ-ቃል ነው።

[12]በተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ በለጠ ለማንበብ መሳይ ከበደ የጻፈውን *ራዲካሊዝም ኤንድ ከልቸራል ዲስሎኬሽን ኢን ኢትዮጵያ 1960-1974* የተሰኘውን በ (ዩኒቨርስቲ ኦቭ ሮችስተር ፕሬስ, 2008) ላይ የታተመውን መጽሐፍ ይመልከቱ።

[13]ኋላ ላይ እርሱ የመላው ኢትዮጵያውያን ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ወይም በሌላ ስሙ የመኢሶን ወሳኝ አባል ሆነ። ፓርቲውም ለደርግ ድጋፉን ይሰጥ የነበረ ኋላ ላይ የተንኮታኮተ ነበር። አብዛኛውን ሕይወቱን በምርኮኝነት ፈረንሳይ ውስጥ ነበር የኖረው።

[14]ሐረር ውስጥ አድገን ለነበርነው በርጫ የተለመደ መጠሪያ ነው። ከሰዓት በኋላዎች ላይ ጫት በመቃም ይካሄድ የነበረ የአካባቢው የሚያነቃቃ ተክል ሲሆን፣ አሁን እንደ አደንዛዥ ዕጽ የተቆጠረ ነው።

[15]ቃሉ የሚያመለክተው ምሁራንን ጨምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ሰዎች የአብዮት ተቃዋሚዎች በሚል ሽፋን በሰፊው የተገደሉትን ነው።

[16]ተካ አማረ በምጣኔ ሐብት ትምህርት ዘርፍ ወደ 1962 ዓ.ም ገደማ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ተመረቀ። እርሱ የመጀመሪያ ዲግሪውን መመረቂያ የጻፈው በአሜሪካ እርዳታዎች አደገኝነት ዙሪያ በጥቅሉ ነበር። እርሱ በእርግጥም ተራማጅ የነበረ ሲሆን፣ የተሰጠ እና በቅንነት የነበረ ኮሚዩኒስት ነበር። እርሱ እንደ መካሪዬ አየው የነበረ ሲበዛ ደግ እና የዋህ ሰው ነበር።

[17]በላይ አሁን ላይ ፕሮፌሰር ሲሆን ዳላስ ውስጥ ከጥቂት ዓመታት በፊት ባገኘሁት ጊዜ ሁሉንም አጋጣሚ ያስታወሰኝ ሰው ነበር። በእርግጥ በቼ ጉቬራ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሥር ሆኜ ነበር የምንቀሳቀሰው።

[18]ሰይፈቲ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ውድ የሆነ ጓደኛዬ ነበር። እንድመለስ እና የኮሌጅ ትምህርቴን እንዳጠናቀቅ በርካታ ደብዳቤዎችን ከዩኒቨርስቲ ሆኖ ይጽፍልኝ ነበር። ጌታን ካመንኩ በኋላ ታሪኬን እና መልካሙን የምስራች አካፍዬዋለሁ። ከሁሉም ጓደኞቼ እጅጉን ለለውጥ ክፍት ያልነበረው ሰው እርሱ ነበር። ለወንጌልም ሲበዛ ተቃዋሚ ነበር። የገዢው ፓርቲ አባል ሆነ፣ ደግሞም በደህንነት ሚኒስቴር ውስጥ የቅርብ አማካሪ በመሆን ሰፊ ሙያዊ አገልግሎት የሰጠ ሰው ነው። ኋላ ላይ በጌታ ተማርኮ ብርቱ አማኝ ሆነ። አሁን አዲስ አበባ ውስጥ ወንጌላዊ ሆኖ በቊጭትና በሰፋት ያገለግላል።

[19]አንዳንዶቹ አሁን ታዋቂ የመንግሥት መኮንኖች ሆነው በወቅቱ ላለው መንግሥት እያገለገሉ ናቸው። አንዳንዶቹ አገሪቱን ለቅቀው በመውጣት በግዞት ይኖራሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ ሞተዋል።

[20]መኸዲ ሁልጊዜም ቢሆን ያደርገዋል። ከሁላችንም ይልቅ ራሱን የገዛው እርሱ ነበር። ኤልያስ እና እኔ ብዙም ሥርዓት አልያዝንም።

[21] መኸዲ ተግባራዊ የሆነ ሰው ነበር። እርሱ ከብዙዎቻችን ይልቅ ልቅ የሆነ የማርክሲስት ደጋፊ አልነበረም። የእርሱን የጠባቂነት ተግባራት በስሕተት ያገኘውን ነገር ሁሉ ለመጠቀም የመፈለግ አዝማሚያ እንዳለው አድርጌ በስሕተት ተረድቼው ነበር። እርሱ ኋላ ላይ በበርካታ አገሮች ውስጥ እንደ ዲፕሎማት ሆኖ አገልግሏል። በአሁኑ ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ታዋቂ የሥራ ቦታን ይዟል።

[22]በመጨረሻም ሻለቃ ኪሮስ በወታደራዊ ገዢዎቹ መካከል በተነሣው ጠብ ሕይወቱን አጥቷል።

[23]ገበሬዎቹ ቢያንስ በዚህ የመነሻ እርከን ላይ ስለ አብዮቱ የሚያውቁት በጣም ጥቂቱን ነበር። ጎንደር ውስጥ የነበሩት ገበሬዎች አንድ ጊዜ ደርግ የንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ወንድ ልጅ እና ተተኪ ነው ብለው ነበር።





[24]ገነት የዋህና ምንም የማታውቅ ልጃገረድ ነበረች። ግንኙነታችን ብዙም አልዘለቀም። ኋላ ላይ እርሷ ዩኒቨርስቲ ገባች፣ ነገር ግን አጿርጣ የባከነ ሕይወት ትኖር ነበር።

[25]በአብዛኞቹ ተማሪዎች ዘንድ "ታዋቂ ተመራጭ" ሆኜ ተመርጬ ነበር። በሆነ ምክንያት አብዛኞቹ ሴት ተማሪዎች እኔን መረጡኝ። ከእስፋው ወሰን የሆኑት በአንዳች ጥርጣሬ ይመለከቱኝ የነበሩ ተማሪዎች የሴቶች ምርጫ መቆጠር እንደሌለበት ሐሳቡን አነሡ።

[26]እነዚህ ከቀድሞው መንግሥት ጋር በተያያዘ ለአካባቢው አለቆች እና የመንግሥት ሠራተኞች ይሰጡ የነበሩ ስሞች ናቸው።

[27] ጥሌ እና እኔ የአብዮት ዝማሬዎችን ከእነዜማው እናቀናብር ነበር። በሰልፋችን ወቅት ከመጠቀማችን በፊት ቀን እና ሌሊት ተማሪዎች እንዲለማመዷቸው እናደርግ ነበር።

[28]የመኸዲ ዕጣ ፈንታ አልታወቀም። እርሱ ከዘመቻ ጣቢያ ጠፍቶ ቀረ። እናቱ በጥልቀት ተጨንቀው ነበር። ከአጎቱ ልጅ ጋር በተደረገ መማከር ወደ እርሱ ጣቢያ እኔ እንድሄድ እና አድራሻውን እንድፈልግ ተደርጌ ነበር። የተባባሰው የወንድሜ ጤንነት እያለም እርሱን ልፈልግ ተስማምቼ ነበር።

[29]ባንዳ የሚለው ቃል በመነሻነት የሚያመለክተው ኢትዮጵያ በጣልያኖች ተይዛ በነበረበት ጊዜ (1928-1933 ዓ.ም) ከጣልያኖች ጋር ወግነው የነበሩትን ነው። አሽከር ወይም አሳልፎ የሰጠ ተብሎ በቀላሉ ሊተረጎምም ይችላል። የኢሕአፓ አዳዲሶቹ ፖለቲከኞች ቃሉን የሚጠቀሙት ከፓርቲያቸው ጋር ያልተባበሩትን ለማሳጣት ነበር። ዶ/ር ኃይሌ ፊዳ ታዋቂ የነበሩ ፖለቲከኛ ሲሆኑ፣ እንዲሁም ከመንግሥት ጋር በመተባበር ይሠሩ የነበሩ የመኢሶን አንደኛው መሪም ጭምር ነበሩ። የሚያሳዝነው የእርሳቸው ሰዎች ከደርግ ጋር ችግሮች ስለ ነበሩባቸው የወታደራዊው መንግሥት የቀደሙት ሰለባዎች እነርሱ ነበሩ።

[30]ፊዲስት የሚለው ስም የተገኘው የመኢሶን መሥራቾች ከሆኑትና ታዋቂውን አብዮት ለማጎልበት በሚል ስም ከመንግሥት ጋር ይሠሩ ከነበሩት ታዋቂ ፖለቲከኛ ከዶ/ር ኃይሌ ፊዳ ነው። ባንዳ እና ፊዲስት የሚሉት ስሞች እየተለዋወጡ ጥቅም ላይ ሲውሉ ፖለቲካዊ ስም ማጥፊያዎች ሆነው ያገለግላሉ።

[31]ያ ማለት ዕለታዊ ምግቦቻችንን በልተን የተወሰነብንን ገንዘብ በወሩ መጨረሻ ላይ ደመወዛችንን ስንቀበል እንከፍላለን ማለት ነው።

[32]ደርግ ማርክሲዝምን ለማስፋፋት ከተጠቀመባቸው ሕዝባዊ ክስተቶች አንደኛው ኪነት ነበር። ተሰጥዖ የነበራቸው ሕጻናት ከእያንዳንዱ ቀበሌ ተወስደው ለጦርነት ማነሣሣት ዓላማዎች እንዲዘፍኑ እና ድራማዎችን እንዲጫወቱ ይደረግ ነበር።

[33]ኢ.ፒ.ኢ.ዲ የሚለው እንግሊዘኛ ምሕጻረ ቃል ኢንቫይረንመንታል ፕሮቴክሽን ኢኮኖሚክ ፕሮጀክት ለሚለው መጠሪያ የዋለ ነበር። በገንዘብ ይደገፍ የነበረው በግብርና ሚስቴር እና እዚያ ይሠሩ በነበሩት ጥሩ ይከፈላቸው በነበሩት ኢትዮጵያውያን ሥር በዩኤስኤይድ ነበር።

[34]ጉዞው ከሦስት ቀናት በላይ ወሰደ። በሺዎች የሚቆጠሩ የጅጅጋ ነዋሪዎች ከተማይቱን ለቅቀው ከ70 ኪሎ ሜትር በላይ በእግር ተጉዘው በሥቃይ ሐረር ደረሱ።

[35]ሰለሞን በፓርቲው ውስጥ ታዋቂ የሆነ ሰው ነበር። እርሱ ሞትን ያመለጠው ገጠራማ አካባቢ ሄዶ የሙስሊም ስም ለራሱ በመውሰድ እና ልክ እንደ ገበሬ ሆኖ አንድ ዓመት ለሚሆን ጊዜ በመኖር ነበር። እርሱ ኋላ ላይ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ የፒኤች.ዲ ዲግሪውን

አግኝቷል። ጌታን በ2003 እ.አ.አ ናይሮቢ ውስጥ አገኘ። እኔ እና የእርሱ ሚስት አልማዝ ወደ ጌታ እንዲመጣ የረዳነው ሰዎች ነበርን። ተሞክሮው በሕይወቴ የማልረሳው አስደናቂ ነበር።

[36]ደቤ ኋላ ላይ ኢትዮጵያን ለቅቆ በመውጣት ወደ አውሮጳ ሄዶ መሐንዲስ ሆነ። ፒኤች.ዲ ዲግሪውን አሜሪካ ውስጥ ያገኘ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ለ AT&T ይሠራል።

[37]ዮሐንስ ኋላ ላይ የሁለተኛ ዲግሪውን በውኃ ቴክኖሎጂ ከሕንድ አገር አገኘ። አርባ ምንጭ ውስጥ በተከፈተው አዲሱ የውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ውስጥ አስተማሪ ሆኖ ሲያገለግል ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ያልተረጋጋ የፖለቲካ ብጥብጥ በጣም ይበሳጭ ነበር። በተለይ ደግሞ የገዢው ፓርቲ አባል እንዲሆን ከፓርቲው መኮንኖች ይመጣበት በነበረው ጫና በጣም ተሰላችቶ ነበር። ራሱን አቃጥሎ ሞተ።

[38]ሕዝብ ድርጅት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) ለሚለው መጠሪያ አጭር መግለጫ ነበር። ኢሠፓአኮ የሠራተኞች ፓርቲን ለመመሥረት እንደ መንገድ ጠራጊ ይሆን ዘንድ በወታደራዊው መንግሥት የተቋቋመ ነበር። እጅግ በጣም የማይወደድና ይጠላ የነበረ ድርጅት ነበር።

[39]ማልሬድ በ1960ዎቹ ተቋቁሞ የነበረ ከማርክሲስት ሌኒንስት ፖለቲካዊ ድርጅቶች ከፍተኛ ቊጥር ያለው አንደኛው ነበር። ምንም እንኳን በከፊል ድብቅ የነበረ ቢሆንም፣ የመንግሥት ደጋፊ የነበረ ፓርቲ ነበር።

[40]እሳት እና ሰደድን ጨምሮ በርካቶች ነበሩ። አንደኛው በኦሮሞ ፖለቲከኞች ይመራ የነበረ ሲሆን፤ ሌላኛው በወታደራዊው ባለ ሥልጣናት ነበር።

[41]ሁለቱ ለቤተሰቤ ዘመድ የሆነችው የየሺ ወንድ ልጆች ነበሩ። ታላቁ ዴቭ ሲባል ታናሹ ዐቢይ ይባል ነበር። ዴቭ **መኢሶን** የነበረ ሲሆን፣ ዐቢይ ደግሞ የ**ኢሕአፓ** ደጋፊ ነበር። ዐቢይ አድራሻው ጠፋ፣ ግልጽ የሆነው ነገር በመንግሥት ተገድሎ የነበረ መሆኑ ነው። ዴቭ ለተወሰኑ ዓመታት ኖሮ ኋላ ላይ ሞተ። ቤተሰቡ በዚህ ያልተለመደ የወንድማማቾች ጦርነት ውስጥ ምን ማድረግ እንደ ነበረበት ባለማወቅ ዘግናኝ የሆነ ኑሮ ኖረ።

[42]ጴጥሮስ ጥሩ ጓደኛዬ ነበር - ሲበዛ የዋህ ነበር። ትምህርቱን ጨርሶ የኮምቦልቻ ወረዳ አስተዳዳሪ እንዲሆን በገዢው ወታደራዊ መንግሥት ከመመልመሉ በፊት ለከተማ ልማት ሚኒስቴር ሲሠራ ነበር። ጴጥሮስ አስተዳዳሪ ሆኖ እያገለገለ ሳለ ግልጽ ባልሆኑ ሁኔታዎች 1982 ዓ.ም ላይ ሞተ።

[43]ታዋቂው ኮባ ሰፈር የሚገኘው ስድስት ኪሎ አቅራቢያ ከናዝሬት ትምህርት ቤት አጠገብ ነበር። በዋናነት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ይስቡ የነበሩ የመጠጥ ቤቶች ረድፍ ነበር። ኮባ ሰፈርን እና ኢብሳ ሔንትሳን ያዘወትሩ የነበሩት አብዛኞቹ ተማሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ምንም ምቾት ሊሰማቸው ያልቻሉ የአብዮቱ ትግል ያቆሰላቸው ነበሩ።

[44]ኋላ ላይ አስኔ ኮተቤ የመምህራን ማሠልጠኛ ገባ። አብዛኛውን ሕይወቱን ሰቅጣጭ በሚባል መልኩ ኖሮት በመጨረሻ በሚያሳዝን ሁኔታ 1989 ዓ.ም ላይ ሞተ።፡

[45]ይሄ 1888 ዓ.ም ላይ በአድዋ ጦርነት ላይ እና 1928 ዓ.ም ላይ በማይጨው ጦርነቶች ላይ ጣልያንን የተዋጉትን ታዋቂውን አርበኛ ደጃዝማች ባልቻን ለማመለከት ነበር።

[46]ትውፊታዊውም ሆነ አዲሱ ዓይነት ጋብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ውስብስብ እና ውድ የሚባል ሥራ ነው። እኔ የከብረ-በዓሉ የተለየ ዝግጅት ሳይኖረኝ በጥቅሉ ቀለል አድርጌው





ነበር። ምንም እንኳን የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ጋብቻ በተለየ ድባብ የሚካሄድ ቢሆንም፣ በአንዳንድ ገጽታው የትውፊታዊው ጋብቻ ሥርዓት ተጽዕኖዎችን የያዘም ነው።

[47]አንድ ጊዜ ለጥሌ *ዘ ሶቪየት ፖለቲካል ቶውት* የሚል መጽሐፍ ሰጥቼው ነበር። የመጽሐፉን የመጀመሪያው ገጽ ላይ ሕይወቱን በተጽዕኖ ከቀረጹት መካከል አንደኛው ግሩም አብዮተኛ እኔ እንደ ሆንኩ መጻፉ እስካሁን ይገርመኛል። የፓርቲ አባል ከመሆኑ ጋር የተያያዘ የማይረባ ሰበብ ነግሮኝ በሠርጌ ላይ ለመገኘት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። የኋላ ኋላ እርሱ እና ባለቤቱ ለረጅም ጊዜ በቆየ ሕመም ተሠቃይተው በሚያሳዝን መልኩ እንደ ዐረፉ ሰማሁ።

[48]ቃኘው ከ1943-1945 ዓ.ም በኮሪያ ጦርነት ወቅት ያገለገሉ የኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች መጠሪያ ነበር። ከጦርነቱ ማብቃት በኋላ የአሜሪካ መንግሥት ራዲዮ ማሪና በሚል እንዲሁም ቃኘው በሚለውም ስም የራዲዮ ጣቢያ ለመመሥረት ወሰኖ ነበር። ይህ በቀዝቃዛው ጦርነት ዐውድ ውስጥ የተከናወነ ነበር።

[49]የዕለት ውሎ መመዝገቢያዬን አሥመራ ውስጥ ጣልሁ። አሥመራ በዚያ ፍጥነት ትያዛለች ብለን ገምተንም አናውቅም ነበር። ወደ ቤታችን እንደምንመለስ በመገመት መጻሕፍትንና የምርምር ሰነዶችን ጨምሮ ንብረቶቻችንን ትተን ወጣን። ነገር ግን ነገሮች ለሁላችንም ያልተጠበቁ አቅጣጫዎችን ያዙ።

[50]ሰፈራ ከሶቪየት የጋርዮሽ መርሐ-ግብር ጋር አብሮ እንዲሄድ የተደረ የመንግሥት መርሐ-ግብር ሲሆን፣ ገበሬዎች በተመሳሳይ መንደሮች ውስጥ ቢጋራ እንዲኖሩ እና በትብብር ድርጅቶች ውስጥ እንዲታቀፉ የተገደዱበት ነበር። መርሐ-ግብሩ በገበሬዎቹ ዘንድ በእጅጉ የተጠላ ነበር። ወታደራዊው መንግሥት እንደ ወደቀ፣ ገበሬዎች ውጥን-ሥራውን መተው እና ወደ ቀደመው መንደሮቻቸው መመለስ ጀመሩ።

[51]ጽዮን በተወሰነ መልኩ በአብዮቱ ተሰባ የነበረች የተሰጠች ክርስቲያን ነበረች። እርሷ እምነቷን በመተው በወታደራዊው መንግሥት ውስጥ ሴቶችን በመወከል ታዋቂ ሴት ሆነች። ኋላ ላይ ወደ ልቧ ተመልሳ ወደ እምነት መጥታለች። እርስ በርስ ወርልድ ቪዥን ውስጥ እንገናኝ ነበር። እዚያ በመሥራቷ ደስተኛ ስላልነበረች፣ ብዙም ሳትቆይ ትታ ወጣች። ለተለያዩ ‹‹መያዶች›› (NGOs) እንደ አማካሪ በመሆን ሠርታለች፣ ደግሞም በነቀርሳ ከመሞቷ በፊት ስኬታማ ሆና ነበር።

[52]እርሱ ከገዛ ጓዶቹ ጋር ችግሮች የነበሩበት ሲሆን፣ ከአሥር ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ እስር ቤት ውስጥ ተጥሎ ነበር። በእስር ላይ ሳለ ሕያው የሆነውን አምላክ አግኝቶ በእስር ቤት ሳለ ሕይወቱን ሰጠ። በአሁኑ ጊዜ የሚኖረው አሜሪካ ውስጥ ሲሆን፣ ጌታን ያገለግላል። ብዙ ጊዜ “ያ የፖለቲካ ትግል ከጠብመንጃ አፈሙዝ ወጥቶ ያድጋል ብዬ አምን ነበር፤ አሁን ግን ሁሉም ትግሎች ከወንጌል አፈሙዝ ይወጣሉ ብዬ አምናለሁ” ይል ነበር።